
# ላንዳፍታ

የአማርኛ የመዝናኛና የቤተሰብ መጽሔት
1ኛ ዓመት ቁጥር 4 መስከረም 1985

የሰላም፣ የፍቅርና የብልፅግና ዓመት ይሁንላችሁ።





ሳምሶን ብርሃኔ መስከረም 1 1985
ከ"ላንዳፍታ" ጋር 1ኛ ዓመት
የልደት በዓሉን
አክብሯል።
"ፍቅርንና ሰላምን" ከወ[illegible] እየተማርኩ ማደግ እፈልጋለሁ።
ሳምሶን (መስከረም 1 ቀን)

Volume I No. 4


An Amharic Entertainment Magazine

September, 1992





# የኢትዮጵያ መንደር





## ETHIO VILLAGE

### CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



**ቀይ ወጥና ዝግኑ ደር ወጥ አልጫው፤**
**አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።**
**የአበሽ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤**
**ሽታው ገቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።**
**ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤**
**የወጥ የቅመሙ የምግቡ ቃና፤**
**አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።**
**የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤**
**ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።**
**በሰባት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤**
**ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤**
**ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።**

## ማ ው ጫ


ከአዘጋጁ 2

ደብዳቤዎች 4

ኑሮ በአሜሪካ 8
ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ
አሜሪካም መጣን (ከግርማ ዘገየ)
ቢከፍቱት ተልባ (በ.ገ.)
ምን ታዝበዋል?

ልብወለድ 14
ከስደተኛው ማህደር" (ከዶቢሳው)
እልከኛው (ከአቦነህ አሻግሬ)
በቀደምለት በሕልሜ (ከዘላለም ሲሳይ)
ዕድሜ ለቀሚሱ (ከዘውዱ እሸቱ)

አዳምና ሔዋን 26
እስቲ ምን ይላሉ?
ለወ/ሪት ምን ይሻላል (ከዘ.ተ.)
ጓደኛ ለሚፈልጉ
እሱና እሷ

"ደራርቱ ደራረ ቢያ" (ከግርማ ዘገየ) 33

እናስተውቃችሁ 34
ችካጉና ኢትዮጵያኖች
የቺካጉው ኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር

የአበው ቅርስ 38

"ዘሬን አትጠይቁኝ" (ከግርማ ዘገየ) 40

ቢስቁም ባይስቁም 43
ሁሉም ቀልድ ያስቃል?
ቢስቁም ባይስቁም

ጨዋታና ሰንጠረዥ 46



በላንዳፍታ መጽሔት ላይ የሚወጡትን ማናቸውንም ጽሑፎች በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ማስተላለፍም ሆነ በተመሳሳይ መንገድ አባዝቶ ለማሰራጨት በቅድሚያ የዋና አዘጋጁንና የደራሲዎቹን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

# ላንዳፍታ
# LANDAFTA

P.O. Box 409358
Chicago, IL 60640



**EDITOR IN CHIEF & PUBLISHER**
Mekonnen Gessesse

**EDITORIAL COMMITTEE**

Felasfaw Wondimu
Girma Zegeye
Abera Sisay (Photographer)

**ADVISORY COMMITTEE**
Dr. Abera Molla
Dawit Deres

**DISTRIBUTION AGENTS**

**Albo African Shop**
6421 Telegraph Av
oakland, CA 94609
(510)647-4410

**Addisu Gebeya**
2202 18th St NW
Washington, D.C.20009
(202)986-6013

**E.T. Beauty Supply**
7020 Fair Oaks
Dallas, Tx 75231
(214)890-7920

**Dr. Tilahun G. Hiwot**
167 Barker St #B-1
Hartford, CT 06114
(203)296-0254

**MERKATO**
1036 1/2 S. Fairfax Av
Los Angeles, CA 90019
(213)935-1775

**Zelleke Nigatu**
5401 Old National HGWY #508
College Pk. Georgia, 30349
(404)577-1595

**Ethio Village Restaurant**
3462 North Clark St.
Chicago, IL 60657
(312)929-8300

**IN ETHIOPIA**
Birana Electro Publishing Co.
P.O.Box 31387
Addis Ababa, Ethiopia
Phone 514662

COPYRIGHT 1992 MEKONNEN GESSESSE


## ከ አ ዘ ጋ ጁ



እንኳን ከዘመን ዘመን በሰላም በጤና አሸጋገራችሁ። አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የፍቅርና የጤና እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞቴን እገልጻለሁ። "ላንዳፍታ"ም ይኸው የአንደኛ ዓመቷን ሻማ ታበራለች። በመጽሔቱ ሽፋን ላይ የሚታየውም ሕፃን ሳምሶን ብርሃኔ ከላንዳፍታ ጋር የ፩ኛ ዓመት ሻማውን አብርቷል። ሳምሶንም ላንዳፍታም የተወለዱት መስከረም 1 1984 ችካጐ ነው። ሳምሶን የፍቅር፣ የሰላምና የጤና ምኞቱን በላንዳፍታ የሽፋን ገጽ ላይ ተገኝቶ ገልጾላችኋል። "እደግ! ተመንደግ! እንበለው እኛም።

"ላንዳፍታ" በ1 ዓመት ዕድገቷ በአዲስ የፊደል ቅርጽ ተሽሞንሙና ከአጥናፍ አጥናፍ ተዳርሳለች። ብዙ አንባብያን ቀደም ሲል እንጠቀምበት የነበረውን የፊደል ቅርጽ እንድንለውጠው በጠየቁን መሠረት ትክክለኛውን የኢትዮጵያ ማተሚያ ፊደላት ከምዴት በማግኘታችን ደስ እያለን ይህንኑ የተራቀቀ የኮምፒውተር ፕሮግራም በመፍጠርና በማቀነባበር በኩል ለግዕዝ ፊደላት በቴክኖሎጂ ማደግ አስተዋጽዖ ላደረጉት ለዶክተር አበራ ሞላ ከፍተኛ አድናቆቴና ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

"ላንዳፍታ" ከብዙ አንባብያን የድጋፍ ደብዳቤዎችና ጽሑፎች እየደረሷት ነው። ይኸው የአንባብያን ያልተቋረጠ ድጋፍ በመኖሩም ልታድግ ችላለች። አሁኑራትንም አቋርጣ አገሯ ገብታ በኢትዮጵያ መታተምና መከፋፈል ለመጀመር ዝግጅቷ አልቋል።

አንባብያን የራሳቸውን የመጀመሪያ (original) ሥራ በመላክ ለመጽሔቷ ዕድገት ያልተቆጠበ አስተዋጽዖ በማድረግ ላይ መሆናቸውን ስንገልጽ ከከፍተኛ ምስጋና ጋር ነው።

አንድ ስነ ጽሑፍ ከሌላ ደራሲ ወስደው ራሳቸው እንደጻፉት አድርገው በመላካቸው እኛም በስማቸው ካወጣነው በኋላ ከዋናው ደራሲ ጥቆማ በደረሰን መሠረት ሁኔታውን ለማጣራት ችለናል። በሐምሌ ወር ቁጥር 3 እትም ገጽ 38 ላይ የወጣው "ዋ! . . .ኢትዮጵያ" የተሰኘው ግጥም በራሳቸው ስም የላኩልን ሰለሞን ገደይ (ከዋተርበሪ-ከነቲከት) ሲሆኑ እኛም የሳቸው ነው በማለት በስማቸው አውጥተነው ነበር። ሆኖም ዶክተር ፍቅሬ ቶሎሳ (ከካሊፎርኒያ) ደውለው ጽሑፉ የራሳቸው መሆኑን ባደረጉት ጥቆማ መሠረት ሁኔታውን ተከታትለን ግጥሙ የዶክተር ፍቅሬ ለመሆኑ ብዙ ፍንጮች አግኝተናል። አቶ ሰለሞን ለዚሁ መልስ እንዲሰጡን በስልክም በደብዳቤም ፈልገን ልናገኛቸው ስላልቻልን መልዕክቱ በዚሁ በኩል ደርሷቸው መልስ እንዲሰጡበት እንጠይቃለን። ለወደፊቱ የራሳቸውን ስነ ጽሑፍ የሚልኩልን ደራሲያን ድርሰቱ የራሳቸው መሆኑን በፊርማቸው አረጋግጠው እንዲልኩልን በትህትና እንጠይቃለን።

ኢትዮጵያውያን በብዛት በማይኖሩበት አካባቢ "ላንዳፍታን" ለማዳረስ አከፋፋይ ለማግኘት ስለተቸገርን ከ10 ቅጅ በላይ በመግዛት ለማከፋፈል ለሚፈልጉ የ20% ቅናሽ ለማድረግ ወስነናል። ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ ከሆነ ግን የመላኪያ ዋጋ ስለሚጨምር 5% ብቻ ነው የምንቀንሰው።





# እንቁጣጣሽ

## ከገርማ ዘገየ

የወራት ማብቂያ ጭማቂ፣
የአዲስ ዓመት ፍንጣቂ፤
መስከረም!

ያገር ባህል አዲስ ዓመት ጀማሪ፣
እየሃ አበባዬን አዘማሪ፤

ጳጉሜን ተንተርሰሽ፣
ጥቅምትን አስከትለሽ፣
መስከረም እንኳን ደህና መጣሽ።

የወሮች መጀመሪያ፣
የወፎች መዘመሪያ፤

የትንብቱክ ሕፃናት ዜና ልሳን፣
የቀሳውስት ጸሎት ድርሳን።

የዓመት ሙሉ ዕጣ ፋንታ፣
በውስጥ ሆዷ ሁሉን ከታ፤
እንቁጣጣሽን ሞሽራ፣
መስከረም ብቅ አለች ወሯን ቆጥራ።

አበባዬ ሆይ በሉላት ለእንቁጣጣሽ፣
በያመቱ ደግሞ ደግሞ ያምጣሽ፣
እንቁጣጣሽ . እንቁጣጣሽ .እንቁጣጣሽ
እንቁጣጣሽ!

**እንቁጣጣሽ በያመቱ ያምጣሽ !**

**እንኳን ከዘመን ዘመን**

**በሰላም**

**አሸጋገራችሁ**







# ደ ብ ዳ ቤ ዎ ች

ውድ የ"ላንዳፍታ" አዘጋጅ እንዲሁም ለጠቅላላ ተባባሪዎችዋ በሙሉ፤ መጽሔቷን አንብቤ በጣም ተደስቻለሁ። በቀድሞው ዘመን የተሳካ የሕዝብ መገናኛ ዘዴ ስላልነበረና በዘዴ ለመጠቀም ሲባል አበው አንድን ነገር ወይም ሁኔታ ለብዙሃኑ የሚያስተጋቡት ወይም ሕዝቡን ሀሳብ ለሀሳብ የሚያገናኙት በአዝማሪዎች የዘፈን ግጥምና በእረኞች የተረት ተረትና የእንካ ሰላንትያ ጭውውት እንደነበረ ይታወቃል። ታዲያ "ላንዳፍታም" በዘመናዊ ስነልቡና (ሳይኮሎጂ) በመጠቀም እያሳሳቀች ቁም ነገር አዘል መልዕክቶችን እንደ ሊጋ ቅቤ ወደ አጥንት ውስጥ የምታሰርግ ለኢትዮጵያችን የሥነ ጽሑፍ ነጻነትና ዘመናዊነት መርህ ትሆናለች ብዬ እገምታለሁ። ዳሩ ግን ባለመታደልና ባለመታገል እኛ መጀመር እንጂ መጨረስ ዕጣ ክፍላችን ስላልሆነ መጽሔቷን እግዚአብሔር ይባርካት እላለሁ፤ በርታ፣በርታ። የሰንጠረዥ መጠይቅ እኔ እንዳረምኩት ነወይስ ተሳስቻለሁ?

ዘውዴ በዳዳ ማሌ (ችካጐ)

ከአዘጋጁ፤– እርሶ ልክ ኖት፣ ስሁተት ነበረው። እናመሰግናለን።

---

ለውድ ላንዳፍታ አዘጋጅ፤ ሰላምና ጤና ለውድ የሀገር ልጆች ለሆናችሁት የ"ላንዳፍታ" አዘጋጆች በሙሉ ስመኝ ደስታና ኩራት ይሰማኛል። "ላንዳፍታ" ወደትም የማታጋድልና እያዝናናች ብዙ ቁም ነገር የምታስጨብጥ በመሆኗ እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ከሚዘጋጁት መጽሔቶች በምንም እንደማታንስ ሽንጤን ገትሬ እመሰክርላታለሁ። ሆኖም የሚሻሻሉ ነገሮች ያሉ መሰለኝ። የመውጫው ጊዜ ርዝመት ቢያጥር፤– የፊደላት ግድፈት ቢስተካከሉ፤– ልክ እንደ (Ethiopian Review) አቅርቦቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢተረፈረፍ፤– ለሳይንስ ግኝቶች (ቅርብ ስለሆናችሁ) አምድ ብትከፍቱ ጥሩ ነው እላለሁ። መልካም እንግዲህ ብርታቱን ይስጣችሁ እያልኩ ለመጽሔቷ የተኘሁትን ግጥም በማከል ላጠናቅ፣

መጽሔት አንብበው ጥምህት ካልረካ፣
ቁምነገር ካጡበት ልብን የሚነካ፤
ላንዳፍታ መሔድ ነው ወደ አሜሪካ።

ታዬ ጥበቡ
ቄስ ሰፈር–አዲስ አበባ



# ደ ብ ዳ ቤ ዎ ች

ከአዘጋጁ፤– "ላንዳፍታ"ን ኢትዮጵያ አከፋፋይ ስላገኘን የስርጭቱ ችግር የሚቃለል መሰለኝ። የፊደላትን ግድፈት ስለጠቆምከን እናመሰግናለን፤ በተቻለ መጠን ጥንቃቄ እናደርጋለን። ለ"ላንዳፍታ" የተቀኘሀላትን ቅኔ በደስታ ተቀብለነዋል። እናመሰግናለን።

---

ውድ አዘጋጅ፤– ለ"ላንዳፍታ" ረዥምና ሰፊ ዕድገት ወሰንና ዳካ አልባ ነው። ባያሌው ለሳበችኝ መጽሔት ዋና አዘጋጅ ሰላምና ጤና እመኝልሃለሁ። "ላንዳፍታ" በመጀመሪያ በአዕምሮዬ ማሕፀን ሃሳብ ጠነሰሰች፤ በሁለተኛዋ ልብወለድን ለብዕር ጸነሰች። በሶስተኛዋ እነሆ የበኩር ልጅዋን "ዕድሜ ለቀሚሱ"ን ለክብርት "ላንዳፍታ" ለክርስትና ተሰጠ እልሃለሁ። ጽሑፍ አገራችን በአንድ ወቅት በጽኑ ይጉላባት የነበረውን ሁኔታ ልትጠቋቁምና ዛሬም በአሜሪካ ላለነው የትውስታ ትዝታ ቢሆን በሚል የጫጫርኳት ናትና አባክህ አውጣልኝ። እኔም ይህችን ልይ እንጂ በዚህች ተወላክፌና ተጠናፍሬ እንደማልቀር ቃል እገባልሃለሁ።

ዘውዱ እሼቱ ተ፡ክለ አረጋይ
(ቺካጐ)

ከአዘጋጁ፤– አመሰግናለሁ። በዚህኛው እትም በ"ልብ ወለድ" አምድ አውጥተናል። ይልመድብህ ታዲያ።

---

ውድ አዘጋጅ፤– እንደምን ከርመሀል። መጽሔትህን ሳነበሁ ደስ አለኝ። ምንም እንኳን የጽሑፉ ጥልቀትና ብስለት በሌሎች አንባብያንም ቢለካ በኔ በኩል ስክንና ትክን ያለች ግሩም መጽሔት ናትና በየጊዜው እንድትልክልኝ የደምበኝነት ቅጹን ሞልቼ ከነክፍያው ልኬልሃለሁ። በርታ አደራ።

ይታገሱ ተክለ ማርያም
ዲካልብ (ኢሊኖይ)

---

ይድረስ ለላንዳፍታ አዘጋጅ፤– "ላንዳፍታ" የምትባለውን መጽሔት ያወኳት ወንድሜ ሲያነብ አይቼ ነው። ወዲያው ተቀብዬ ማንበብ ስጀምር አዝናኝና አስቂኝ ሆና አገኘሁት። ከሥራ ወጥቶ የደከመ

አዕምሮን ለማዝናናት ከአስፈለገ "ላንዳፍታን" ማንበብ ብልህነት ነው እላለሁ። በዚህ አጋጣሚ ለመጽሔቱ አዘጋጅ ከፍተኛ አድናቆቴንና ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ከማውቃቸው ቀልዶችና ለመጽሔቱ ይጠቅማሉ የምላቸውን ጹሑፎችም ለመላክ እዘጋጃለሁ። ያገኘሁት መጽሔት በየካቲት የወጣውን ሲሆን በጣም ያዝናናኝ "እባብ ለእባብ" የተሰኘው አጭር ልብ ወለድ ነው። ሳነበው አገላለጹ ጁሊ ባር እንዳለ በሀሳቤ መጥቶ ስነ ጽሑፉን እንደ ፊልም እያየሁት መጨረሻውን ያልጠበቅሁት ሆኖ ሳገኘው በጣም ደስ አለኝ።ግሩም የተዋጣለት ጽሑፍ ነው። ጸሐፊው የድርሰት ልምድ ያለው ይመስላል። የቃላት ሰንጠረዥ ጨዋታውም ብዙ የተረሱ ቃላቶችን የሚያስታውስ፤ ጭንቅላት የሚጠይቅና የሚያዝናና ነው። ግን ምነው ሶስት ወር አልበዛም። በየወሩ ቢወጣ በጣም ጥሩ ነው።

ሊሊ ሉችያኖ
ዋሽንግተን፣ሜሪላንድ

---

ለውድ አዘጋጅ፤- በመጀመሪያ የከበረ ሰላምታ ለ"ላንዳፍታ" ዝግጅት ክፍል እያቀረብኩ ይህንን መጽሔት በአጋጣሚ አሜሪካ ለዕረፍት ሄዶ የነበረ ሰው ይዞት መጥቶ አንብቤው በጣም ደስ ብሎኛል። እኔ የምኖረው ሆላንድ ነው። ስለዚህ መጽሔቱን በሚወጣበት ጊዜ ሁሉ እንዳገኝ ስለክፍያው እንድታስረዱኝ እፈልጋለሁ።አደራ እንዳትረሱኝ።

ጥላሁን ሉልሰገድ
1421 AZ Uithoorn
Nederland

ከዝግጅት ክፍሉ፤- አቶ ጥላሁን፤ ስለ መጽሔቱ የላኩልንን አድናቆት በደስታ ተቀብለነዋል፤ እናመሰግናለን። መጽሔቱ በሚታተምበት ጊዜ እንዲላክሎት ለአራት እትም ከነመላኪያው በአሜሪካን ብር $15.00 በአድራሻችን ይላኩ። ለመጼሔቷ ያሎትን አድናቆት በመመርከዝ የዚህን እትም 1 ቅጂ መላኪያውንም እኛው ከፍለን በነጻ ልከንልዎታል። ከሚቀጥለው ጀምሮ ያለው እንዲላክሎት ቅጹን ሞልተው ከነክፍያው ይላኩ። እርሶም መጽሔቱን በሆላንድ ያስተዋውቁልን እንግዲህ፤ ስለ ሆላንድ የኢትዮጵያኖች አኗኗር ቢጽፉልንሳ?

---

ለ"ላንዳፍታ" አዘጋጅ፤- ጤና ይስጥልኝ፤ "ጓደኛ ለሚፈልጉ"የሚለውን አምዳችሁን ወድጃለሁ። እንዳላችሁት ጥንቃቄ አድርጋችሁ የኔን ፍላጐት አውጡልኝ። ደምበኛ ለመሆንም ክፍያውን ልኬአለሁ።

እ. (ከአሜሪካ)

ከዝግጅት ክፍሉ፤- ስምን ያላወጣነውም ለዚሁ ነው። ክፍያው ደርሶናል። እናመሰግናለን።

---

ተወዳጁ የ"ላንዳፍታ" አዘጋጅ፤- እሰየው መጽሔትህ በጥራትም በገጽ ብዛትም እየተሻሻለች ስለመጣች ነው መሰለኝ ባለፈው እትም ሁለተኛው ገጽ ላይ ያለው ምስልህ የሥራ ውጥረት የበዛብህና "በጣም busy ሆኜ የድካሜ ውጤት ነው የሚል ይመስላል። ታዲያስ። ቀልዶች ልኬልሃለሁ።አንተን ካሳቀችህ ብቻ ነው ታዲያ የምታወጣው። አለበለዚያ የቃሻሻ ማጠራቀሚያህ ውስጥ እኑራት።

ብርሃን አብርሃም
ከዋሺንግተን ዲ ሲ

ከአዘጋጁ፤- አላሳቀኝም ብልሳ? ትንሽ ስለኮረኮረኝ እንዱን አውጥቼዋለሁ። ሌሎቹን የሚቀጥለው ላይ እወጣዋለሁ። በኔ ይሁንብሽ ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ እጠገቡም አላደርስ።

---

ለ"ላንዳፍታ" አዘጋጅ፤- የከበረ ሰላምታችን ስናቀርብ ዝቅ ብለን ነው። በመጽሔቱ ዝግጅት ተደስናል። ባለፈው እትም "ጓደኛ ለሚፈልጉ" የሚለው ልባችንንን ነክቷል። ስለዚህ እኛም ጓደኛ ስለምንፈልግ በርቀት የተነሳ ባንገናኝ እንኳ እንድንጻጻፍ አውጣልን።

እ.ና ብ. (ከሆላንድ)

ከዝግጅት ክፍሉ፤- ወጥቶላችኋል። ይቅናችሁ። ስማችሁን ያላወጣነው ለዚህ ነው።

---

ለ"ላንዳፍታ" 1ኛ ዓመት መታሰቢያ
ከወንድ ወሰን ይመር (ቺካጐ)

ላንዳፍታ እውነትም ላንዳፍታ፣
ግን በውስጥሽ ያለው ትምህርት ሰጪ ትዝታ።
ዳር እስከ ዳር ተሰራጭተሽ፣
እዚህ ቺካጐ ተመስርተሽ፤
በገጽ ብዛት ቁም ነገር ጨምረሽ፤
እንኳን አደረሰሽ ለአንደኛ ዓመትሽ።
ላንዳፍታ እለሽ መኩንን ጸሐፊው፣
አንባቢዎች አሉሽ የማትሰለችው።
መልዕክትሽን ሲያነቡት፤
ታረኪያለሽ ላንዳፍታ በውነት።
ልብወለዱ ገጠመኙ ተረትና ምሳሌው፤
ሁሉም ነገር አዝናኝ ነው።
እኔስ አልኩሽ ለዘወትር፣
መልዕክትሽ ሁሉ ጣፋጭ እንደማር።
-----

ከዝግጅት ክፍሉ፤- እናመሰግናለን ወንድወሰን፤
"አንተን የመሰለ ደጋፊ ስላላት፣
ላንዳፍታም አይደለም ለሁሌም ኩሩ ናት።"

---

ለ"ላንዳፍታ" መጽሔት አዘጋጅ፤- እንደምን ሰንብተሃል። እንኳን ከዘመን ዘመን አሸጋገረህ። "ላንዳፍታ" መጽሔትህን በተከታታይ አግኝቼ ተመለከትኳት። መቸም ዛሬ ቦጠሊቀኛ በበዛበት ጊዜ እንዲህ እንደአንተ ከቦጠሊቃ ሌላ ሕይወት ያለ መሆኑን ሲያስመለክተን ምንኛ መታደል መሰለህ። የቁሉቢው ቢያስመለክትህ ነውና እንዲሁ በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ አወያየን፤ አዝናናን፤ አሳውቀን! ትንሽም እንደ ሰው ይመርብን እንጂ።

ይኼ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርጌ የላክሁት በሐምሌ ወር የ"ላንዳፍታ" እትም ላይ "እኔስ የሚሆነኝ ባል ጠፉ ብል!" በሚል ርዕስ ወ/ሪት "ምን ይሻላል" ለጻፈችው መልስ ቢጤ ነው። የወይዘሪቷ አድራሻ የለኝም። አንተ ሳይኖርህ አይቀርም ብዬ እንዲላክላት እነሆ ወዳንተ አሻገርኩት።

ከአንተ ወደሷ ማሻገሪያውን ቴምብር ይኸው በሽልንግ ካራት ፍራንክና ከሁለት ቤሳ ገዝቼ ልኬልሃለሁ። ካልሆነም አጣጣፉን አጠዳዳውና በመጽሔቱ እንዲወጣ ዕድል ስጠው።

በዚሁም ላይ ልጅቷ ዘንድ ወርደህ "አባት ትሆኑን ልጁ እንሆናችሁ ዘንድ መጣን" ትልልኝ ዘንድ ሽማግሌ አድርጌ እልክሃለሁና ፈረስህን ጫን። መልካም ዓመት።

ዘ. ተ. (ከሎስ አንጀለስ)

ከአዘጋጁ፤-

በነገራችን ላይ ቁርጡ አስቲታወቅ በሚል ስምህን በአጫጭር ፊደል መጻፌ ልክ መሰለኝ፤ ቅር እንደማይልህ ተስፋ አደርጋለሁ። ሽማግሌ ሁነኝ ብለሃልና እንዲያ ማድረጌን በጸጋ ተቀበለው።

እርሶታህን መንቀፌ አይደለም እንድቀይረው ያደረገኝ፤ (እርሶ ብለህ ስለጻፍክና እኔ ደግሞ ስለቀየርኩት) አንተ ተብዬ የሚነገረኝ ነገር ከቅርበት የመነጨ ስለሚመስለኝ ነው። ለማንኛውም እኔ ብቻ ሳልሆን የዝግጅቱ ክፍል አባላት ሽምግልናውን ተቀብለን አትላንታ ለመውረድ ፈረሳችንን ጭነናል። በልጅቷ በኩል ያለውን እንስማና መጀመሪያ።

እሷም ነገሩን እንድታውቀው መጽሔቱን በነጻ በአድራሻዋ ልከንላታል፤ ያንተንም ስምና አድራሻ ጨምረን። በል ይቅናን እንግዲህ።

---

ለውድ አዘጋጅ፤-

የ"ላንዳፍታ" ሶስተኛ እትም ድንገት እጃችን ላይ ወደቀች፤ ወደድናት፤ አዝናኝ ናት። ማህበራዊ ጉዳዮቿ ለእኛም ትምህርት የሚሆኑ ብዙ ቁምነገሮች ይዛለች። ፈቃድህ ከሆነ በኢትዮጵያ የማሳተምና የማከፋፈሉን ሥራ ለመውሰድ መስማማታችንን ልንገልጽልህ እንወዳለን። ዝርዝር proposal ልከናል።

ብራና ኤሌክትሮ አሳታሚ
አዲስ አበባ

ከአዘጋጁ፤- በጣም ደስ ይለኛል። ለአገር ያልሆነ ለማን ሊሆን? ዝርዝሩን በደብዳቤ እልክላችኋለሁ።

---

ለላንዳፍታ አዘጋጅ፤-

እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሰህ። መጽሔትህን በተከታታይ አየሁት። ጉሽ የሚያሰኝ ነው። አንዳንድ በመጽሔቷ የወጡት ጽሑፎች እዚህ ዲ ሲ ባሉ አንዳንድ ሬዲዮ ጣቢያዎች ሲነበቡ እሰማለሁ። ፈቅደህላቸው ነወይስ በጉልበታቸው የሰውን ድርሰት የማያነቡት? ከተፈቀደላቸው ለምን በቅጡ አያነቡትም። "አሜሪካም መጣን" የሚለውን ጽሑፍ ሲያነቡት ምነው ለዛ አሳጡት? በሬዲዮ ከተሰማ ለምን መጽሔቱን ለመግዛትስ እሂዳለሁ? መጽሔቱን ለማስዋወቅ ከሆነ ሃሳባችሁ እባካችሁ በሥርዓቱ ይነበብ በሉዋቸው። ከመነበቡ በፊት ልምምድ የተደረገ አይመስልም። እና አስቡበት።

ዳኜ (ከዋሽንግተን ዲ.ሲ.)

---

## ውድ አንባብያን፤

የምትልኩልንን ደብዳቤዎች አጠራ አጠር ብታደርጉ ለሁሉም የመደብነውን ገጽ ለማዳረስ እንችላለን። ዘግየት ብለው የመጡትን በሚቀጥለው እትም እናወጣለን።
ስለመጽሔቷም ሆነ ስለሌሎች ጉዳዮች በአጭሩ የተዘጋጁ ደብዳቤዎቻችሁን በሚቀጥለው አድራሻ ብትልኩልን ደስ ይለናል።

LANDAFTA
P.O.box 409358
Chicago, IL 60640

---

የሳምሶንን እናትና አባት ወ/ሮ አፀደ ይመርንና
አቶ ብርሃኔ ሺፈራውን ከልብ እናመሰግናለን።

ኢ. ቲ. የቁንጅና ዕቃዎች አከፋፋይ

# E.T BEAUTY SUPPLY & WHOLESALE



*7020 Fair Oaks*
*Dallas, Texas 75231*
*(214) 890-7920*

SPECIALIZING IN
ETHNIC
HAIR CARE

*We will gladly accept your personal check*
ይህችን ማስታወቂያ ይዞ ለሚመጣ 10% ከጠቅላላ ሽያጭ ቅናሽ እናደርጋለን።
*10% off total purchase with coupon*
*(offer expires 12-1-93)*

የባሮ ባንድ

# BAARO BAND

*WITH THEIR NEW ETHIO-WORLD BEAT SOUND*

BAARO


የ ባ ሮ ባ ን ድ



**FOR BOOKING INFORMATION CALL (708) 724-6819 or (312) 561-6865**




# ኑሮ በአሜሪካ



ኑሮ በአሜሪካ



# ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ

እንዴት ከረማችሁ? እንኳን ከዘመን ዘመን በሰላም አሸጋገራችሁ። በአሜሪካ ኑሯችሁ በዚህ በአዲሱ የኛ ዓመት ምን እቅድ አወጣችሁ? በ1985 ማለቴ ነው። ሲጋራ ለማቆም፣ ብር ለማጠራቀም፣ ትምህርት ቤት ለመግባት፣ አዲስ መኪና ለመግዛት፣ ሚስት/ባል ለማግባት፣ ቤት ለመግዛት፣ ወዘተ. . . ማቀድ ወይም መዛት ልበለው መሰለኝ፣ አዲስ ዓመት በገባ ቁጥር የተለመደ ነው። እና ታዲያ የትኛውን አቅዳችኋል? ደግመን እንመርቃችሁ፤ "እንኳን ከዘመን ዘመን አሸጋገራችሁ፤ ያሰባችሁት፣ ያለማችሁት እንዲፈጸም ምኞታችንን እንገልጻለን።"

መቸም እንቁጣጣሽ ዕለት እንደ አገር ቤሣ በግና ወሰራ ዶሮ ባይታረድም ጓደኛና ዘመድ ተሰባስቦ ያገርን ባህል በማስታወስ ተገባብዞ፣ ተጫውቶ አዲስ ዓመትን መቀበል ውጭ አገር በምንኖር ኢትዮጵያውያን እየተለመደ መጥቷል። በጠላው ፋንታ ቢራ፣ በምትታረድ ዶሮ ፋንታ የchicken legs እና breast በገፍ፣ በትልቅ ሸንጥና ታላቅ ፋንታ በኪሎ የተገዛ የብርስኬት ሥጋ (እንዳገር ቤቱ በተፈጥሮ ሳይሆን በኬሚካል የደለበ በሬ ሥጋ)፣ በአረቄ (ቁንዲፍቱ) ውይም እናትና ልጅ ፋንታ ሺፋዝ ውስኪና ኩርቫዚየር በቆሎ ፋንታ ፖፕ ኮርን፣ ወዘተ . . . ይደረደራል። የአገር ዘፈን ቴፕ ይዘፍናል። በቃ ምን አለፋችሁ፤ ሲጨፍሩ መዋልና ማደር ነው። ወደ አገር ደግሞ ስልክ ይደወላል። ዘመድ አዝማድ እንኳን አደረሳችሁ ይባላሉ። አገር ከሙቼውም የበለጠ ትዝ የሚለው ይኼኔ ነው። ይህ ሁሉ እንግዲህ የሚሆነው በመኖሪያ ቤት ውስጥ ነው።

ከቤት ወጣ ካሉ ግን ምንም የበዓል መንፈሱ አይታይም። ከኛ ሌላ ማን የኛን በዓል ያውቅልንና። "Today is Ethioipan New year." ትሉታላችሁ አንዱን የዚህ አገር ጓደኛችሁን። "New Year! You are kidding? In September" ይላችኋል። "You know what year it is?" ብላችሁ ትጠይቁታላችሁ። "You think I am crazy or something? It is 1992." ይሆናል መልሱ። "Not in Ethiopia. It is 1985 now"."1985?" ይልና በመገረም ያያችኋል። እውነት አይመስላቸውም። የምናሾፍ የሚመስላቸው አሉ። አንዷ አሜሪካዊት እንዴ እንደዚያ ስላት፣ "Are you telling me that I will be 7 years younger if I go to your country?" አለችኝ፤ ማሾፏ ነበር።

በበስደትም፣ በትምህርትም ሆነ በሌላ ጉዳይ አሜሪካን አገር የምንኖር ኢትዮጵያውያን ሁሉ በቆይታችን አንድ ዓመት ጨምረናል ማለት ነው። በቀናት፣በወራት ቆይታችንን እየቆጠርን ዓመታት እንደ ነፋስ ሽው እያሉ ሲያልፉ ይገርማል። "ከመጣሁ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት፣ አስር ዓመት ሞላኝ ማለት ነው? ይገርማል እኮ!" እያልን ብዙዎቻችን ራሳችንን እንጠይቃለን። ቀንቶን ትምህርታችንነ ያገባደድን፣" አይ ዘንድሮ ባይሆን በሚቀጥለው ዓመት ትምህርት ቤት እገባለሁ ፣"ብለን የወሰን፣ "የትምህርት ነገር እንኳ አልሆን ብሎኛል፣ እስቲ ጥሩ ሥራ ሰርቼ ገንዘብ አጠራቅሜ የራሴን የንግድ ሥራ ጀምራለሁ ብለን የወሰን፣" አገር ቤት ለመመለስ ወይም ጐብንተን ለመምጣት የወሰን፣ ሌላም ሌላም ዕቅድ የነደፍን ሁላችንም ከአንድ ሐቅ ልንሸሽ አንችልም። ይህም ሐቅ በዕድሜአችን ላይ አንድ ዓመት መጨመራችን ነው። ጊዜው እንዲህ እንደ ነፋስ ሽው እያለ ሲያልፍ "ወይኔ እምና እንዲህ ሰርቼ ቢሆን ኖሮ!" ብለን የሚቀጥለው ዓመት ጸጸት እንዳንገባ ዕቅዳችንን በተግባር ለማዋል እንበርታ።

ዓምናም ዓምና ነበር ካቻምናም ካቻምና፣
ዘንድሮን ሥራበት ያመልጥሃልና።

# አሜሪካም መጣን፣

ከግርማ ዘገየ ይግለጡ

. . . ካለፈው የቀጠለ

ባለፈው እትም በምድር አሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የኑሮ ገጠመኝና፤ አገር ቤት ያሉ ዘመዶቻችን ስለኛ ያላቸው ግምት፤ እንዲሁም ያንድ ጉብል አስገራሚ የሕይወት ድራማ አቅርቤላችሁ ነበር። የዛሬውም ጽሑፌ ከዚህ አያልፍም። እስኪ አንድ ጥያቄ በጅምላ ልጠይቃችሁ። ወደዚህ አገር ከመምጣታችሁ በፊት ለስንት ዘመዳችሁ፣ ለሚያውቃችሁና ይቀርበኛል ለምትሉት ሰው ልታደርጉ ቃል የገባችሁት ነገር ትዝ ይላችኋል? ለወላጆቻችሁ የወር ተቆራጭ ገንዘብ፣ ለታናናሾቻችሁ የውጭውን ዓለም ፋሺን ልብስ፣ ለምታውቋቸውን ለሚቀርቧችሁ እጃችሁ የገባውን ማንኛውንም የገበያ ሸቀጥ፣ ውለታው ለጠነከረባችሁ ደግሞ ከሜዳ ይታፈስ ይመስላችሁ የነበረውን "የጉብኝት ደብዳቤ"፤ ብቻ ለሁሉም እንደየቅርበታቸው ለምታውቁት ሁሉ የገባችሁት ቃል የአሜሪካንን ምድር ስትረግጡ ፈጽማችሁታል? ወይስ "የእምቧይ ካብ" ሆኖባችኋል?

ይህንን ያለ ምክንያት ያነሳሁት እንዳይመስላችሁ፤ የምለው ስላለኝ ነው። ጊዜው ረዝሞ ካልዘነጋችሁትና የሩጫው ኑሮ ካላስረሳችሁ በስተቀር በአብዛኛው አገሩን ለቆ ከባህር ማዶ ለሚሻገር ማንኛውም ሰው ቤተሰብ ዘመድና የቅርቤ የሚሉት ሰው ሁሉ ከስንብቱና ከመልካም ምኞቱ ቀጥሎ በልቦናችሁ እንድታሳድሩት አጥብቆ የሚወተውታችሁ አደራ የሚላችሁ ነገር አለ። ኑሮ የተሳካለትና ኮከቡ የገጠመለት ውሎ አድሮም ቢሆን ጥያቄውን በከፊልም ሆነ በሙሉ ይፈጽማል። "ያለመው ሌላ የገጠመው ሌላ፣" የሆነበት ደግሞ ወዳጆቹን ላለማሳፈርና ላለማስቀየም በ"ፋታ ስጡኝ" መከረም ይፈልጋል። ተስፋ የማይቆርጡት ወዳጆች ግን የደብዳቤያቸው መከታተል፣ የጽሑፋቸው መርዘም የጉድ የሚያሰኝ ነው። ያንዳንዶቹ ደብዳቤ ከማስገረም አልፎ ያስቃል። እስቲ ይህን ደብዳቤ ተመልከቱት፤

"ቀን በሀሳቤ ሌት በሕልሜ ለማስብህ ዘወትር ትዝታህ ካይኔ ለማይጠፋው ውድ ወንድሜ ... መለየት የሚሉት ክፉ ቀን ከለያየን ጀምሮ በብርቱ ለጤናህ እንዴት ነህልኝ?መቼም ያንተ ነገር እንደማይሆንልኝ ታውቃለህ። ካገኘኋቸው ሰዎች ጋር የማወራው ስላንተ ነው። እንኳን የሰለጠነው ዓለም ገብተህ ይቅርና እዚህም ሆነህ ለዕድገት ታደርግ የነበረው ምን ጊዜም አይዘነጋኝም። በተለይ እኔን ለመምከርና ሕይወቴን ለመለወጥ ያደረግህልኝ ውለታ በልቤ ትልቅ ቦታ አለው።" ይልና ሌሎችን ሐተታዎች በመጨመር ወደ መደምደሚያው ላይ "መጨረሻ ልገልጽልህ የምፈልገው ባለፈው ደብዳቤዬ እንደጻፍኩልህ ለሠርጌ የቀረኝ 8 ወር ብቻ ነው። የኔ ሙሉ ልብስ እንኳን ቢዘገይ የቧን የሙሽራ ልብስ ቀደም አድርግልኝ። በእርግጥ እንዳልረሳህ አውቃለሁ። ቢሆንም ጊዜው ገና ነው ብለህ እንዳልዘነጋህ አውቃለሁ።"

. . . ምን ጊዜም ናፋቂህ።

እንዲህ ዐይነት ደብዳቤ ደርሷችሁ ስታነቡ ብዙ ነገር አዕምሮአችሁ ውስጥ ይመላለሳል። ከጸሐፊው ጋር ይህን ያህል የጠበቀ ወዳጅነት እንዳልነበራችሁ ለማወቅ ጊዜ አይፈጅባችሁም። የሱንም ሕይወት ለመለወጥ ምክር የለገሳችሁበት ጊዜ ትዝ አይላችሁም፤ ምን የሚሉት ጉድ ነው?፣ ለማለት ይቃጣችኋል።

የደብዳቤ ነገር ከተነሳ ከቤተሰብ ስለሚላክ ደብዳቤ እስቲ ትንሽ ላውጋችሁ። መሐይም ከሆኑ በጎረቤት ልጆች፤ ልጆች ካሏቸው ደግሞ በታናናሾቻችሁ ወይም በቅርብ ባሉ የቤተሰብ አባላት የተጻፈ የእናት፣ የአባት፣ የእህት ወይም የወንድም ደብዳቤ ሲደርሳችሁ ደስታችሁ ወሰን እንደሌለው አይጠረጠርም። ከቤተሰብና ከወላጅ የቀረበ ስለሌለ ከሁሉ ቅድሚያ ተሰጥቶ በርጋታ የሚነበበውም እንዲህ ዓይነት ደብዳቤ ነው። እስቲ አንድ ደብዳቤ እንመልከት፤

" ልጄ፣ ወንድሜ . . . አይ ክፉ መለየት! እንደጨው ዘር ተበታትነን ቀረን፤ አንድ ቀን እንገናኛለን በሚል ተስፋ እጽናናለሁ። ለመሆኑ ለጤናህ እንዴት ነህ? አገሩ ምንም እንደማይል ባለፈው ድብዳቤህ ስትግልጽልኝ ከልቤ ደስ አለኝ። ጉሽ ልጄ በርታ፤ ያ ማታ ማታ ስተኛ ያቃዠኛል ያልከው አሁንም አልተወህ ወይ? በጣም አሳስቦኛል። አይ ልጄ መቼም አንተ ምቀኛ አያጣህ፤ ምናምኑን እዙረውብህ ይሆናል። የዛሬ ሰው እኮ አይታመንም። ለሁሉም ጠንቀቅ በል። እኔ እናትህ ደግሞ ዝም ያልኩ አይምሰልህ። ልክ እንደ ጻፍክልኝ ነው ለገብሬል የነገርኩት፤ እሱ መቼም የኔን ልመና መሬት ጥሎ አያውቅም፣ አይዞህ ምንም አትሆንም ተስዬልሃለሁ፤" ይልና ወደ መጨረሻው ላይ "መቸም እንዳልረሳኸው ተስፋ አደርጋለሁ፤ ላንተ ገልጨ ባልነግርህም በደህና ከዚህ ወጥተህ ያሰብከበት እንድትደርስ፣ ለቁልቢ ገብሬል 2 ምንጣፍ፤ ለግቢው ገብሬል 1 ግንጥላ፤ ለአጥቢያችን ኪዳነ ምህረት 6 ፓኮ ሻማና 12 ጧፍ፤ ለተክልዬ የንግሳቸው ዕለት 8 ኪሎ ዘቢብ፤ ሁሌ በፀሎታቸው እንዳይረሱህ ስምክን እንዲያነሱህ ለአባታችን ለመምሬ ልሳኑ 9 ዙር የራስ ጥምጥም ተስያለሁና ዛሬ ነገ ሳትል እንድትልክልኝ። እኔ ከዚሁ ፈላልጌ ስለቴን አገባ ነበር፤ ግን ለቄስ ነግሬ አይሆኖም አሉኝ፤ ያንተው ገንዘብ መሆን አለበት። አደራ እንዳትረሳ፣ በኋላ መቀሰፍ ነው። " የሚል የእምነት ማስፈራሪያ ጭምር ያለበት ደብዳቤ ወይም ተመሳሳዩ ደርሷችሁ አያውቅም። አንዳንዴ

ደብዳቤውን ያዘጋጀው ታናሻችሁ ከሆነ ከስሩ " እኔም ለሲኒማ ራስ $5 ተስዬልሃለውና ቶሎ ላክልኝ!" የሚል የተጻፈበት ደርሷችሁ ያውቃል?

እስቲ እናንተ ባልተስማማችሁበት ጉዳይ የሚሰጥ የስለት ጋጋታ ምን ይባላል?

ሌላም የሚገርመኝ አለ! ላጫውታችሁ።አንድ በቅርብ የማውቀው የወንዜ ልጅ ከምኖርበት ከተማ ወጣ ብሎ ካለ ሰፈር ይኖራል። በአብዛኛው የአበሻ ዓይን ማየት ሲናፍቀኝ ሮጬ የምሄደው እሱ ጋ ነው። የራሳችን በሆነው ቋንቋ ስናወራ! ስንከራከርና ስንሚጉት ደስ ይለኛል። በጠባዩ ስለምቀርበው "ወንዝ ከተሻገሩ ያገር ልጅም የሥጋ ዝምድና ያህል ነውና!" የሚቸግረኝን ሁሉ የማዋየው እሱኑ ነው። ከትችት ይልቅ ምክር ላይ ያተኩራል። ከመናገር ማዳመጥን፣ ከክፉ ይልቅ ደግ ደጉን ማሰብ ይወዳል። ይኸው ከናት አገሩ ከወጣና ከሚወዳቸው ቤተሰቦቹ ከተለየ ያንድ ወጣት ጉብል ዕድሜ ሊያክል ምንም አልቀረው። ታዲያ አሁንም ልቡ ሁሌ አገሩ ነው። ሁሌ ጓዙን ጠቅሎ አገሩ ሲገባ ይታየዋል። በዕውቀትም ደረጃ አልተጎዳም። ከአንድም ሁለት የዕውቀት ማስረጃዎችን ጨብጧል። ጣራውን ለመምታት አሁንም አንገቱን ከመጽሐፍት መሐል እንደደፋ ነው።

ታዲያ ምን ሆነ መሰላችሁ፣ ይህ ወዳጄ በዙ ጊዜ ገልፍጦ መሳቅ ከተፈጥሮው ውጪ ናቸው! ደስታውን የሚገልጸው ምጥን ባለች አጭር ፈገግታ ብቻ ነው። አልፎ አልፎ ቅዳሜን አብረን ስለምናሳልፍ እሱ መኖሪያ የደረስኩት በረፋዱ ላይ ከሰዓት በኋላ ከሥራ መልስ ነበር።

በዕለቱ በፊቱ ላያ የተለየ ፈገግታ ይታይበታል። አለምክንያት ሳቅ ሳቅ ይለዋል። ነገሩ ለኔ አዲስ ቢሆንም የገጠመው ጥሩ አዲስ የምስራች እንዳለ በመገመት የሆነውን ነገር ጠየቅሁት። በዝርዝር ሊነግረኝ አልፈለገም። በደፈናው "ከአገር ቤት ቅመም ተልኮልኛል፣ ላንተም ትንሽ ውሰድ!" አለኝ። የተፈቀደልኝን ድርሻ ለመውሰድና የቅመሙን ዓይነት ለማየት ከመቀመጫዬ ተነስቼ ወደ ማዕድ ቤት አለፍኩ።በትንሽ ካርቶን ውስጥ በተለያየ ዓይነት መጠቅለያ የተጠመጠመ ነገር ነው። ምንነቱን ለማወቅ ፈጥነን መፈታታት ጀመርን። ከላይ ካኪ ወረቀት፣ ከዚያ ወፍራም ላስቲክ እንደገና ወረቀት ከዚያ ላስቲክ። ሁሉንም ጨራርሰን ምንነቱን አረጋገጥን። ለጥንቃቄው ጥሩ ዘይደዋል። በጭነት ብዛት ቢፈታ እንኳን መጠቅለያው ውስጥ የወጣው መጠኑ የማይታመን ነው። ወረቀቶቹን ቁሻሻ መጣያ ውስጥ ጨመርንና ሚጥሚጣውን ወደ ሰፌ ጠርሙስ ገለበጥነው። በትንሹ የ'ራት' ብልቃጥ ግማሽ ሊሆን ምንም አልቀረው። በጣዕሙ ይህ ቀረው አይባልም! እኔ በበኩሌ ደስ ብሎኛል፣ ከላዩ አንድ ሁለት የሾርባ ማንኪያ ማግኘቴ ስለማይቀር፣ ለሽታ ትንሽ ሳያከርመኝ አይቀርም። ሳቁን መቆጣጠር ያልቻለው ወዳጄ ደጋግሞ የሚፈነዳ ሳቅ ያፍነዋል። የገጠመውን እንዲያጫውተኝ አጥብቄ በመጠየቄ ከቅመሙ ጋር አብሮ የመጣውን አራት ገጽ ደብዳቤ እንዳነበው ሰጠኝ። ደብዳቤው በናፍቆት ሰላምታ ይጀምራል። ሰላምታው ብቻ አንድ ገጽ ያህል ነው። ታዲያ ይህ ምን ያስቃል ናፍቆት ይቀሰቅሳል እንጂ ብዬ በልቤ ታዘብኩት።

"እባክህ ከሶስተኛው ገጽ ጀምርና አንብብ፣ ቁም ነገሩ እሱ ላይ ነው!" ብሎ ሳቁን ለቀቀው። እንዲህ ይላል!

". . . ሙቼም ያለብንን ናፍቆት ለመግለጽ የሚስማንን በሙሉ ለመጻፍ ቃላት ያጥረናል። ወደ ቁም ነገሩ እንግባና ይህን ሚጥሚጣ ከገበያ በዕውቅ ፈልጋ የገዛቼው ዓለሚቱ ናት። እሷ መቸም ለዚህ ማን ብሏት። ለቅማና ቀንጥሳ ያሰጣችው ያቺ ዘነቡን ታውቃት የለ የጋሽ ፍልፍሉ ልጅ፣ ይኸውልህ እሷው ናት፣ የተባረከች ልጅ፣ እንኳን እሷ ቀርቶ ደካማ እናቷ ለጸሐይ የተሰጣውን ዶሮዎች እንዳይለቅሙ ሁለት ቀን ሲከላከሉ ውለዋል።"(ያገሬ ዶሮ ሚጥሚጣ ሲለቅም ታየኝ)" . . . የታመሰውና የተወቀጠው በአጉትህ ልጆች በሰናይትና በበልዩ ነው። ብቻ ያኔ አንተ ስትሄድ ትንንሾች ነበሩ! ብዙም አታውቃቸው! ይልና ወደሚቀጥለው ገጽ ሲገባ፣ "እንደምታውቀው ጊዜው እንኳን ዘመድ ባዳ የሚረዳዳበት ጊዜ ነው። በተቻለህ ውለህ ሳታድር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ብትልክ ደስ ይለናል። ታዲያ ስትልከው በአደራ ደብዳቤ ይሁን። . . ."ዝርዝሩ የጉድ የሚያሰኝ ነው። በሚጥሚጣው ዝግጅት ላይ ለተሳተፉት በሙሉ ከጫማ እስከ ሹራብ በራሳቸው ምርጫ በዝርዝር እንዲላክ ይጠይቃል። የጫማና የወገብ ቁጥር ተዘርዝሯል። አልፎ ተርፎ ጉረቤት የሚኖሩት የሰማንያ ሰባት ዓመቷ እማማ ጣዲቄ " ምነው ልጄ አሳድጌ አሳድጌ ዝም አልከኝ!" ያሉት ሰፍሯል። አሮጊቷ እማማ ጣዲቄ እንኳን ሊያሳድጉት ቀርቶ መሐን በመሆናቸው የልጅ ፍቅር ስለሌላቸው አዘውትረው በሕጻንነቱ የሚጫወቱበትን፣ የጨርቅ ኳሱን ሽንት ቤት ይጨምሩበት እንደነበረ ያጫወተኝ በኋላ ነው።

እና ይኸውላችሁ ዕለቱን ባልታሰበ ሳቅ ታጅበን በመዋል ማምሻው ላይ ተለያየን እላችኋለሁ። ታዲያ አንዳንዴ በስልክ ስንገናኝ "የቅመሙን ዋጋ ከፈለክ" እለዋለሁ። "ደህና የረሳሁትን አታስቀኝ!" ይለኛል።

. . . ይቀጥላል

# "ቢከፍቱት ተልባ"

በ.ገ. (ከቺካጐ)

"አላማርሺኝም" በሚል ርዕስ ከፈላስፋው ወንድሙ ችካጐ አሁን ስላለንበት አገር ማለትም ስለ አሜሪካ ሰፋ ያለ መልዕክት በጉጉም አቅርበዋል። በእውነት በ2ኛውና በ3ኛው ስንኞች ላይ እንዳሉት አሜሪካን ሁላችንም ብዙ አስበን ተመኝተን ለፍተን ተንከራተን ደርሰንበታል።

በእርግጥ ሁሉም ነገር እንደተነገረንና እንደተወራለት ባይሆንም በአገራችን ያጣነውን ሰላምና ነፃነት አግኝተን ለቤተሰቦቻችንና ለሀገራችን ሁሉ የምንረዳበትና ጥሩ ኑሮ የምንኖርበት አገር ሆኗል። በውነት ስንቶቻችን ነን በአገራችን ውስጥ ከራሳችን አልፈን ቤተሰብ ሆነ ወዳጅ ዘመድ የምንረዳው? ስንቶቻችን ነን የተማርነው? አሁን የአለንበት አሜሪካ ግን የመማር ሆነ የመሥራት ዕድሉ ተገኝቶ ተሟልቶ በውን ቀርቶ በሕልም በስም እንኳን የማናውቀውን ሽንጣም መኪና የምንነዳው? ስንቶቻችን ነን የስንት ትልልቅና ትንንሽ የግል ንግድ ባለቤት ይሆን?

በውነቱ "አሜሪካም መጣን" በሚለው የግርማ ዘገዬ ጹሑፍ ላይ "ሁሌ አዲስ ነገር ፈላጊ አገር፤ ለኑሮም ደከመው እስከለፉና በሰው ሳይሆን በራስ እስካመኑ ድረስ የድካም ዋጋ በተገቢ መንገድ የሚገኝበት አገር ናት፤" ሲሉ የግል አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ታዲያ እኔ አገሬን ጠልቼ ሳይሆን የእኛም አገር ኢትዮጵያችን ተፈጥሮም ሆነ የውስጥ ቀበኛው እምላክ ገላግሎን አንድ ቀን በልጆቿ ትገነባና አሜሪካን ትሆናለች።

እንግዲህ "ላንዳፍታ" የጐደለውን አስተካክለሽ የዚህ ዓይነት አጉል እምነት ላላቸው ሰዎች ያሉበትን ለማያመሰግኑ ትምህርት ስጪልኝ እላለሁ።

++++++++++++++++++++++++++++++++++++

## + ውድ አንባብያን +

"ኑሮ በአሜሪካ" በተባለው አምድ ላይ እንዲወጣላችሁ የምትፈልጉትን ገጠመኞቻችሁን፤ አስተያየቶቻችሁን ሆነ ሌሎች በጻፉት ላይ ልታቀርቡ የምትፈልጉትን ትችቶች ልትልኩልን ትችላላችሁ። በአሁኑ ጊዜ "ላንዳፍታ" አገር ቤት የሚሰራጭ ስለሆነ ወደዚህ ለመምጣት የሚፈልጉ ወገኖቻችን ከመምጣታቸው በፊት ስለ አሜሪካ ደህና ግንዛቤ ሊሰጣቸው ይችላል የሚል እምነት አለን። ከዚህ በተጨማሪ ሥራ ለማግኘት፤ ትምህርት ቤት ለመግባት፣ የራስን የንግድ ሥራ ለመክፈት፤ የጤናና የኢንሹራንስ አገልግሎት ለማግኘት ወዘተ... የሚረዱ ሀሳቦችን የያዙ ጹሑፎችን ላኩልን።

===========

# ምን ታዝበዋል?

ከገረሱ

የምንኖረው ሁሉ ነገር ከአገራችን ለየት በሚልበት ቦታ ነው። ሥልጣኔ ከፍተኛ ቦታ ደርሷል ከምንልበት ቦታ ነን ያለነው። የሰው ልጅ ከእንሰሳት ሁሉ ለየት የሚያደርገው አንዱ ባህሪው የሚያጋጥመውን አዲስ ሁኔታ አጢኖ ከዛ ጋር ሊግባባ መቻሉ ነው። እናም ገና እንደመጣን ቅጣምባሩ የሚጠፋን የሚመስለው ነገር ሁሉ እየተላመድነው ስንሄድ ቀላል ሆኖ ነው የምናገኘው። የማይለመድ ነገር የለም ልመድህ ካሉት ለማለት ነው። ብዙውን ነገር መላመድ ችለን ግን አልሆን የሚሉንን አንዳንድ ነገሮች ልጠቋቁም ወዳለሁ።

ቀጠሮ ማክበር፤- ለሥራ በሰዓት ሳንደርስ ስንቀር ምን እንደሚደርስብን እናውቃለን። ቀጠሮዋ ላይ ግን እምቢ ብላናለች አንዳንዶቻችንን። ለስብሰባ፣ ለጓደኛ ቀጠሮ በሰዓት አንደርስም። ምነዋ?

በዕቅድ መሥራት፤- አንዳንዶቻችን ይህ ችግር አለብን። ዕቅድ እናወጣለን፤ ዕቅዳችን የወረቀት ላይ ነብር ብቻ ሆኖ ነው የሚቀረው። ቀጥዬ ይህን እፈጽማለሁ ብለን ወስነን ጊዜው ሲመጣ ጭራሽ ስለሱ ረስተን አዲስ ዕቅድ ነደፋ እንገባለን። ምነው ምን ነካን ጃል?

የማይፈጸም ቃል መግባት፤- እስቲ ትዝ ይበላችሁ። ይህንን አደርግልሃለሁ ብላችሁ ለአንዱ ቃል ገብታችሁ ሳትፈጽሙት የቀራችሁት ነገር ካለ፤ ይሉኝታ ይይዘንና ወይ ለጉራ ብለን "ይህን እፈጽምልሃለሁ" ብለን ለአንዱ ከአቅማችንና ከችሎታችን በላይ ቃል እንገባና ሳንፈጽመው ቀርተን ሰውዬውን ስናየው መግቢያ ቀዳዳ የሚጠፋን ስንት ነን? ኸረ ጉድ ነው!

አለማወቅን መሸሸግ፤- የማናውቀውን ነገር "እናውቀውም" ብለን መናገር ራስን ዝቅ አድርጐ መውሰድ ነው በሚል አጉል እምነት በማናውቀው ገብተን ስንፈተፍት የሰው መሳቂያ የምንሆን የለንም? ኸረ ተው ታዛቢው ብዙ ነው።

በመጨረሻም እባካችሁ በትንሽ በትልቁ አትከፋ፣ አትበሳጩ። ያለነው እናት ጓዳ አይደለንም፤ ሁሉ የምናሚላው ራሳችን ነንና ለችግራችን መፍትሔ ሊሰጠን የሚችለውን አዕምሮአችንን ጉድተን ሰውነታችንን ያለጊዜው አናገርጅፈው።

ሥዕሉን እዩት።
ሁሌ ፈገግታ
አይለያችሁ
እንደ ሰውየው።
አለበለዚያ

።ብቋኑ ሄገ.ፉ
ብቋሃዝጊ ህኃ



# ModEth
# Ethiopian Word Processor

ለማንኛውም የኅትመት ሥራ - ሞዴት ! ModEth's (የሞዴት) patent pending technology is probably the best thing that happened to the ancient Ethiopic alphabet since Gothenberg's invention of the printing press. Join the leader who pioneered a perfect and simple *Ge'ez* (በግዕዝና ሌሎችም) word **publisher** (የኢትዮጵያ ቃላት ማተሚያ), and enjoy the beauty and clarity of each and every *Amharic* (አማርኛ), *Gurage* (ጉራጌ), *Oromo* (ኦሮሞ) and *Tigre* (ትግሬ) characters (ፊደላት). Design your own PostScript fonts, use the mouse, make forms and calendars, edit up to ten files simultaneously, import PCX and TIFF graphics... just to mention some of our Ethiopic features for the IBM XT, PC, PS/2 and compatible computers. ♠

**የኢትዮጵያ ኮምፕዩተርችና ሶፍትዌር**
**Ethiopian Computers and Software**
**9781 W. Fremont Pl.,**
**Littleton, Colorado 80123**
**(303) 972-2186**





ይህ የቆየ የኢትዮጵያ የቋንቋና የጎሳ ካርታ በኤችፒ እስካነር (HP Scanner) ከወረቀት ላይ ከተቀዳ በኋላ በሞዴት (ModEth) ተነቦ እስክሪን ላይ ተጽፎበት እንደገና የታተመ (printout) ነው ። ♠


ለማንኛውም የኅትመት ሥራ - ሞዴት ! ModEth word publisher የኢትዮጵያ ቃላት ማተሚያ !

**የኢትዮጵያ ቃላት ማተሚያ**
**Ethiopian Word Processor**

ሞ ዴ ት ♠ ModEth




## ከ ታ ጋ ሹ  ሀ ሁ

### ኢትዮጵያ


ሌሎች ፊደላት ገስግሰው
ብዙ ሥራ ሲሠራባቸው
እንደለመደብን ስንጣላ
ከረምናት አይደል ስንጉላላ ?
ስንቱ ሀሁ ብሎ እንዳልተማረን
የወረቀት እነር እንዳልነበርን
ከማን እንጀዎች ተነስተውብን

ሲ ተ ጣ ጥ ሉ ን  ሲ ቀ ራ ር ጡ ን  ሲ ያ በ ላ ል ጡ ን
ሲ ያ ወ ር ዱ ን  ሲ ያ ን ጋ ድ ዱ ን  ሲ ደ ል ዙ ን
ሲ ሰ ታ ቅ ሉ ን  ሲ ያ ጣ ብ ቡ ን  ሲ ረ ሱ ን
ሲ ሰ ነ ጥ ቁ ን  ሲ መ ራ ር ጡ ን  ሲ ያ ተ ጣ ጥ ሉ ን
ሲ ያ ለ ያ ዩ ን  ሲ ያ ራ ር ቁ ን  ሲ ያ ጋ ጩ ን

የሌለብንን አላችሁ ብለው
ያልነበረንን ቀጣጥለው
የወደዷቸውን ከበው
ያልመሰሏቸውን አግልለው
ሲያቅታቸው እንደመተው ፤
እየተዶለተብን እንደፈዝ
ልንጠፋ ነበር የግዕዝ
ፊደላት ፤ ምልክቶችና አኀዝ ።
ቀን እስኪያልፍ ያለፋል እንደሚባለው
ስላልተሳካላቸው ሁሉም ሴራቸው
የማይሆን ሆኗል እንርሳው ።
ኮምፕዩተሩ እዳነን አበራልን
ዱሮስ እኛ መቼ ሊቃጣን ?
ሳናውቀውም ቢነጋብን ፤ እሻፈረን እትነካኩን
እንደቀድሞው እንዳማርን ፤ እንደተዋብን ተዋህደን
በዶሮ ላባ ከመቀረጽ ተሻሽለን
ወደ ማተሚያ ቤት እንደተጓዝን
ገና ከዋክብትን እንጎበኛለን ።
ማናችንም ሳንቀር ሳንጎዳ
ሳንበላለጥ ሳንረዳ
በእኩልነት ዓይታችሁን ፤ በትክክል ዐውቃችሁን
ሳትለያዩን ሳትከፋፍሉን ፤ ለዘላለም እንኖራለን !



# ልብ ወለድ



# ከስደተኛው ማህደር

ከዶቢሳው

ከአለፈው የቀጠለ፤

መቸም አይደረስ የለም ቤት እንበለውና ከቤታችን ስንደርስ ገርበብ ያለውን በር ከአጠገቤ ብር ብላ ጨንዩ በርግዳው ቀድማኝ ገባች። ብስጭቴ ብዙ ነገር እንዳወጣ እንዳወርድ አድርጎኝ ኖሮ እስከ መኖሯም ረስቼአት ነበር ብል ስህተት አይመስለኝም።

ከቤቱ ጥግ ለውሃ ማቀዝቀዣ ከተቀመጠችው ዚር አንድ ኩዞ ውሃ ጠጥቼ የተቃጠለውን ቆሽቴን አቀዘቀዝኩ። ወደ ቤት ስገባም ጨንዩ ከምስኪን እናቴ አንገት ላይ ተጠምጥማ ስታለቅስ አየሁአት። ያለዕድሜዋ መንገላተትዋ በየሰበቡ እንድታለቅስ አድርጓታል እንጂ መንገድላይ ስለገጠመን ጉዳይ ዐረብኛ ገብቷት የተረዳችው ነገር ያለ አልመሰለኝም። እናቴም ብትሆን የኔን ሆድ የባሰ ላለማባባት ካልሆነ በቀር ዕንባዋ በዕይኗ ሽፋን ላይ ተንጠለጠሎ ሲተናነቃትና ታግላ ስትመልሰው በግልጽ ያስታውቅ ነበር። ሆኖም ሆደባሻነት አሸንፏት ደራሽ እንባዋ ግድቡን ፈንቅሎ ፈሰሰ። ለማጽናናትም ሆነ ዝም እንዲሉ ለመጠየቅ አልደፈርኩም። ውስጤን ሀፍረትና ባዶነት ተሰማኝ።

መልስ ላላገኘለት ነገር "ለምን ቤተሰቤን ለዚህ አበቃሁ" ብዬ ራሴን ጠየቅሁ። ይህን ላለማየት ወደ ደጅ ወጣሁና ከቤቱ ጥግ ትንሽ ጥላ የምታርፍባት ቦታ ፈልጌ ቁጭ አልኩ። ለጥቂት ደቂቃ ያህል መሬቱን ቆረቆርኩ፤ መፍትሔ ከአፈሩ ላይ የማገኝ ይመስል በጣቴ ወዲያ ወዲህ እያንገዋለልኩ አሰላሁት። ሰይጣናዊ ምስሎችና መጥፎ መንፈሶችን ያመላልስብኝ ጀመር።

"እስከ መቼ ድረስ እንደዚህ ትዘልቃለህ?"

"በአንተ ምክንያት እኮ ነው እንዲህ የሚሰቃዩት፤"

"እናትህንስ ለምን ላገሯ መሬት አታበቃትም?"

ሀሳብ በሀሳብ ላይ፣ ጭንቀት በጭንቀት ላይ እየጨመረ ሄዶ ፍርሃት ዋጠኝ። ቅዠቱ አየል አደረገና "ሕይወትክን ብታጠፋ ከዚህ ሁሉ በተገላገልክ!" ሲለኝ ሰውነቴ በላብ መጠመቁ ተሰማኝ። እጆቼ ተንቀጠቀጡ፣ ዓይኔ ከተተከለበት ሳይነቀል ጣቶቼ በደመነፍስ ወዲህና ወዲያ እንገዋለው የከመሩትን የአሸዋ ክምር አፈጥበት ጀመር። ሕይወትስ ለማጥፋት ወኔ ይሻ የለ? እንደወትሮዬ ሁሉ የሞት ነገር ሳስብ ፍርሃቴ አየል አደረገና በአገሬ ውስጥ ተሰቃይተው የተገደሉትን፤ በእስር ቤት የዕድሜአቸውን ሲሶ የጨረሱትን፣ በግርፋትና በስቃይ አካለ ጐዶሎ ሆነው ለዘመድ አዝማድ ሸክም የሆኑትን ጓደኞቼን አስታወስኩና መለስ አልኩ። "ራሴን ባጠፋስ! እማዬ አለኔ ማን አላት? ጨንዩስ?"

ጨንዩ መጥታ ትከሻዬን ያዝ ስታደርገው ነው ከቁም ቅዠቴ የባነንኩት። ቀና ብዬ በለቅሶ የደፈረሱ ዓይኖቿንና ቲማቲም የመሰለውን አፍንጫዋን ስመለከት መልሶ የአጥፊነትና የተጠያቂነት ስሜት ተሰማኝ።

"ምነው ምን ፈለግሽ?" አልኳት፤ ቁጣም፣ ጥያቄም ይመስላል አባባሌ።

"እማዬ ጥሪው ብላኝ ነው።" ቀደም ብሎ መንገድ ላይ አትያዢኝ ያልኳት ትዝ ብሏት ነው መሰለኝ፤ ቆጣ ማለቴን አይታ ትከሻዬን ያዝ ያደረገችውን እሯን ሰብሰብ አደረገች በፍርሃት።

እናቴ ጨንዩ ስታለቅስ የልሯን እንባ በማየቷ ያለቀሰችበትን ምክንያት ሳታውቅ ነበርና አብራ ያለቀሰችው አልቅሰው አልቅሰው ሲወጣላቸው ጨንዩኔ ብትጠይቃት ምንም ልታስረዳ ባለመቻሏ የሆነውን ከኔ ለመረዳት ነበር ያስጠራችኝ። የሆነውን ዝግ ብዬ አስረዳኋት።

"አይ ልጄ ለዚህ ነው እንዴ፤ ይኼማ ምን ያበሳጫል፤ በሰው አገር ከዚህም የከፋ ያገጥም የለ?"

ትንሽ ተከዝ አለችና፤

"እነሱ እንደው ጠምደውናል። በቀደም እሁድ ለታ ከመድሃንያለም በተስኪያን ስመጣ እመንገድ ላይ ሁለት ማሙሽን የሚያካክሉ ናቸው እኮ ጠጠር ወረወሩብኝና 'ሀበሺ! ሀበሺ!' አይሉኝም መሰለህ፤ ታዲያ አልከፉኝ፤ ቻልኩት። ታዲያ ለዚህ ነው እንዲህ የምትሆኑት?"

ስትለኝ ደካማነቴ ተሰማኝ። የእናቴ ሞራል ፈርጠም ማለቱ እኔንም ገፋፋኝና ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሁኔታዎችን እንዳመዛዝን አደረገኝ።

እያደገ የመጣው ሱዳኖች በኛ ላይ የሚያሳዩት ጥላቻ ሁሉ ፈቴ ድቅን አለ። እኔ በመጣሁበት ሰሞን እንዲህ እንዳሁኑ መቼ ይከፉብንና፤ ያኔ የዋህና ደግ ለተራበ ለተጠማ አዛኝ ነበሩ። ለጋስነታቸው ለጉድ ነበር። ያኔ ገና እንደመጣሁ መውጫ መግቢያውን ሳላውቀው፣ ሥራ የሚባልም ሳልጀምር በተለይ ከአዲስ

አበባ የምንመጣው ጮሌ ነን ባዮች መተዳደሪያችን ከነሱ በምናገኘው ገንዘብ ነበር። ዓይን አፋር የሆነውና የሰው ዓይን የሚያሸማቅቀው፤ "ብሞትም አልሠራት" የሚለው ዓይን የበላው ደግሞ ሞቅ ያለ ደመወዝ በወር ሳይሆን በቀን ይዞ የሚገባበት "ጥፍጠፋ" የሚሉዋት ሥራ ናት። ካርቱም ከተማ መንገድ ላይ ጥሩ ልብስ ለብሶ ሳምሶናይት ሻንጣ በእጁ ይዞ ከመኪና ወርዶ በእግሩ የሚጓዘውን ቢሮ ከመግባቱ በፊት ከተል ይባልና "Sir" ተብሎ ዞር ሲል በግራ እጅ ሆድ፣ በቀኝ እጅ ደግሞ ራስን እያሻሹ "I am a refugee" ማለት፤ ቀጠል አድርጐም "I was a pilot in my country, but now I am hungry"( አገሬ ፓይለት ነበርኩ፣ አሁን ግን ርቦኛል) ተብሎ ሲለመን ከአለባበሳችን ጋር በማይሄደው ልመና በሀዘን ተገርሞ (ቢስሚላሂ ረሂማን ኢረሂም" ብሎ ቦርሳውን አውጥቶ ሁለትም ሆነ ሶስት ብር ሲሰጥ ተቀብሎ ወዲያው የሚቀጥለውን ባለተራ ጠብቆ መያዝ ነው።

ታዲያ አንዳንዴ ትላንት ፓይለት ነበርኩ ተብሎ የተጠየቀው ነገ በአጋጣሚ ተገኝቶ "አገሬ እያለሁ መካኒክ ነበርኩ" ተብሎ ሲጀመር ጆሮውን ይይዝና እንዳላየ አልፎ ይሄዳል። ሆኖም የሱዳንን ዕድሜ ያርዝመው እየተባለ ቀረጥ ያልተከፈለበት መቶና ሁለት መቶ ብር መቁጠር የተለመደ ነበር። በረመዳን ጾም ጊዜም በማፍጠሪያው (መግደፊያው) ሰዓት በመንገድ ላይ ስናልፍ "አሌክ አላህ ኢትፈደል" (በእግዚአብሔር ቅረብ) ብለው ያበሉን ነበር። ግን አሁን በስደተኛው ቁጥር መብዛት ፣ በጠፍጣፊውም መብዛትም ይሁን ወይንም አንዳንዱ እግዜር የረገመው እቤታቸው ተቀጥሮ ሲሠራ ኖሮ በመጨረሻ ዘርፎአቸው ከፋ ያለውም ሚስት ወይም ልጃቸውን ደፍሮ መጥፋቱ ለመከፋታቸው ምክንያት ሳይሆን አይቀርም አበሻ በዓይናችን አንይ ከማለታቸውም ሌላ ዕድል ሲያጋጥማቸውም በምክንያት ቀጥቅጠው ይጥሉታል። "በደረቅ አበሳ እርጥብ ይነዳል" እንዲሉ ሁሉም አበሻ ሌባ፤ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ችግረኛና የኢኮኖሚ ስደተኛ አድርገው ነበር የሚያዩት።

"እዚህ ስንት ዓመት ኖርክ?" ብለው ሲጠይቁ "ሶስት ወይም አራት" የሚል መልስ ሲያገኙ "ታዲያ የሚበቃህን ያህል አጠራቅመሀልና ለምን አገርህ አትመለስም?" ብለው የሚናገሩ ብዙ ናቸው። ቀልዶች ሁሉ በአበሻው ይፈጠር ጀመር። አንዱ ከጓደኛው ጋር ሲጫወት " ሰማህ አበሻ የሌለበት ዓለም የለም። ለንደን፣ አሜሪካን፣ ሳውዲ የትም የትም ብትሄድ አታጣቸውም። እንዲያውም አንድ ፓኬት ቤንሰን ሲጋራ ገዝተህ ብትከፍተው አስራ ስምንት ሲጋራና ሁለት አበሻ ታገኛለህ፤" አለውና ተሳሳቁ። " ለመሆኑ አገራችሁ ሰማይ አለ?" ብለው የጠየቁ እንዳሉ አንዱ አጫወተኝ። ቢጠሉን ቢጠሉን ወንዶቹን ይጥሉን እንጂ ሴቶቻችንን

እንዳንድ ነገር ይወዷቸው ነበር። ሕፃን ትሁን አሮጊት ግድ አይሰጣቸውም፤ ያው "ሀቢብቲ" ነው፤ ለፍቅር ሳይሆን ለጊዜያዊ ፍላጐት ማርኪያ።

ይሆንና ይህን የመሳሰሉት በሃሳቤ ሳመላልስ ቆይቼ "ተመስገን ነው እንጂ ከዚህ የባሰስ አለ አይደል?" በማለት ተጽናናሁ። ጨንዶም የቡና ሲኒውን አቀራርባ እጣኑን አጭሳ ለእናቴ ለቀቀችላት። እናቴ ብስጭቷ ዞር የሚልላት ከቤተሰብ፣ ከዘመድ አዝማድ የተቀላቀለች ተሚመስላት ቡናዋን አፍልታ እጣኗን አጭሳ "የኢትዮጵያ አምላክ፣ አንተ ታቃለህ፤ ልጆቼን ጠብቅልኝ" ብላ ስትለማምን ብቻ ነው። በተለይማ የእናት ቡና የሚያምራቸው ጓደኞቼ መጥተው ስንጫወት "ይኸ ሁሉ ጐረምሳ አገር የገባ ዕለት" ብላ በተስፋ ደስታ ፊቷ ሲፈካ ሳይ እኔም ደስ ይለኛል።

ቡናውን በመጠጣት ላይ እንዳለን በራችን ተንኳኳ። ከጓደኞቼ አንዱ ይሆናል ብዬ ጨንዶን በሩን ክፈቺው አልኳት።

"ሰላም ወአለይኩም፤" አለ ሰምቼው የማላውቀው ወፍራም ድምጽ።

ወተት የመሰለ ጀለቢያውን ለብሷ፣ በጭንቅላቱ ታቦት የሚያስመስለውን ኢማ የሚሉትን ጥምጥም የጠመጠመና ጥቁር መነጽር ያደረገ ረዘም ያለ ሱዳናዊ ገባ። እኔም እናቴም ብድግ አልን፣ እንግዳ ሲገባ ልንቀበል። መጀመሪያ እናቴን ቀጥሎም እኔን ጨበጠን።

ጨንዶ ተቀምጣበት ከነበረው በርጩማ ላይ እኛ ሳንለው ራሱ ተቀመጠ። ከሰውነቱ የሚተነው ሽቶ ገላውን ታጥቦበት እንደሁ እንጂ ተቀብቶት ነው የሚያሰኝ አልነበረም።

በአገሩ ባህል መሠረት እንግዳ ቤት ሲገባ ውሃ ቀድቶ መስጠት የተለመደ ነበርና እንደወትሮዬ ጨንዶን ሳላዝ ራሴ ብድግ ብዬ ሰጠሁት። ጨንዶንም ወደ ጓዳ እንድትገባ በራሴ ቋንቋ ነገርኳት። በክት ልብሱ ተደግሶ እመጣጡ አላምር አለኝና። የኔም የእናቴም ከሁሉም በላይ የእሱ ዓይን ከፈገግታ ጋራ ጨንዶን ወደ ጓዳ በመከተል ሸኘን። በሆዴ "አይ ምስኪን" አልኩኝ የጨንዶ አካሄድ ሆዴን ቡጭ ቡጭ አድርጐት።

ለጨዋታ ራሴን ለማመቻቸት አንዱን በርጩማ ይዤ ከፊትለፊቱ ሂጄ ስቀመጥና እሱም መነጽሩን ሲያወጣ ቅድም መንገድ ላይ ከእህቴ ጋር ተቃቅፎ በመሄዴ የቀናው ባለማርቼዲስ መሆኑን ተረዳሁ።

. . . በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል።

# እልከኛው

**ከአብነህ አሸግሬ**
**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**
**ቲያትር አርትስ ዲፖርትሜንት**

የማታ ፀሐይ ስንብቷን ልታስጠነቅቅ፣ የጠዋት ብቅታዋን በናፍቆት ልታስጠብቅ ከቀን ውበቷ ይልቅ በቀይ ቀለም ደምቃ ከባለወልድ በተስኪያን ጉልላት በስተጀርባ ትታያለች።

ከበተስኪያ ኑ በታች ባለችው ትንሽ ሜዳ ላይ በቀይና በነጭ ከናቴራ የተለያ ዩ የባለወልድና የጃልሜዳ ሠፈር ልጆች በጨርቅ ኳስ ግጥሚያ ጀምረዋል። አብዶ፣ መለጋት፣ መሣት፣ መርገጥ፣ ቴስታ፣ መገፋት፣ መውደቅ፣ ማልቀስ፣ መነሳት፣ ማኖ፣ ተመልካች በሌለበት ሜዳ ይከናወናል።

ከብርማ የሲጋራ ወረቀት የተሠራች ትንሽ ዋንጫ ከመጫወቻው ሜዳ ክልል በስተግራ ባለው ቋጥኝ ላይ ቁጢጥ ብላ አሸናፊዋን ትጠብቃለች።

ጉንጃቦ፣ የባለወልድ ሰፈር ካፒቴን፣ የመጀመሪያውን የጉል ሙከራ አድርጉ ኳሷን ለጥቂት ወደውጭ እንዳስወጣ ከሜዳው በታች የጥሪ ድምጽ ተሰማ። በ ጉን ዓይኑ ሰረቅ አድርጉ ወደ ቤቱ አየ። አንገቷን በመስኮት አውጥታ የምትጣራዋ ዓለሚቱ መሆኗን ተመለከተ። ወደ በተስኪያ ኑ ዞር «ምነው ባወልድ እናቴን ከምትገድልብኝ አክስቴን ብትገልልኝ ኖር፤» አለና ጨዋታውን ቀጠለ።

ኳስ በጃልሜዳ ቡድን የግብ ክልል ውስጥ ትርመሰመሰለች። ጉንጃቦ ለብቻው ያገኛትን ኳስ አስተካክሎ ወደ ግብ ሊመታ እግሩን አስተካከለ። ዓለሚቱ ሜዳውን አቋርጣ ጆሮውን እየጎተተች በታስወጣው ኖሮ ያቺ ምት ጎል ነበረች።

ጉንጃቦ ቤት እስኪደርስ ድረስ በልቡ ባለወልድን ብስት ነገር ለመነ። ዓለሚቱ ከሚኒስትሪ ፈተና እንድትወድቅ፣ እንዲገድለትና አሰድጉ ጉልበት እንዲሰጠው።

«ስትጠራ የማትሰማው ጆሮህ ላይ ተቀምጠህ ነው? በል እንትፍ! ይህች ምራቅ ሳትደርቅ ወንጂ ሱካር ገዝተህ እንድትመጣ፤» ብላ አሥር ሳንቲም በእጁ አንድ ኩርኩም በራሱ ሰጠችው።

እምባውን ዱብዱብ እያደረገ፣ ጉንጩንና ከንፈሩን በኩርፊያ እየነፋ፣ ሳንቲሙን በትንሽ መዳፉ ጨብጦ በተመልሶ መጫወት ጉጉት ኃይል እየተነዳ አፈተለከ። የታዘዘውንም ገዝቶ አስረከበ።

ዓለሚቱ እንደልማዷ የወንጂ ስኳሩን ከረጢት አገላብጣ መረመረች። የጎንጃቦ ትንሽ ልብ የሰባት ዓመት ዕድሜ ያለውን የደረቱን አጥንት ሰባብራ ለመውጣት ምቷን አፋፋመች። አክስቱ የልቡን ምት እንዳትሰማበት ደረቱን በሁለት ትናንሽ መዳፉ ጫን አድርጎ ያዘው።

«ከረጢቱን ማን በሳው?» አለች ዓለሚቱ ትላልቅ ዓይኖቿን አጉረጥርጣ።

«እኔ ምን አውቃለሁ? እንዲሁ ነው የገዛሁት።»

«የተበሳበትንስ አካባቢ ምን አረጠበው? እንደልማድህ ስትስብ ነው የመጣኸው፤ ልታታልለኝ ነው?»

«እንዴ እኔ የስኳር ሌባ ነኝ? ሌባ ከሆንኩ ለምን ላከሺኝ ታዲያ?»

ዓለሚቱ ከ ጉንጃብ ከንፈር ሥር አንዲት ስኳር አንስታ አሳየችው። ለለቅሶ መከማተር የጀመሩት ዓይኖች በድንጋጤ ፈጠጡ። በተሳጨው ራሱ ላይ ያረፈው ሁለት ኩርኩም ሳያስበው ወደ በሩ አስሮጠው።

«ወዴት ወዴት ሌቦ! ናና ቤቱን ጠርገህ ስትጨርስ ሄደህ ትጫወታለህ።»

ቆም ብሎ ለማልቀስ የፊቱን ጡንቻዎች አከመታተረ። የልጆች የደስታ ጩኸት ከሜዳው ሿ ብሎ አረጭ አለ። ጎል እንደ ገባ ገመተ። ልቡ በሩጫ ወደ ሜዳው አፈተለከች። የመጣ ይምጣ ብሎ በእግሩ ተከተላት፤ ግን ብዙም አልራቀ፣ ትላል ቅ እርምጃዎች ትናንሽ ቹን ውጠው አፈፍ!!

ዓለሚቱ የ ጉንጃበን ቁንጮ ይዛ በቀንዱ እንደሚሳብ ፍየል እየ ጐተተችው ወደ ቤት ወስዳ መጥረጊያ ሰጠችው።

ዓይ ኑንና አፍንጫውን በማሊያው እጅጌ እየጠረገ ቤቱን ማጽዳት ጀመረ። የልጆች የሜዳው ጩኸት ጨ ዋታውን በአዕምሮው እየሳለበት ፍጥነት ሰጠው። የቤቱን ጥራጊ አንድ ላይ ካሰባሰበ በኋላ ቁጢጥ ብሎ ከርታሱ ላይ መቆለል ሲጀምር ከ ቅርቡ ጩኸት ሰማ።

«ጠረጴዛው ስር ያለውንስ ለማን ተውከው?»

ከሩቅ ደግሞ የልጆች የደስታ ጩኸት ሿ! እረጭ! ቀና ብሎ ወገቧን ይዛ ቁልቁል የምታፈጥበትን ዓለሚቱን በእምባው መስታወት ውስጥ አያት።

«እንዴ ጠርጌው የለ?»

«እንጀራ ቢሆን ሳህን ላይ አንድ ነጥብ አታስቀርም ነበረ። ወለሉን በመጥረጊያ ማዳረስ ላይ ግን ወገብህን ይይዝሃል። በል አሁን ጥረገው።»

« ጉንጃበ ብድግ አለ። ትናንሽ ዓይኖቹን አፈጠጠ። ትናንሽ እጆቹን ጨበጠ። ከንፈሩን አሳበጠ።

«አልጠርግም።»

«ይህቺ በቂላ ከደረች አትቆረጠምም።»

«ዓለሚቱ ወደ ጉንጃበ ተራመደች። ጎንጃበ ተንደርድሮ እግሮቿ ላይ ተጠመጠመ። ተየህ ቀደም ሞክሮ ያልተሳካለትን ዳግም ሊሞክር። ወደላይ አንስቶ ሊያፈርጣት ሞከረ። ከበደችው። የዓለሚቱን ሳቅ ሲሰማ ይበልጥ ተናደደና በቷን ነከሰ። የዓለሚቱን ጡጫ ጀርባው ላይ ቀመሰ። በሆዱ ተዘረጋ።

«እሺ የኛ ጉረምሳ በል ተነስ አሁን፤»

ጉንጃበ እንደሞተ ሰው መሆኑን መረጠ። «ሞትኩ፣» ሲል ሞቱን አወጀና ባለፈው ፋሲካ ጎረቤታቸው እንደታረደው በግ ተንፈራገጠ።

«ሞትክ! ነፍስህን ይማረው። ይልቅስ ሳላቀምስህ ተነስ፤ ሌባ!!»

ተንፈራግጦ፣ ተንፈራግጦ ተዘረጋ። ዓለሚቱ ቂጡ ላይ ያሰረፈችበት የመጥረጊያ እንጨት ግን ነፍስ ዘርቶበት በእግሩ አስቆመው።

ከሜዳው የደስታ ጩኸት ሸ! ብሎ አረጭ! ጮኾ በማልቀስ ጉረቤት ደርሰ እንዲያለቅቀው ፈለገ። ጮኾ ማልቀስ ደግሞ ሌላ ኩርኩም እንደሚያመጣ ገመተ። ሲፈነዳ ከሚጋፋው የእልክ አየር ጋር እየታገለ መጥረጊያውን ተቀብሎ ጠረጴዛ ስር ገባ። አንገቱን ወደ መሬት አቀርቅሮ ዓይኑን በድብቅ ወደ ባለወልድ በተስኪያን እዙሮ ተሳለ።

«አከስቴን የገደልክልኝ እንደሆን የአምስት ሳንቲም እጣን አስገባልሃለሁ።»

በልቡ ያሰበውን ዓለሚቱ ሰምታበት እንደሆነ ለማጣራት ከጠረጴዛው ስር ሆኖ ቀና ብሎ አያት፣ በእንባ መስታወት ውስጥ።

«ምን ታየኛለህ? እልክ ከሆነ ገና ጓዳውንም አስጠርግሃለሁ።»

«ጓዳ!»

«አዎን!»

መጥረጊያውን ወረወረ። ከጠረጴዛው ሸልኮ ሩጫ። አፈፍ። ዓለሚቱ የ ጉንጃበን ሳይሆን የእልክ የብስጭት ጆሮ እየጎተተች ወደ መኝታ ክፍል አመሩ። ጎንጃበ አያቱን እልጋ ላይ ተኝታ እንዳያት « አኩዩ! አኩዩ! አስጥይኝ፤» ብሎ በመሮህ የሙጥኝ አለ።

«ምነው ዓለሚቱ ከልጅ ጋር እልህ መያያዝ ደግ ነው?» የለሰለሰ ድምጽ ከብርድልብስ ወስጥ ተሰማ።

«እንቺን እያገባሽም እማማ፣ አርፈሽ ተኚ። ዝም በል!» ቋ! ቋ! ቋ! ኩርኩሞች በተላጨ ራስ ቅል ላይ። «ዝም!»

«እጆቹን ከአልጋዋ እግር በሲባጎ አቆራኝታ ወደ መስታወቱ ተጠጋች። መልከት፤ አፍሮ ጸጉሯን ነካ ነካ፣ ቅንድቧን ለሽ ለሽ፣ ነጠላዋን አጠፍ ለበስ አድርጋ ጉንጃበን ከተቀመጠበት መሬት ጋር በግልምጫ አጣብቃ ፈትለከ።

የልጆች የደስታ ጩኸት ሿ! ብሎ አረጭ!

ጉንጃበ፣ ዓለሚቱ መራቋን እንደገመተ ሲባጎውን ለመበጠስ አልጋውን በአንድ እግሩ ረግጦ እጁን ወደደረቱ በኃይል ሳበ። ይበልጥ ግን ጠበቀ። የትናንሽ እጆቹ ደም ስሮች ተቆጡ። ሲባጎውን በጥርሱ ነከሰ። የተነቃነቀችው የፊት ጥርሱ ስላመመችው ሙከራውን ትቶ ሌላ ዘዴ

ሲፈልግ አከባቢውን በዓይኑ ቃኘ። ያኔ ነበር ልማደኛው የቅቤ ሌባ የመንደር ውሻ አንገቱን ገበ አድርጐ ምሳሱን አውጥቶ ሲያለከልክ ያየው።

«አትወጣም!» አለ ጉንጃበ በአፉ ልትወጣ የምትተናነቀውን ልቡን እበታዋ ለማቆየት በደመነፍስ ወደውጭ መተንፈሱን አቁሞ። ግን ፍጥጥ! ፍጥጥ!! ከቀፎዋቸው ወልቀው መሬት ዱብ ሊሉ ጥቂት የቀራቸው የጉንጃበ ዓይኖች በውሻው ሹል ጥርሶች ላይ አረፉ። ድው! ድው! ድው! የልብ ነጋሪት።

ጉንጃበ የጠበንጃ ጩኸት ለማሰማት ምላሱን ከላንቃው ጋር አጋጭቶ የተኩስ ድምጽ አሰማ። ፍጥጥ! ፍጥጥጥ!!

«እከ!» ብሎ ጮኸ ሳያስብ፤ ውሻው እንደ ጥይት ተተኩሶ ወጣ፣ ሳያስበው።

« ጉንጃበ፤» የደከመ ያያቱ ድምጽ ከብርድልብስ ውስጥ።

«እኩዩ! ውሻ በላኝ! ፍቺኝ ሊበላኝ ነው!»

የአያቱ እንባ በጎንና በጎን እየተንከባለለ ወደ አንዱ ጆሮ ወረደ።

«ምን ላድርግ ልጄ ሁለታችንም የአልጋ ቁራኞች። እኔ ያርጊት፣ አንተ የልጅ ያልጋ ቁራኛ፣ እንዴት እንፈታታ፤ የሁለታችን ጉሮሮ የዓለሚቱ ጉልበት ምርኩኛ፤ እንዴት እንፈታታ።» የለሰለሰ ድምጽ ከብርድ ልብስ ውስጥ።

« ሂፒፕ! ሁሬ! ሂፒፕ! ሁሬ!» ከሜዳው የነፈሰ ጩኸት የጎንጃበን ለቅሶ አስቆመው። ቀጠለና ዘፈን ተሰማ።

« አሸነፈው ባለወልድ አሸነፈው፣
 እሃሃ!
 አለቀሰ ጃልሜዳ አለቀሰ፤»

በዝምታ እምባዎቹን አስጎረፈው። ሲባጎውን ሊበጥስ ተፍጨረጨረ። ግን ይበልጥ ደም ስሩ ተወጠረ። እንደገና ተሰለ ለማርያም፤ ባለወልድ አልሰማ አሉ።

« ቅዱስ ማርያም ዓለሚቱን ከገደልሺልኝ የአስር ሰንቲም እጣን አስገባልሻለሁ።»

እየደራ እየቀረበ የነበረው ዘፈን ባንዴ አረጭ እንዳለ የሰፈሩ ልጆች በጃልሜዳዎቹ እየተባረሩ ወደ ጉንጃበ ቤት በሩጫ ገቡ። የጠጠር ዝናብ በጣራው ላይ ዘነበ።

ጉንጃበ ዋንጫዋን ኢሳሳ እጅ እንዳየ ማልቀስ ጀመረ። ዓለሚቱ ባትመቀኝበት ኖሮ በአምበልነቱ ዋንጫውን ከራሱ በላይ እያወዘወዘ የሚዘፍነው እሱ እንደነበረ ሲገምት።

ኢሳሳ ለቅሶ ሰምቶ ዘር አለ። በግጥሚያ ዕለት ለራሱ መጠበቂያ ከኪሱ በማትለየው የተሳለች በንዳ ሲባጎውን ቆረጠለት። ጉንጃበ እንባውን በማልያው እጅጌ ጠረገና የመጣበትን ንፍጥ ወደውስጥ ምጎ ዋንጫውን ከኢሳሳ ነጥቆ ማቀንቀን ጀመረ። ጓደኞቹም ተቀበሉት።

«አሸነፈው በለወልድ አሸነፈው፤
አሃሃ!
አሸነፈው! ... »

እየዘፈ ኑ ከተጫ ዋቾች ወለጆች ሰማንያ ሳንቲም ከሰበሰ ቡ በኋላ ወዳጆ ፖስቴ ቤት ተዝናንተው ጨለምለም ሲል ወደየቤታቸው ተበታተ ኑ።

ጉንጆበ በራፍ ላይ እንደደረሰ የዓለሚቱ ጉዳይ ትዝ አለውና ልቡ ቱር! ቱር! ማለት ጀመረች። እንጆቱም በፍርሃት ተለወሰ። ውሻና ሰይጣን በጨለማው ክፍል ውስጥ መኖር አለመኖሩን ገልመጥ ገልመጥ እያለ ካረጋገጠ በኋላ ጓዳ ገብቶ ኩራዝ አብርቶ እያ ቱ መኝታ ክፍል ገባ። ከአልጋዋ ግርጌ ኩርምት ብሎ ተቀመጠ። ጥቂት ካሰበ በኋላ ለማርያም ተሳለ። « ቅዱስ ማርያም፣ አክስቴን የቅድሙን እንዳትረሳ፣ ወይንም አቤት እንዳትመጣ ካደረግሽልኝ የ15 ሳንቲም እጣን አስገባልሻለሁ።

ክው! ድንጋጤ አፉን አስከፈተው። ይህ ሁሉ ስለት ቢይዝለት ሳንቲም ከየት፤ የዓለሚቱ ሳጥን ክፍት መሆን ግን ነፍሱን መለስ አደረገለት።

ሳጥ ኑ አንድ ሃሳብ በአዕምሮው ጫረበት።

«እ ኩ፣ በቀደም አንዲት ልጅ ሰንደ ቅ ዓላማ ላይ ተገረፈች።» እፍንጫውን በሌባ ጣቱ እየ ኩረ ኩረ።

«ለምን ልጁ?»

«ገመድ ስትጫወት ሊተር ከደረቷ ሹራብ ወድቶ የጂምናስቲክ አስተማሪ ስላገኙት።»

«ለሹራ ቡ ቁልፍ ለማይጠነቀቅ መድኃ ኒቱ ነው። አንተም ስትዘል ከኮትህ የሚረግፈውን ቁልፍ አግኝተው ባቀመሱልኝ።» አሉ አ ኩ።

«እንዴ ቁልፍ እኮ አይደለም። ባለ ጌ ነገር ነው። በተለበደ መጽሐፍ ውስጥ ተደር ጉ የሚሰጥ። ዓለሚቱም የራሷን እዚህ ሳጥን ውስጥ ደብቃለች። ቆይ ላሳይሽ!»ከአልጋው ዱብ አለና ሳጥን ከፍቶ አንድ ፖስታ አወጣ። ወደበር ሄደ ገልመጥ ገልመጥ ካለ በኋላ ከአያ ቱ ፊት ላይ ብርድ ልብሱን ገለጥ አድር ጉ ፎቶግራፍ አውጥቶ ሰጣቸው።

«ኢብራ ሂም ነው አታውቂውም?»

ሳሪያን ኮትና ቁምጣ፣ ሸራ ጫማ ያደረገ፣ የቀኝ አውራ ጣቱን በቀበቶው ዘለበት ላይ አስደግፎ በሌላው እጁ አርቲፊሺያል አበባ ያቀፈ፣ ጣሪያ ጣሪያውን የሚያይ ጉረምሳ ሥዕል ትኩር ብለው አዩ።

«በል መልሰው፣ ከየት ደግሞ ትሞህብናለች።»

«ቆይ ላንብበው ሌተሩን። የልብ ሥዕልም አለበት።»
ማነበብ ይጀምራል።

«እስቲ በስማም ብዩ ልጀምር ሰላምታ፣
ለተቀመጥሺበት ላለሽበት ቦታ።
ጥርስሽ የሚመስለው የጊደር ወተት፣
ፀጉርሽ የሚመስለው የሐር ጉንጉን።»

«በል፣ በል ጉንጃበ የቧ አይደለም። የዓለሚቱ ጸጉር ደግሞ ከመቼ ወዲህ ነው የሐር ጉንጉን የሆነው?»

«ቆይ እንጂ እኮ ልጨርስልሽ፣

«የዚህ የደብዳቤ ከልደረሰ መልሱ፣
ጦርነት ይነሳል እንደ ልጅ ኢያሱ።»

እያቱ ደንገጥ አሉ።

«ልጁ ኃይለኛ ነው ልበል? በል በል ከመጣች ትጨርስናለች፣ እቡታው መልስ።»

ጉንጃበ እንደጠበቀው ሳይሆንለት ሲቀር ደብዳቤውን በጥንቃቄ መልሶ እልጋዋ ግርጌ ኩርምት ብሎ ማንበት ጀመረ።

ዓለሚቱ ዱብዱብ እያለች ገብታ የተመሰቃቀለ ጸጉሯን መስተዋቱ ጋ ከስተካከለች በኋላ ጉንጃበን ገልመጥመጥ አደረገችው።

«ማነው የፈታህ አንተ?»

ዝም፣

«አትናገርም!» እንድ ኩርኩም።

እያት ፊታቸውን ከግድግዳ በግድ መለሱ።
«ምንድነው የሙት ልጅ እንደ እባብ መቀጥቀጥ። እንዳንጣላ እንግዲህ ዓለሚቱ፤ መጀመሪያ ራስን ነው መቅጣት፤»

ጉንጃበ በእያቱና በግድግዳው መሐል ፈጥኖ ተቀመጠ።

«እኔ ደግሞ ጉድሽን ለእኮ ነግሬአታለሁ፤ ሌተርሽንም እንብቤላታለሁ።»

ድንግጥ፣ ትናንሽ ዓይኖች ብልጥጥ። ዓለሚቱ እጅ ላይ የነበረው የተለበደ መጽሐፍ ዱብ። የጎንጃበ ልብ በፍርሃትና በደስታ ድብልቅ ስሜት ድው! ድው!

አፍጣ አየችው፤ አፍጦ እያት።

«ለካ ንብ በጆሮዬ ላይ ሲጮህ የዋለው ይህን ሊያሰማኝ ነበር።» አለች ዓለሚቱ ደርቃ እንደቆመች፣ እንበ እየተናነቃት።

ለጥቂት ደቂቃ በዝምታ ከየችው በኋላ በነጠላዋ ዓይኗንና አፍንጫ ዋን እየጠረገች በዝግታ ወደ ጓዳ ገባች። ኩርኩም አብሯት ጓዳ ገባ። ጉንጀባ ጉል ሲያስገባ ከሚደሰተው ደስታ ይበልጥ ፈነደቀ። እራት ግን አልተበላም።

ጉረቤት ወደ ጓዳዋ ሄዶ አባብሏት እስከመጣት እስከ ሰስት ቀን ድረስ ጉንጀባ ሰባት ግጥሚያ አድርጉ እራት ጉል አስገባ።

ዓለሚቱ ከጓዳ ስትወጣ ግን ኩርኩም አብሯት ወጣ። ቷ!ቷ!ቷ!ቷ! የ ጉንጀባ ጭንቅላት ለአንድ ዓመት ቷ!ቷ! እከ አርፈው በሰልስቱ በሊስትሮ ነት ከቤት እስከወጣበት ዕለት። ከዚያ በኋላ ብዙ የኪስ ግጥሚያ፣ ብዙ የመከራ ግጥሚያ።

---

# በቀደም ዕለት በሕልሜ

ከዘላለም ሲሳይ

ለግርማ ዘገዬ "ወጣት በግዱ" ለሚለው መልስ ቢጤ

የልደት ቀኔን አላከብርም፣
ሻማ አብርቼ አላጉራም፣
ኬክ ቆርሼ አልዘከርም፣
ምኑስ ሊጉዳ፣ ምኑስ ሊጠቅም።

ለነገሩማ –
ከቤት ስለተወለድኩኝ፣
"በርዝ ሰርቲፊኬትም" የለኝ፣
ማዘጋጃ ቤትም አያውቀኝ፣
ከሕዝብ ቆጠራም አልገባሁኝ።

እናም –
ዕድሜዬን አላውቀውም፣
ላውቀውም አልፈልግም፣
እባካችሁ አትጠይቁኝ እናንተም። (2)

እኔማ ምን ቸገረኝ፣
ተፈጥሮ ናት የምትቀልበኝ፣
መሬት ናት የምትይዘኝ፣
ድንቁርናዬ ነው የማያኖረኝ፣
ሰው ነው የሚያሰኘኝ።
እናም –
ዕድሜዬን አላውቀውም፣
ላውቀውም አልፈልግም፣
እባካችሁ አትጠይቁኝ እናንተም። (2)

ም ና ል ባ ት ?
ለሞት ከሆነ ዕድሜን የምትፈሩት፣
ዝግጁ ነኝ ሁለተኛ ልሞት።
እኔ ሞትን አልፈራት፣
ገና ድሮ ጥንት፣
ዘጠኝ ወር ሟልቷት፣
የሕይወቴን ፓስፖርት
እትብቴን ስትቆር – ቧት!
የእንግዲህ ልጅ ብላችሁ ስትቀብሯት፣
ያኔ ነው ያሳረጉት፣
የእኔን ሕይወት ተዝካር ያወጣሁት፣
የናንተን መኖር የጀመርኩት።
እናም –
ዕድሜዬን አላውቀውም፣
ለማውቅም አልፈልግም፣
እባካችሁ አትጠይቁኝ እናንተም። (2)

ምናልባት ታውቅ እንደሆን፣
ጠይቋት ወላጅ እናቴን።
ከማሕፀኗ ስታስናብተኝ፣
ለማን አደራ – አደራ እንዳለችኝ።

* * *
*

# ዕድሜ ለቀሚሱ!

ከዘውዱ እሸቱ ተ.አረጋይ

ወደ በርጫ ድግስ ለመሄድ ተቻኩለን፣
ሐኒ በግራዬ እኔና ኤልሳ ሆነን፤
እሁድ በሰንበቱ ሳሚ ጋ ተጉዘን፣
ከታክሲያችን ወርደን ከደጃፉ ደርሰን፣
ገብተን አረፍ አልን ሾኬ ተሳስመን።
　　ቶማስና ሳሚ በደምብ አነጣጥፈው፣
　　ከፍራሹ መሐል በርጫውን ጉዝጉዘው፤
　　ይጠባበቁናል ጀለቢያ ለብሰው፤
　　　　ሙዚቃውን ለቀው።
ሐኒም ከቦርሳዋ የሸመለለችው፣
ኤልሳም ከብብቷ ያንጠለጠለችው፤
የዚያንለቱ በርጫ ዕውቅ ግጥሚያችን ነው።
　　የሙዚቃው ጩኸት የዕጣኑ ቡልቡልታ፣
　　የኮካው የፔፕሲው የሰንደሉ ሽታ፤
　　ቤቷን ሞቅ አርጓታል የጆሊው ጨዋታ።
ኤልሳ ከፍራሹ በቅጡ ተንጋላ፣
በቤቱ መርካቷን ለማሳወቅ ብላ፤
ታወዛውዛለች እግሯን አንጠልጥላ።
　　እኔ ያልገባኝ ጥቅሻ በሴቶቹ መሐል፣
　　የቶማስ ገርል ለካ ዘግይታበት ኖሯል፤
　　ትራሱን እያሸ በድካም ተከዟል፣
　　ወደ ዕጣኑ ጪስ ዓይኖቹን አቡዟል።
　　ደቂቃም አልቆየ በሩ ተንኳኳና፤
　　ሣርዬ ብቅ አለች በደምብ ተሽሞንሙና።
ፕስ!. . .ለባጊሽ፣
ከየት ተላከልሽ።
"ብራዘር ሲወጣ ፕሮሚስ ገብቶልኝ፣
　ከምዕራብ ጀርመን ሳምንት ከላከልኝ።
　ምኑም አይነሳ የቀረጡ ነገር፤
　እንደዚህ ከሆነ ምነው ባይልክ ቢቀር።"
　　ቶማስ . . .ተነፈሰ፣
　　የልቡ ደረሰ፤
　　ለፍቅረኛው መምጣት ሰንደሉን ለኮሰ።
ካዳሚ አሳላፊው ሁሉም ተደላድለው፤
እናኝከው ጀመር ቡና ጀባ ብለው።
የሙዚቃው ዓይነት እየተቀየረ፣
ጫቱ በጫቱ ላይ እየተደመረ፤
ያ የምንጠብቀው ምርቃና ሰመረ።
　　"ሳሚ!" አለች ሐኒ ትንሽ ዘና ብላ፤
　　ለማጉረስ ዘርግታ የጫቱን ዘለላ።
"አሁን አውቀህ አይደል ያንን መች አጣኸው፣
　ኤልሳ እኮ ነግራው ነው ወስዶ ያስቀጠረው፤
　ደግሞም ሰምቻለሁ ያንተ ጓደኛ ነው።
　ታዲያ ምናለበት ዴቪድ ያጉቴን
　　ልጅ አንተም ታውቀዋለህ፣
　አንዱ ሴክሽን ያርገው ለምን ታሾፋለህ?"
"አይ ሃኒ! ምነው ብትተይው እንዲያው ብትረሺው፤
　　መልሱ ምን እንደሆን አንቺም እያወቅሺው፤
　　ይልቅ ያቺን ሽንጣም አምጪና አጣብሺው።
　　ከዚያ በኋላ ነው የጥያቄው መልሱ፤
　　መቼ እሺ ይለኛል ሳይገኝ ምሡ?
　　ጸጉረ ረጂማም ልጅ ባይኑ ላይ ካረፈች፤
　　ጥያቄ የለውም ሙቶ ታገኛለች።"
"ማን". . . አለች ኤልሳ
ካወጣት በኋላ ችኮ ቢሆንባት፣
ማወቅ ያስፈልጋል ይህንን ምናልባት፤
በየሆቴሉ ዶርም ወስዶ ቢገትራት፣
ለምን ሥራው አይቀር ሩት ምን ቀረባት?"
　　"ይህች ደግሞ ጥፍራም!
　　 ሁልጊዜ ሲነግሯት ነገር አይገባትም።
　　 ምኑ ፋራ መስሎሽ ተጣብቆ ሚቀረው፤
　　 የሴት ቀሚስ እንደሁ ፈታዩ ሩሱ ነው።
ይህ መች ጠፋሽ ላንቺ ጥንትም ታውቂዋለሽ፣
ግራ ማጋባቱን እንደ ልማድ አርገሽ፤
　　 ሲነግሩሽ አትሰሚም ትነዛነዣለሽ።
ቶማስ ጣራ ቆጥሮ፣
በምርቃና በርሮ፤
በተስፋ ተውጦ በምኞቱ ሰክሮ።
አውሮፓ አሜሪካን ካናዳን ጨርሶ፤
ከወጣበት አገር መጣ ተመልሶ።
　　"የምን ንትርክ ነው ሁልጊዜ ደቡሮች፤
ጭቅጭቅ ልማድ ነው ለእናንተ ዓይነት ፍጡሮች።
　በጊዜ መጠቀም ወይ ካልሆነ መተው፤
እንዲህ ዓይነቱ ብህል የማን ኮቴሽን ነው።
ኢሮፕ! . . . ዋይ! . . . . ሐው???
　　 መጥቀስ ካስፈለገ ስለ ነጮች አገር፣
　　 ሬገንም ቢሆን የፊልም አክተር ነበር።
　　 ታዲያ ምን ያረጋል በትዝታ መብረር፤
　ወይ ተጣብሶ ማግኘት ወይ ነግዶ መክበር።
　ለዚህ ቀላል ጉዳይ የምን መጨነቅ ነው፤
　በደምብ ተጣብሳ ፎግራ ትንገረው።
　ለሴት መጋደሚያ እንጀቱ ሰፊ ነው፤
　ደውለሽ ንገሪያት ሊፍት ላይ ታግኘው።
　　 የፊቷ ፈገግታ ሐሞቱን ሲያሰክረው፣
　　 ትህትናው ብዙ ሥራው የጻድቅ ነው፤
　　 ቁም ነገሩ ይህ ነው የዴቪድ ቲዎሪው።
　የጫማው ቋቋቴ ክላሲካል ሆኖት፣
　ከሚሠራው ሥራ ቁጭ ብድግ አስብሎት፤
　የውበቷ ሞገስ ይልቀቀው አዙሮት።
　　 የአፈጣጠሯ ስልት ኩርኩሮ ካሳቀው፤
　　 ፍጻሜው ቅርብ ነው ከቤ ምን ቸገረው።
　　 ቀጠሮ አክባሪ ነች የዴቪድ መስዋዕት፣
　　 ዕድሜ ለቀሚሱ ዕድሜ ለነሂሩት።"

============

# ADDISU GEBEYA አዲሱ ገበያ

## 2202 18th St. N.W., Washington, DC 20009

## 202•986•6013/23

### አዲሱ ገበያ እናንተን በይበልጥ ለማገልገል ተጉዘው የማማያገኙትን ቅመማ ቅመም ያሉበት ቦታ ለመላክ አዲስ አገልግሎት ጀምሯል

| የስም ዝርዝር | መጠን | ዋጋ |
|---|---|---|
| 1. በርበሬ | 1/2 | 3.99 |
| 2. ምጥን ሽሮ | 1/2 | 3.50 |
| 3. የእጃ ዱቄት | 1/2 | 3.50 |
| 4. ሚጥሚጣ | 1/2 | 3.50 |
| 5. አዋዜ | 1/2 | 3.99 |
| 6. የቅቤ ማንጠሪያ | 1 | 13.99 |
| 7. ቡላ | 1/2 | 3.50 |
| 8. መከለሻ | 1 | 13.50 |
| 9. ክክ | 1 | 0.49 |
| 10. ባቄላ | 1 | 1.79 |
| 11. ምስር | 1 | 0.89 |
| 12. ቅንጭ | 1 | 0.39 |
| 13. ተልባ | 1 | 1.25 |



## ማስታወሻ

### የሚያስፈልግዎትን ለማግኘት አዲሱ ገበያ መደወልዎን አይርሱ

ዝርዝሩ ሰፊ ነው፡- የሚፈልጉት ቅመማ ቅመም ጌጣጌጥ ወይንም የባሕል ዕቃ ከሆነ አዲሱ ገበያ ደውለው ይረዱ። ቅቤ፣ ሽሮ፣ ቡና፣ አተር፣ ሽንብራ፣ ጥቁር አዝሙድ፣ ዕርድ፣ ጌሾ፣ ብቅል፣ ጦስኝ፣ ቁጢ፣ በሶብላ፣ ዕጣን፣ የባሕል ቀሚስ፣ ሹራብ፣ ስኒ፣ ረከቦት፣ ዘፈን በካሴት ወይንም ቪድዮ ቴፕና ብዙ ብዙ ባሕላዊ ዕቃዎች አሉን።

## በአዲሱ ገበያ ቅመማ ቅመም ባጀትዎን ያሟሉ

NAME____________________

ADDRESS____________________

CITY__________ STATE________ ZIP________ Tel. ( )________

Please Include $5.50 For Shipping And Make Your Check Or Money Order Payable To: Addisu Gebeya

# አዳምና ሔዋን





# እስቲ ምን ይላሉ ?

ቀደም ባሉት እትሞች ገልጸናል። ይህ "አዳምና ሔዋን " የተሰኘው አምድ ዋና ዓላማው በተቃራኒ ጾታ ግኙኝነቶች ሳቢያ የሚነሱ ነገሮችን ማወያየት ብሎም ማቀራረብን ነው። በዚህ በኩል ያለው ልምዳችን የተገነባው ምስጢር ጭራሽም ብልግና አድርጐ በመወሰድ ላይ ነው። ስለ ወሲባዊ ግኙኝነት ቁጭ ብሎ ለመወያየት ይቅርና በትምህርት ቤት ዓለም እንኳ አንዱ አንዷን ልጅ ወድዶ ቢጠይቅ ( ለመጠየቅ እንኳ ድፍረቱ የለም ደብዳቤ ቢጽፍ) "ወደድኩሽ" ብሎ መግለጽ እንደወንጀል ተቆጥሮ ተማሪ በተሰበሰበበት ይገረፍ የነበረበት ጊዜ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። እንግዲህ በዚህ ኋላቀር ልምድ ውስጥ አልፈን የመጣን በመሆናችን ስሜቱ አሁንም በውስጣችን አለና ስለ ፍቅር ስለወሲብ፤ ስለወንድና ሴት ግኙኝነት የምናደርጋቸው ጨዋታዎች ሁሉ በሹክሹክታና በሐሜት መልክ ነው። ይፋ ካወጣነው ማ "ምን ስድ ነው?" ልንባል ነው። ይህን ስል ደግሞ ጭራሹኑ መረን የለቀቀ አባባል መናገር አለብን ለማለት አይደለም። አስፈላጊ ናቸው ተብለው በሚወሰዱ ጉዳዮች ላይ መወያየት ብልግና አይደለም ለማለት ነው።

ይህን ለማለት ያነሳሳኝ ምክንያት ስላለኝ ነው። በአለፉት እትሞች ላይ ከየአቅጣጫው እንደተገለጸም ሆነ በየቦታው እንደሚወራው ወንዱ "ሚስት አጣሁ!" ሴቷም "ባል አጣሁ!" ይላሉ። እንደሚባለው ጠፍቶ ወይም ጠፍታ ይሆን ወይስ ያለመደፋፈሩ፣ ያለመግባባቱ ችግር ፈጥሮ ነው። እስቲ ችግሩን የሚያወያይ ሁኔታ ለመፍጠር መጠነኛ ግንዛቤ ልጨብጥ በማለት በቅርብ የማውቃቸውንም ሆነ የማላውቃቸውን በቃልና በስልክ እየደወልኩ አንድ አጠር ያለ ጥያቄ አቀረብኩላቸው። "ለማግባት ችግሩ ምንድነው? ሴቱም አለ ወንዱም አለ፤" የሚል ነው። ይህንኑ በመጠነኛ ጥናት (survey) ያገኘሁዋቸውን መልሶች (ከሴቱም ከወንዱም) ድግግሞሹን ትቼ እንዳለ "ሴቶች ምን ይላሉ?"፤ ና "ወንዶች ምን ይላሉ?" በሚሉ ሁለት ንዑስ ርዕሶች ስር ከዚህ በታች አስፍሬዋለሁ። ለመወያያ መድረክ ይከፍትልናል የሚል ግምት አለኝ።

## ሴቶች ምን ይላሉ ?

የኛ ወንዶች ትምክህተኞች ናቸው። "ሴት ለባሏ ተገዢ ናት" የሚል ኋላ ቀር አመለካከታቸው እዚህ እሠለጠነውም አገር መጥተው አይለያቸውም።

---

ለምን ሌላ ወንድ አነጋገርሽ ብለው የሚደባደቡ አሉ፤ ሴት ልጅን አምኖ ነጻነት መስጠት የሚባል ነገር ከኛ አገር ወንዶች አላየሁም።

---

"ከፈሪ ቆንጆ የጀግና ፉንጋ፣
አብሬው አድሬ ሲያወጋኝ ይንጋ።"

በራሱ የሚተማመንን ወንድ ልነጠፍለት? ግን አላጋጠመኝም።

---

ሴት ለመጠየቅ ቀርቶ ለማናገር ይፈራሉ፤ ወኔው ከድቷቸዋል ልበል? ሴቶች ብንፈልግ እንኳ እስክንጠየቅ መጠበቃችንን መረዳት የተሳናቸው ይመስላል። እየፈለግን የፈለግነው ሰው ሳይጠይቀን ሲቀር እርር ድብን ያደርገናል። "ደስ ትይኛለሽ" ብሎ መናገር እኮ ምንም አይደለም። compliment ነው። ከሆነ ይሆናል ካልሆነ አይሆንም፤ እምቢ የሚባሉ ይመስላቸዋል፤ ቢባሉም ያንን በጸጋ ለመቀበል የሚዘጋጁ አይመስሉም።

---

የኛ ወንዶች ሴት ልጅን ማክበር አይሆንላቸውም። መጀመሪያ እስኪያወጡ ድረስ ጠባያቸው ሌላ ነው። ትንሽ ሲቆዩ ጠባያቸው ይቀየራል። ማክበር ሲኖር መከባበር ይኖራል። ይህን ሐቅ ያጤኑት አይመስሉም።

---

መልክ ታጥቦ የሚበላ ይመስል ቆንጆ ካልሆነች ይላሉ። ከመልኳ ይልቅ ለቁምነገሯ ቦታ ስለማይሰጡት ቁምነገረኛ ሴቶች ቆመን ቀርተናል።

---

የኛ ወንዶች ስንፍና ያጠቃቸዋል። እንደአገሬው ሰው ሲጣጣሩ የሚታዩ ጥቂት ናቸው። እነሱም አግብተዋል። ቤት ገብተው ቲ ቪ ላይ ተለጥፎ መዋል፤ አለያም እየዞሩ መጠጣትን ትልቅ ሙያ ያደርጉታል።

---

መጠጥ! መጠጥ! በአብዛኛው መጠጥ ይወዳሉ። መጠጥ ሲጠጡ ብቻ ሴት መኖሯ የሚታያቸው ብዙ ናቸው። ካልጠጡ ድፍረት አግኝተው ሴት የማይጠይቁ ብዙ ናቸው።

---

ምን ወንድ አለና እዚህ? የከረመውም እዚሁ ስለመቆየቱ እያወራ ጉራ ከመንዛት በቀር ቁም ነገር አላየሁበትም። በቅርብ የመጣውም የዞረበት ነው።

---

የኛ ወንዶች በአብዛኛው ኮምፕሌክስ አለባቸው መሰለኝ ቢጠይቁ እሺ የሚባሉ ስለማይመስላቸው መቅለስለስ ያበዛሉ። እምቢ የተባሉ እንደሆነ ሌላ ሴት ያለች አይመስላቸውም። መሬት የተደፋባቸው ይመስል ሴቱን በአጠቃላይ መኮነን ይጀምራሉ።

---

(."ወንዶች ምን ይላሉ" ገጽ 29 ላይ ይቀጥላል።)

# ግልጽ ደብዳቤ

ከዞ.ተ. (ከL.A.)

ይድረስ ለወይዘሪት ምን ይሻላል፤

በሐምሌ ወር በወጣው "ላንዳፍታ" መጽሔት ላይ "እኔስ የሚሆነኝ ባል ጠፋ ብል?" በሚል ርዕስ ያሰፈርሺውን ቅሬታ ተመለከትኩት። ቅሬታሽ ቢገባኝም ኢትዮጵያውያን ወንዶች በሙሉ፣

"ምግብ መቀቀልም ሆነ የቤት ሥራ በሙሉ የሴቶች ሥራ ነው የሚል የዛገ እምነት አይለያቸውም። . .የT.V. ወዳጆች፣ . . የሶፋ ጠላቶች . ."

ብለሽ በአንድ ላይ መሸምለልሽ መልካም አልመሰለኝም። ኸረ ባዛኙቱ የእኔ እመቤት! "ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ" እንዳይሆን እየተስተዋለ እንጂ!! ምናልባት አደባበይ ወጥተን ባታይን ነው እንጂ አንዳንድ አንቺ የኮነንሻቸው ባህርያት ምን እንደሆኑ የማናውቅ አንጠፋም። ጊዜና አጋጣሚ እያጣን ባንታወቅም መኖራችን በቀላሉ የሚሰረዝ አይደለም።

እስኪ "የሚሆነኝ ባል ጠፋ" ብለሻልና አንቺ ከጠቀስሻቸው ጋር በማዛመድ የእኔንም ልግለጽልሽና ዕጣ ክፍላችን ከገጠመ "ሎጋው ሸቦ!" እናስብል።

የምግብ መቀቀሉንና የቤቱን ሥራ በሚመለከት አያያዜ ወንዶቹን ትተሽ አያሌ ሴቶችን የሚያስከነዳ፣ የሚያስቀና ነው። በአንድ በኩል ለቤተሰቤ አንድ ልጅ በመሆኔ ከእናቴ የተማርኩት ሙያ፣ በሌላ በኩል ለጤንነቴ በግድ ያስለመደኝ ነው። እንዲያው ካልሸስ አይቀር ሰው የሠራው ምግብ ብዙም አይጥመኝ። ልብሴንም ራሴው በቀዝቃዛ ውሃ አጥቤው ካልተኮስኩት ደስ ብሎኝ አልለብስም። በዚህ በኩል እንግዲህ የሚያሳስብሽ የለም። እንዲያውም "እይሄ!" የምትይ ከሆነ እንድታይው አስቀድሜ አንድ ድስት ዶሮ ከነ 12 ብልቷ ጥሎሽ አድርጌ እልካለሁ።

"የዛገ እምነት" ምነው ሞገደኛ ሞገደኛ ሰነፉን ብቻ ነው እንዴ ያየሽው? በእንዳንዶቻችን ዘንድ እኮ መዛጉን ትተሽ እምነቱም ራሱ አይታወቅ። በእኔ በኩል የሴት ሥራ የምለው ልጅ አርግዞ መውለድን ብቻ ነው። ከዚህ በመለስም ሆነ ባሻገር ያለው ሥራ በእኔ ዘንድ የፆታ ልዩነት የለውም።

የቴሌቪዥኑም ነገር ቢሆን የእኔ እመቤት አታስቢ። አዋጅ አለ ካላሉኝ በስተቀር አላየውም። ይጠናወተኛል። ለዚህም ጊዜውም ፍላጎቱም የለኝም። ባይገርምሽ ቴሌቪዥንም የለኝም። ለወሬ ጋዜጣ እነባለሁ። እሱንም ቢሆን የመጀመሪያውን ገጽ ብቻ።

ይኸውልሽ እንግዲህ ይህ ጉረምሳ አንቺ እንዳልሽው የT.V. ወዳጅ፣ የሶፋ ጠላት" ተብሎ ቢወገዝ ጡር ይሆናል። እንዲያው መጥፎ ዐመል ብለሽ ከገመትሽው እቤት ውስጥ የሚጉልተኝ ቢኖር መጽሐፍ ወረቀትና ብዕር ነው። ይህንንም ቢሆን በመውደድ የተነሳ ብቻ ሳይሆን ለሽልጦ መግቢያዬም የሚሆነኝ ስለሆነ ነው። ታዲያ ብራና ፋቂ ወይም መጽሐፍ ደጓሽ እንዳልመስልሽ!

እቱ፣ ይህ እንግዲህ ክብርትነትሽ በአንድነት ጠቅለሽ በብዕር ጦር የወጋሽውን የወንዶች ባህሪ ሌላ ገጽታ በትንሹ ለማሳየት ነበር። መቼም ይህን ብቻ ተናግሬ ሎሚ ብወረውርልሽ አትቀልቢልኝም። እስኪ እንግዲህ አንቺም እኔም መሸ በከንቱ እንዳንሆን ያኽ! እኔነቴን አንድ በይልኝ።

በዕድሜዬ ካንቺ ትንሽ ነጠቅ እላለሁ። ብዙ ሳይሆን በሶስት በጋና ክረምት። ሁለታችንም በቁም ነገር የዕድሜ ክልል ውስጥ ነውና ያለነው ደመናው ሳይዳምን፣ ገደሉ ሳይወረዛ ጉልቻ እናፋልግ።

ስለ ሥራሽ መንገርሽ ያስመሰግንሻል። እመኚኝ የሥራ ትልቅና ትንሽ የለውምና ሥራሽን አከብራለሁ። ዋናው ቁም ነገር ገቢ ማስገኘቱ ብቻ ነው። እኔ ከጉልበት ሌላ የሚሸጥ ሙያ አለኝ። እሱን እየቸበቸብኩና በግሌም ሠርቼ የማገባው የወር ምንዳዬ ለእኔም፣ እኔ ለማስብላቸውም በቂ ነው። በነገራችን ላይ ዋጋ ካገኘሁበት ጉልበቴንም ቢሆን እቸበችበዋለሁ። በአዕምሮና በጉልበት ሥራ መካከል ልዩነት የለም ብዬሻለሁና። ስላንቺ ከገለጥሺው ውስጥ እጅግ የሚያስመሰግንሽ መማርሽ ነው። አሜሪካ እያለ ያልተማረን ኢትዮጵያዊ፣ ወንድም ሆነ ሴት ነፍሴ አጥብቃ ትጠላለች። የእኛን ዕድል ሌሎች አያገኙትምና። ስለዚህ ተምሬአለሁ ብልሽ እንደ ትንግርት የምታይው አይሆንም። እንዲያው ተምሬአለሁ የሚል ሰው በቀላሉ አፍንጫውን አይፎንንብኝም ብልሽ ይበቃል። አንቺም ልጆችንም የምትኮሩብኝ እንጂ የምታፍሩብኝ አትሆኑም።

መልክሽ ጠይም መሆኑ በግጥምም በቅኔም ለማወደስ የተመቸ ነው። በእኔ አመለካከት መልክ ለጋብቻ መለኪያ አይደለም። መልክ የሌለው ሁሉ መልከኛ በሚሆንበት ዘመን መልክ ምን ዋጋ አለው? ጠይም መሆንሽ ደግ ነገር፤ አንድ ደብተራ ቀይ ሴት በዞረችበት እንዳትደርስ ስላለኝ ገዴ ከጠያይሞቹ ነው።

ስለኔ መልክና ቁመና ለመናገር በጣም ያስቸግራል። ለክቼው አላውቅም። እንዲያው ስገምተው ግን በጠጣና በመልዐክ መካከል ነኝ። ለሁሉም እስኪ ሰኑን መልክ

መለኪያ ቦታ ካለ ፈልጌ ውጤቱን አስታውቅሻለሁ። ከቁመቱ መዘዝ ከስባቱ መጠጥ ያልኩ ነኝ።

ወ/ት ምን ይሻላል፤

እስካሁን በጻፍኩት ሳትፈርጂብኝ ወይም ሳትፈርጂልኝ ከማገባት ሴት የምፈልገውን ደግሞ ልንገርሽ። እነዚህም ባህርይና አመለካከት ናቸው። ሚስት ልትሆነኝ የምትችል ሴት በባህርይዋ ትዕግሥተኛ፣ ሐቀኛ፣ ርህሩ ፣ አስተዋይ፣ መልካም የምትመኝ፤ ተስፋ የማትቆርጥ መሆን አለባት።

በአመለካከቷ ደግሞ ትላንትን አስታውሳና ነገን አስባ ዛሬን በጥንቃቄ የምትይዝ መሆን አለባት። የራሿን ሀሳብ ከመግለጥ ወደኋላ የማትል፣ የሰው ሀሳብ፣ እምነትና አመለካከት የማታንቋሽሽ፣ በራሷ የምትተማመን ግን ለብቻዋ ከ ብረተሰብ ተለይታ እንደማትኖር የምታውቅ፣ በጠቅላላው አካቢቢዋን መስላ መኖር የምትችል ሆኖም ግን ክብሯን በማንም በምንም የማታስደፍር፤

ከነዚህ ሌላ የምጠይቀው ቢኖር ልጅ ለመውለድ ፈቃደኛ መሆንን ነው። የመጨረሻው ዘር መሆንን ስለማልወድ ቢያንስ አንድ ልጅ እፈልጋለሁ። የማገባት ልጅ በተፈጥሮ ምክንያት የማትወልድ ከሆነ (መሆን ከሆነች) ግድየለም። "እርግዝና አልወልድም" ካለች ቁርበቷን አስይዤ ወደ ቤተሰቦቿ እመልሳለሁ። እንዴ መቼም መናገር ደግ ነው። አንቺም አፍላ ዕድሜሽ ላይ ነሽና ጊዜ አለን ብዬ እገምታለሁ።

ሌላው መቼም እንግዲህ ላገባት የምፈልገው ሴት ፍሬ ባለው ነገር ላይ ሀሳብ ላካፍላት፤ ምክር ልጠይቃት፤ ላነጋግራት የምችል መሆን አለባት። ኢትዮጵያዊት "ቢምቦ" ካልሰከርኩ በቀር ለዓይኔም ለጆሮዬም አትስማማኝም።

ይኸው እንግዲህ እቱ! በወንዱ ላይ በጥምሉ ኩነኔ ከምታወርጂበት "ባል ጠፋም" ብለሽ ከምትጨነቂ ነገሬን አንድ በይውና ሁለታችንም መሸ በከንቱዎች ሳንሆን ሀይ ሎጋ እናስብል። ሀይ ሎጋ ማሰኘት ካሁኑ ነው። ወደ ኋላ ከመሸ በኋላ ሀይ ሎጋ ቢያሰኙም "ሎጋ ለሎጋ ሲዋጋ ነጋ" ብሎ ለማቅራራት ያስቸግራል!

ፈረሴን ጭኜ፣ ሽማግሌ ይዤ አትላንታ ቆላ ልምጣ እንዴ? "አይ!አይጥመኝም" ካልሽም ምናለ ባዞኝቷ ይሁንብሽና አርፈን በተቀመጥንበት በጅምላ አታውግዥን፣ ኸረ እባክሽ። "ባል ጠፋ" ስትይ የጠላትም ጆሮ አይስማ።

መልካም ዓመት ይሁንልሽ።

. . . ከገጽ 27 የዞረ

## ወንዶች ምን ይላሉ?

የኛ ሴቶች ልባቸው እየፈለገ ሲሽኮረመሙ ያናድዳል። እዚህ እስለጠነው አገር መጥተው እንኳ አይማሩም። መግደርደር። ቆየት ያሉት ደግሞ ከአገሬው የተማሩትን game በተግባር ለማዋል ሲሞክሩ አያምርባቸውም?

---

ማነው እሱ ሳይሆን ምን አለው ማለት ይቀናቸዋል። ሀብት ላይ ነው የሚያተኩሩት። ሀብቱ ያለቀ ዕለት ፍቅራቸውም አብሮ ያልቃል።

---

ከፍቅራቸው ቅናታቸው ያይላል። የገዛ እህትህን እንኳ ስታናግር የሚቀኑ አሉ።

---

የኛ ሴቶች confused (የዞረባቸው እንዳልል ስድብ ይሆናል) ናቸው። በራሳቸው አይተማመኑም። ሁሌ የበለጠ የማግኘት ስሜት ስለሚጠናወታቸው ዘላቂ ግኙኝነት በማበጀቱ በኩል ድክመት አለባቸው።

---

"ይወደኛል ወይ? ያስብልኛል ወይ? ያከብረኛል ወይ? ብሎ ከማሰብ "ምን ያደርግልኛል? ምን ይገዛልኛል?" ማለትን ያዘወትራሉ።

---

ትምህርታቸውን ለማሻሻል የሚጥሩ ብዙ ሴቶች አላየሁም። በትምህርት ራስን አበልጽጉ የአስተሳሰብን አድማስ ለማስፋት ከማሰብ ይልቅ ተሽቀርቅሮና ተቆነጃጅቶ ሀብታም ባል መፈለግን ቁም ነገር ያደርጉታል።

---


ቅርብ የመጡት ጥራዝ ነጠቅነት ያበዛሉ። "ፉራ" የሚሏት ቋንቋ አለቻቸው። fresh ነን በማለት እንደ አቅሚቲ ሰው ይንቃሉ። የከረሙት ሲያማርጡ ከርመው ገርጅፈው ቆመው ቀርተዋል። ታዲያ ማንን ላግባ?

---

ሐሜት ያጠቃቸዋል። ምሥጢረኞች ስለሆኑ ልባቸው አይገኝም።

---

ውድ አንባብያን፤- ከሁለቱም ጾታዎች የቀረቡት እንዳለ ነው። ሌሎችም በብዛት ስላሉ በሚቀጥለው እትም እናወጣዋለን። እስቲ የሚሰማችሁን እናንተም ላኩልንና እንወያይበት።




## ጓደኛ ለሚፈልጉ

ጓደኛ ፈላጊዎች ራሳቸውን አስተዋውቀው፣ ሊተዋወቁ የሚፈልጉትን ሰው ዓይነት የሚጠቁሙበት አምድ ነው። ስምና አድራሻ በይፋ በመጽሔቱ ላይ አይወጣም። በስምና በአድራሻ ምትክ የኮድ ቁጥር ይወጣል። ስምና አድራሻ እኛ ጋ ይቆያል። ትክክለኛ ስምና አድራሻ ለኛ መላክ አለበት፤ ምሳሌውን ከታች ይመልከቱ፤

ምሳሌ፤-

*********************************************************************

ስምና - 1111፤ ከተማ - ቺካጐ፤ ዕድሜ - 34፤ ወንድ፤ ትምህርት - መጀመሪያ ዲግሪ፤ ሥራ -ካሸር፤ ቁመት - አጭር፤ ሙዚቃና ሲኒማ ወድዳለሁ፤ አላጨስም፤ አንዳንዴ ጠጣለሁ፤ ልጅ የለኝም ግን ወዳለሁ፤ ተጫዋች፤ የምፈልጋት ፤- አስተዋይ፤ የማታጨስ የማትጠጣ፣ አስተማማኝ ሥራ ያላት፤ ልጅ የሌላት፣ ለዘላቂ ጓደኝነት፣ (በአድራሻ ቁጥር 1111 በ"ላንዳፍታ"በኩል ጻፈልኝ)

*********************************************************************

እኛም ስምና አድራሻ ትተን የኮድ ቁጥር በመስጠት እናወጣዋለን። ከላይ የተጠቀሰውን 1111ን መተዋወቅ የምትፈልግ ደብዳቤ ለ1111 ብላ ገልጻ ትጽፍና በፖስታ አሽጋ ፖስታው ላይ የራሷን አድራሻ ብቻ በመጻፍ የተቀባይ አድራሻ ቦታ ሳትሞላ ይህን የታሸገውን ፖስታ የፖስታ ቴምብር በመለጠፍ በሌላ ፖስታ ውስጥ በመክተት ትልክልናለች። እኛም የኛን ፖስታ በመክፈት ከውስጥ ያለውን ፖስታ አውጥተን የ1111ን ትክክለኛ ስምና አድራሻ በመሙላት ለባለቤቱ እንልካለን። ከዚያ በኋላ እንግዲህ እንደ ፍጥርጥራችሁ። ምሳሌው የወንድ ይሁን እንጂ ለሴቶችም ተመሳሳይ ነው። አድራሻችን

LANDAFTA
P.O.Box 409358
Chicago, IL 60640 ነው።

====================================================================

### ከዚህ የሚቀጥሉት በትክክል የጻፉልን መልስ ተጠባባቂዎች ናቸው።

*********************************************************************

ስም - 1001፤ ወንድ፤ አድራሻ - ኒውዮርክ፤ ዕድሜ - 29፤ የአለፉት ዘመናትን ስነጽሑፍ ወዳለሁ። ዝናባማና ቀዝቃዛ ቀናትን እመርጣለሁ። ተመሳሳይ ስሜት ያላት ከ30 ዓመት በላይ የሆነች ጓደኛ መተዋወቅ እፈልጋለሁ።(በአድራሻ ቁጥር 1001 በ"ላንዳፍታ"በኩል ጻፈልኝ)

*********************************************************************

ስም - 1002፤ ወንድ፤ ዕድሜ 41፤ 2ኛ ዲግሪና አስተማማኝ ሥራ ያለኝ፤ ስነጽሑፍ፣ ሙዚቃና ትያትር እወዳለሁ። እጨሳለሁ ለማቆም በመጣጣር ላይ ነኝ። መጠጥ አልወድም። ተጫዋችና ግልጽ ነኝ። አገሬን እወዳለሁ። አገሯን የምትወድ፣ ሠርታ የምታሠራ ታታሪ፤ ተጫዋችና ተግባቢ ግልጽ የሆነች ጓደኛ እፈልጋለሁ። ለመልክ ብዙም ግድ የለኝ ስትስቅ ደስ ካለችኝ።(በአድራሻ ቁጥር 1002 በ"ላንዳፍታ"በኩል ጻፈልኝ)

*********************************************************************

ስም - 1003፤ ወንድ፤ ዕድሜ 22፤ አድራሻ ሆላንድ፤ ሥራ ተማሪ ዲፕሎም ኮርስ በመከታተል ላይ፤ ሙዚቃ፣ እግር ኳስ፣ ቲያትርና ማንበብ እወዳለሁ። የኔን ሃሳብ የምታሟላ ዕድሜዋ ከ20 እስከ 30፣ ልጅ የሌላት ለዘላቂ ጓደኝነት የምታስብ ጓደኛ መተዋወቅ እፈልጋለሁ። (በአድራሻ ቁጥር 1003 በ"ላንዳፍታ"በኩል ጻፈልኝ)

*********************************************************************

ስም - 1004፤ አድራሻ አዲስ አበባ (ኢትዮጵያ)፤ ወንድ፤ አጭር መልከ ቀና፤ ዕድሜ 41፤ 2ኛ ዲግሪ አለኝ፤ሥራዬን የምወድ፤ ታማኝና ትዕግስተኛ፤ ቤትና መኪና የለኝም፤ ቤት ማስተዳደር አይሆንልኝም፤ ሰው አፈቅራለሁ፤ ዘመድ መጠያየቅ አይሆንልኝም፤ እጨሳለሁ፤ አልፎ አልፎ እቀማምሳለሁ፤ በትርፍ ጊዜዬ ከራር መጫወት፣ መጻፍና ማንበብ እዘወትራለሁ። የምፈልጋት የቤት ጓደኛ አገሯ መመለስ የምትፈልግ፤ ዕድሜዋ ከ29 በላይ፣ የተማረች፣ ሥራ የማግኘት ችሎታ ያላት፤ ቤቷን አፍቃሪ፤ ፍጹም ታማኝ፤ ቆንጆ የማትባል የደም ገምቦ የሆነች። (በአድራሻ ቁጥር 1004 በ"ላንዳፍታ"በኩል ጻፈልኝ)

*********************************************************************

# እሱና እሷ

(የመጀመሪያ ቀናቸው ነው። አንድ ፓርቲ ላይ ነው የተገናኙት፣ ለዳንስ ይጋብዛታል።)

እሱ፣ – እንጫወት
እሷ፣ – ደክሞኛል ባክህ
እሱ፣ – ባክሽ ምንም አይልሽ
እሷ፣ – አቦ በፈጠረህ
እሱ፣ – ኧረ ባክሽ
እሷ፣ – (በሆዷ) የምን መድረቅ ነው
(ትነሳለታለች)
እሱ፣ – (ዳንሱ መድረክ ላይ እየደነሱ)
ጥሩ ዘፈን እኮ ነው።
እሷ፣ – ይሆናል
እሱ፣ – እንዴት ይሆናል
እሷ፣ – ለኔ እስከዚህ ነው
እሱ፣ – አልወደድሽውም ማለት ነው?
እሷ፣ – ነገርኩህ እኮ
እሱ፣ – እሱማ ነግረሽኛል። ዳንስ አሪፍ ነሽ።
እሷ፣ – ይሆናል
እሱ፣ – ሙች እውነቴን እኮ ነው።
እሷ፣ – (ፈገግ ትላለች) አላወቅሁም ነበር።
እሱ፣ – ምኑን?
እሷ፣ – ዳንስ አሪፍ መሆኔን ነዋ
እሱ፣ – ማንም ነግሮሽ አያውቅ?
እሷ፣ – ማንም?
እሱ፣ – ዕውሮች መሆን አለባቸው።
እሷ፣ – እነማ?
እሱ፣ – ከዚህ በፊት አብረሽ የደነስሻቸው።
እሷ፣ – ኧረ አይደሉም፣ (ፈገግ ትላለች)
እሱ፣ – እዚህ ከተማ ቆየሽ?
እሷ፣ – ስድስት ወሬ ነው ከመጣሁ
እሱ፣ – ፊት የት ነበርሽ?
እሷ፣ – ከአዲስ አበባ ነው የመጣሁት
እሱ፣ – ገና ነሻ?
እሷ፣ – ለምኑ?
እሱ፣ – አገር አለመድሺም ማለቴ ነው።
እሷ፣ – አዎ ገና ነኝ።
እሱ፣ – አለማማጅ ያስፈልግሻል እኮ
እሷ፣ – እሱማ አለኝ
እሱ፣ – ከሙቼው ልጅ? እሳት ነሽ ማለት ነው።
እሷ፣ – ምን ማለትህ ነው?
እሱ፣ – ከሙቼው ተቀላጠፉሽ ልጂ?
እሷ፣ – አልገባኝም
እሱ፣ – ከሙቼው ያዝሽ ማለቴ ነው
እሷ፣ – ምን?
እሱ፣ – ምኑን ምን ትያለሽ? ቦይ ፍሬንድ ማለቴ ነው።
እሷ፣ – የምን ቦይ ፍሬንድ?
እሱ፣ – አለማማጅ አግኝቻለሁ አላልሽኝም?
እሷ፣ – ታዲያ ቦይ ፍሬንድ አልኩህ?
እሱ፣ – ታዲያ አገኘሁ ያልሺው
ምኑን ነው?
እሷ፣ – አለማማጅ፣ ቦይ ፍሬንድ ካልሆነ
አያለማምድም እንዴ?
እሱ፣ – ማ እንደ ቦይ ፍሬንድ?
እሷ፣ – ለምሳሌ ወንድም፣ ወይም ቦይ
ፍሬንድ ያልሆነ ጓደኛ።
እሱ፣ – የወንድምን እንኳ ተይው?
እሷ፣ – እንዴ እንዴት?
እሱ፣ – እየሽ ወንድም ሁሉን አያሳይም
እሷ፣ – ለምሳሌ ምን?
እሱ፣ – ሙቼ አጣሽውና ትጠይቂኛለሽ?
እሷ፣ – እኔ ደግሞ የማልፈልግ ከሆነስ?
እሱ፣ – ምኑን?
እሷ፣ – አንተ የምትለውን?
እሱ፣ – እኔ ምንም አላልኩ
(ሳቅ ይላል)
እሷ፣ – በቃ ምንም ካላልክ እርሳው።
እሱ፣ – እሺ በቃ ቦይ ፍሬንድ አለሽ?
እሷ፣ – አዎን አለኝ
እሱ፣ – ታዲያ ምነው
አብረአችሁ አላየሁሽ?
እሷ፣ – እሱ እዚህ የለማ?
እሱ፣ – የት ነው?
እሷ፣ – አዲስ አባ
እሱ፣ – "ላም አለኝ በሰማይ . . "
እሷ፣ – ምን ማለትህ ነው?
እሷ፣ – ሩቅ ነው ማለቴ ነው።
እሷ፣ – ሩቅ ቢሆንሳ?
እሱ፣ – ልትገናኙም ላትገናኙም
ትችላላችሁ
እሷ፣ – እንገናኛለን ይመጣል።
እሱ፣ – መቼ?
እሷ፣ – የሚቀጥለው ዓመት
እሱ፣ – ዓመት?
እሷ፣ – ዓመት እኮ ቅርብ ነው
እሱ፣ – በዓመት ውስጥ ብዙ ነገር ይሠራል
እሷ፣ – ምን?
እሱ፣ – ሌላ ሊወድ ይችላል
እሷ፣ – ምን? (በቁጣ)
እሱ፣ – አትቆጪ፣ ያለ ነው ይኸ
እሷ፣ – (በንዴት) የፈለገው ቢሆን
እሱም ቢሞት እንኳ እንዳንተ
ካለው ጋር በውን ቀርቶ በሕልሜም
አልወጣም። (በንዴት መድረክ ላይ
ጥላው ትሄዳለች።)

*

"SLAVES & IVORY"

አሁን ኢትዮጵያ ያለችበትን ለመረዳት
ያለፈውን ታሪክ ማንበብ ያስፈልጋል።
"መሄዴ ነው ማጂ መሄዴ ነው ማጂ፣
እሱን ተከትዬ እንደናቴ ልጅ፤"
እየተባለ ይዘፈን የነበረው ለምን እንደሆነ ያውቃሉ?
ይህንና ይህን የመሳሰሉትን ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት

"SLAVES & IVORY"

የተባለውን መጽሐፍ ያንብቡ።
መጀመሪያ በ1926 ታትሞ out of print
ከሆነ በኋላ እንደገና በ1972 ዓ.ም. ታትሞ
አሁን በገበያ ላይ የዋለ የአጼ ምኒልክን
መንግሥት ማክተሚያና የ ይለ ሥላሴን መንግሥት
መጀመሪያ በዓይን ምስክርነት ያየ፤በኢትዮጵያ የነበረውን
"የባሪያ ፍንገላና ንግድ" ታሪክ ያካተተ
ዝነኛ መጽሐፍ ነው። ብዙ ፎቶግራፎች አሉት።

ጠንካራ ሽፋን ዋጋ $25 U.S. መላኪያ $2.50
በመጨመር በአድራሻችን ይላኩ።
AFRICAN SUN PRESS
P.O.BOX 21365
OAKLAND, CA 94620
Oakland አካባቢ ላላችሁ
Albo African Gift Shop ጠይቁ።

**ALBO AFRICAN GIFT SHOP**

6421 Telegraph Ave.
Oakland, CA 94609

**WE MAKE CUSTOM CLOTHING**



*Ethiopian Silver crosses*
*Paintings on leather canvas*
*Handmade jewelry*
*Wood carvings*
*Trading beads*
*Post cards*
*Posters*
*Clothing*
*Books*
*Spices*
*& much, much more*

(510) 647-4410

(510) 428-2526

5% discount with this ad



**ዶክተር ሣህለ ሥላሴ አርአያ**
**የጥርስ ሐኪም**

GENERAL AND COSMETIC DENTISTRY
Sahle Araya, B.D.S., D.D.S.

*6044 W. North Avenue*
*Chicago, Il. 60639*
*(312)237-8405*

የጥርስ ሕመምን ስቃይ የሚያውቃት ያውቃታል፤
ከጽኑ ሕመም በፊት ጥንቃቄ ያሻል።
በየስድስት ወሩ ጥርስ አለመታጠብ፤
የሚያመጣው ጉዳት ፍጹም አይታሰብ።
ትንፋሽ ደስ ካሰለ ጠረን እያመጣ፤
ጥርስም እየደማ ከመጠበት ጣጣ፤
ሐኪም እክ አለሎት መፍትሔ የሚያመጣ።

የምግባችንን ልምድ አጢኖ የሚያውቀው፤
የሚስማን ስሜት ይኸ ነው ስንለው፤
ያለ ቋንቋ ገደብ በደምብ የሚረዳው፤
የአገር የወንዝ ልጅ ዶክተር ሣህሌ ነው።

*OPEN MONDAY Thru SATURDAY*
*10:30 A.M. to 7:00 P.M.*

*CALL FOR APPOINTMENT*

# ደራርቱ

ለሠራችው ተግባር ላገር ለዋለችው፣
ጥንካሬያችንን ደግማ ላሳይችው፣
በወንዱም በሴቱም እኛው ነን ባለችው፣
ያገሯን ባንዲራ በዓለም አደባባይ ላውለበለበችው፣
ባለ ሦሥቱን ቀለም ለብሳ ለኮራችው፤

ለአፍሪካዋ ጀግና ለኢትዮጵያ ብስራት፣
ለደራርቱ ቱሉ መታሠቢያ ይሁናት።

ይህን ሰጥቻለሁ መታሰቢያዋ ነው፤
የሁላችን ኩራት መሆንዋን ትወቀው።

## ደራርቱ ደራሪ ቢያ

አጥንትን ቀሲቃሽ ሙት አስታዋሽ፣
ያበበ ደም የዘር ትንፋሽ።

የማሞ ክንድ የግራሩ፣
የውስጥ እምቅ ያገር ፍቅሩ።

የሴት ዝክር ኩሩ ባገር፣
የባንዲራ ሰንደቅ ማገር።

አንቺ ሴቷ አፍሪካዊ፣
ልበ አንበሳ ኢትዮጵያዊ።

"ደራርቱ አማስ ደራሪ፣ "
እኛም ኮራን አንቺም ኩሪ።

የዘር ማንዘር ያለም ጉራ፣
የጥድ ማገር የሴት አውራ።

የለበስሺው ያ ባንዲራ፣
ስንት ያገር ልጅ ባንቺ ኩራ።

የአገር ዕንቁ የኢትዮጵያ፣
ደራርቱ ደራሪ ቢያ፤
ደራርቱ ደራሪ ቢያ።

ደራርቱ ደራሪ ቢያ

ከግርማ ዘገየ

# ችካጎና ኢትዮጵያውያኖች

ከ"ላንዳፍታ" ዝግጅት ክፍል

ችካጎ በአሜሪካ መካከለኛው ምዕራብ፣ በኢሊኖይ እስቴት የሚገኝ ትልቅ ከተማ ነው። በከተሞች ሕዝብ ብዛትና ስፋት በአሜሪካ ሶስተኛው ነው፤ ከኒው ዮርክና ከሎስ አንጀለስ ለጥቆ ማለት ነው። በረዣዥም ሕንፃ ብዛት ከኒው ዮርክ ቀጥሎ የሚስተካከለ የለም። ሎስ አንጀለስ የሕንፃ ነገር ሲነሳ ከቦታውም የለ። ዋሽንግተን ዲ ሲም እንዲሁ። ቺካጐ መጥቶ ሰማይ ሰማይ ማየት የሚያበዛ ጐብኚ ወይ ከዲ ሲ ወይ ከሎስ አንጀለስ የመጣ መሆን አለበት ተብሎ ይታማል። የሚባለውን ነው፣ ዲ ሲዎችና ኤል ኤዎች አትቆጡ እንግዲህ።


ድሮ ምን ይመስለኝ ነበር፤ በሕንፃና በሁሉ ነገር የሚያጌጥ የአንድ አገር ዋና ከተማ ይመስለኝ ነበር። ዲ ሲ ለጉብኝት ሄጄ ሳይ ገረመኝ። ከካፒቶል ልቆ የሚገኝ ሕንፃ ፈቃድ አግኝቶ አይሰራም ተባልኩ። ምነው ስለ ሕንፃ ቀባጠርክ ትሉኝ ይሆናል። ቺካጐን አንደኛ የሚያደርገው በዓለም ረዥሙ ፎቅ የሚገኘው እዚህ ስለሆነ ነው። ሲርስ ታወር ይባላል። 115 ፎቅ አለው። በዓለም ፈጣኑ ኤሌቬተር እያክተፈተፈ በአንድ ደቂቃ ከጣራው ያደርሳል። 30,000 ሠራተኞች ተዝናንተው የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን የሚያከናውኑባቸው በጣም ብዙ ድርጅቶች ተከራይተውታል። የቺካጐ ሕንፃዎች ቅርፅ (architecture) አንዱ ከሌላው ስለሚለይ ለዓይን አይሰለችም። በዓለም ላይ በአንድ ደቂቃ ውስጥ ብዙ አይሮፕላን በማሳረፍና በማስነሳት ተወዳዳሪ የሌለው የ ኦ ሄር (O'Hare) አይሮፕላን ማረፊያ የሚገኘውም እዚሁ ችካጐ ነው።

ችካጐ ከሰሜኑ ጫፍ አንስቶ እስከ ደቡቡ ጫፍ በግምት ከ25 እስከ 30 ማይል ርዝመት ሲኖረው ይኸው ክልል የሚችጋንን ሐይቅ ይዋሰናል። ሐይቁ ለከተማው ውበት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ከማድረጉም በላይ ለከተማው ነዋሪ ጥሩ የመዝናኛና የመናፈሻ ቦታ ፈጥሯል።

የከተማው ሕዝብ ብዛት በ1990 ቆጠራ 2,783,726 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ነጩ 37.9% ፤ ጥቁር አሜሪካዊው 38.6%፤ ሂስፓኒኩ 19.6%፤ አሜሪካዊ ሕንዱ፤ እስያዊውና ሌላው ቀሪው others በመባል የሚታወቀው (እኛም የምንታከልበት ማለት ነው) 3.9% ብቻ ነው።

ትክክለኛ ቆጥራ ተካሂዶ ባይታወቅም በችካጐ ከተማና አካባቢው ከ2,500 እስከ 3,000 የሚደርሱ ኢትዮጵያኖች ይኖራሉ የሚል ግምት አለ። እንደሌላው የአሜሪካ ከተማ ሁሉ እዚህ የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን የመጡት ለትምህርት፣ በስደትና በሥራ ነው። እንደ ከተማው ትልቅነት ብዙ ኢትዮጵያውያኖችን ያልሳበው በአየሩ ጠባይ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም። ሲቀዘቅዝ (በwinter) ጣርማ በርጉና ነፋስ መውጫን ቆላ ያሰኛል። ሲሞቅ (በsummer) ከግለቱ ሌላ የአየሩ ሂውሚዲቲ ያስጨንቃል። ታዲያ ቀብራራው ያገሬ ልጅ "ይህችን ይወዳል፤ የምን በቁም መቃጠል ነው" የሚልበት ያየር ጠባይ በመሆኑም ሊሆን ይችላል። ለሥራውም ሆነ ለትምህርቱ ባይበልጥ እንጂ ከሌሎቹ ከተሞች አያንስም።

ቺካጐ በ77 የኮሚኒቲ ክልሎች የተከፈለ ሲሆን ሕዝቡ በወገን በወገኑ ተለያይቶ በተለያዩ የኮሚኒቲ ክልሎች ስለሚኖር በሴግሪጌሽን ከፍተኛውን ቦታ ከሚይዙ ከተሞች አንዱ ነው። የጥቁር ሰፈር፣ የነጭ ሰፈር፣ የሂስፓኒክ ሰፈር ተለያይቶ ይገኛል።



የተለያዩ ቅርጽ ያላቸው ሕንፃዎች ለከተማው ውበት ሰጥተውታል።


(ከርቀት የሚታየው ባለ ቀንዱ ባለም ረዥሙ ሕንፃ ነው)

ጥቂት አካባቢዎች ብቻ ናቸው ሁሉም ዓይነት ሰው በአንድነት የሚኖርበት። ታዲያ አበሻውም በብዛት የሚኖረው በነኚህ የተለያዩ ዘሮች በአንድነት በሚኖሩባቸው የኮሚኒቲ ክልሎች ማለትም (integrated) በሆኑት ውስጥ ነው። እነኚህ integrated የሆኑ ኮሚኒቲዎች የሚገኙት በተቀራረበ ቦታ ስለሆነ ደግሞ ኢትዮጵያዊው እንደ ልቡ ይገናኛል።

በትምህርት ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ደረጃ፣ በሥራ መስክም በተለያዩ የሙያና የጉልበት ሥራዎች የተሰማሩ ብዙ ኢትዮጵያኖች አሉ። የራሳቸውን የንግድ ድርጅት በመክፈት በሬስቶራንት፤ በማታ ክበብ፤ በጥርስ ሕክምና፣ በታክሲ ሥራ፤ በመልዕክት ማድረስ አገልግሎት (messenger service) በጉዞ ውክልና፣ በሕትመት ሥራ፣ በኢንሹራንስ፤ በመጽሔት ዝግጅት ወዘተ. . .የተሰማሩ ኢትዮጵያኖችም አሉ። በቺካጐ ታዋቂውና ትልቁ የሬጌ ክለብ (Wild Hare)፤ የኢትዮ ቪሌጅ ሬስቶራንት፤ አዲስ አበባ ሬስቶራንት፤ ማማ ደስታ ሬስቶራንት፤ ከብዙው በጥቂቱ የሚጠቀሱ ኢትዮጵያውያን በባለቤትነት የያዙዋቸው ድርጅቶች ናቸው። እነኚህ ድርጅቶች በአብዛኛው የሚገኙት በአንድ አካባቢ በመሆኑ ለኢትዮጵያኖች መገናኛት አመቺ ሁኔታ ፈጥረዋል። የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያኖች በየሳምንቱ እሁድ እሁድ ለጸሎት የሚገናኙበት የመድሃኒያለም ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ኤቫንስተን በሚባል የቅርብ ከተማ ይገኛል። ከ 5 በላይ ቋሚ ሠራተኞች ቀጥሮ የሚስተዳደረው በችካጐ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበርም በየወቅቱ የሚያዘጋጀው የመዝናኛ ምሽቶችና ስብሰባዎችም ኢትዮጵያውያንን በማገናኘት በኩል ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጓል።

እንደ ማንኛውም ትልቅ ከተማ ቺካጐ ቀልጠፍ ካላሉበት እንደማያዛልቅ በደምብ ስለገባው አበሻው ነቃ ማለትን ያዘወትራል። እንደ ኒው ዮርካዊ እሳት ባይሆንም። መፍዘዝና መቅለስለስ ውጤት አልባ መሆኑን ለመረዳት አበሻው ጊዜ አይፈጅበትም። አካባቢው ራሱ ያሯሩጣል። ካልተሯሯጡ የ"ሶፋ ድንች" (couch potatoe) ሆኖ የቲ ቪ ቀበኛ መሆን ነውና።

==========



የአገር ልብሳችን ውበታችንም ነው።
ከቺካጐው መድሃኒያለም ቤተክርስትያን ፊትለፊት



ቺካጐ - ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በእስክስታ ሲፎካከሩ

# የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማኅበር በችካጐ

ከቺካጐው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር የተገኘ

የችካጐ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ መረዳጃ ማህበር በዲሴምበር 1984 ተቋቋመ። ይህን ማህበር በመመሥረትና በማጠናከር ረገድ የኮሚኒቲው አባላትና መሪዎች እንዲሁም ደጋፊዎች ያደረጉት ተሳትፎና አስተዋጽዖ ከፍተኛ ቦታና አስተዋጽዖ የሚሰጠው ነው። ችግርን በጋራ መቋቋምና ደስታን በባህላዊ መንገድ ለመግለጽ የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር በሚል መሠረታዊ እምነትና አስተሳሰብ ላይ ተመርኩዞ ነው ማህበሩ የተቋቋመው።

በችካጐና አካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን በሥራ፣ በትምህርትና በማህበራዊ ኑሮና በመሳሰሉት ረገድ የሚገጥማቸውን ችግሮች ለማስወገድና ጠቅላላ ዕድገታቸውን ለማዳበር ይረዳም ዘንድ ታስቦ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ባህላችንንም ለሌሎች ሕዝቦችና ባህሎች ማስተዋወቅ፣ ሕጻናትም ጥሩ ኢትዮጵያዊ ባህሪያቸውን እንዳይረሱ ማስተማር ሌላው ዓላማና ተግባር ነው። ለዘመናት በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰውን ረሀብና ስደት በሚመለከት ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማስታወቅና አቅም የሚፈቅደውን ያህል መርዳት ከማህበሩ ዓላማዎች ከፊሎቹ ናቸው።



ዶ/ር እርቁ ይመር - የማህበሩ ኤግዚክቲቭ ዲሬክተር

ማህበሩ እነዚህን መሠረታዊ ዓላማዎችና ተግባሮች ለማሟላት የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ፕሮግራሞችንና ዘርፎችን ፈጥሮ ለኢትዮጵያውያንና ለሌሎችም አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው። የአሜሪካን ባህልና አኗኗር ትምህርትና ምክር መስጠት፤ የጤና አገልግሎቶች እንዴት እንደሚገኙና ሥራ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል በመሳሰሉት በማህበሩ በኩል ተገቢ የሆነ ጥቆማዎችን (Referral) ያደርጋል። የትርጉም አገልግሎት ከመስጠቱም በላይ በተገልጋይ ስም ጉዳይ ያስፈጽማል። ኢሚግሬሽን ነክ በሆኑ ጉዳዮች ትምህርታዊ ስብሰባዎችንና ጠቃሚ ዜናዎችን ለኮሚኒቲው አባላት ማቅረብ ሌሎች የአገልግሎት ዘርፎቹ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የሥራ ፍለጋ አገልግሎት ዘርፉ በመጠናከር ሥራ ፈላጊዎችን በቅድሚያ ከማዘጋጀት ጀምሮ እስከ ሥራ ፈልጐ ማስያዝ ድረስ ከፍተኛ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። የሕጻናትን ፕሮግራም በሰፊው ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ነው። የኢኮኖሚ ዕድገትና የሴቶች ፕሮግራምን ለመዘርጋት ታቅዶ በጥናት ላይ ይገኛል።

የኮሚኒቲው ማህበር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ብቻ ሳይሆን የሌሎች አፍሪካ አገሮችንችንና የመካከለኛውን ምሥራቅ ስደተኞች በችካጐ አካባቢ እንዲሰፍሩ የሚያስችል የአገልግሎት ፕሮግራም ጀምሯል። ከመሠረታዊ አገልግሎቶቹ በተጨማሪ ደግሞ በየአገሩ በስደት



የማህበሩ ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች

ላይ ያሉ ኢትዮጵያውያን ሕገወጥና ኢሰብአዊ የሆነ በደል እንዳይፈጸምባቸው፣ መብታቸው እንዲከበርና እንዲታወቅ ለሚመለከታቸው ሰብዓዊና መንግሥታዊ ተቋሞች በየጊዜው በማስታወቅ ጥብቅና በመቆም (advocacy) አስተዋጽዖ አድርጓል። በተለይም ወደ አሜሪካ በስደተኝነት እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው አፍሪካውያን ቁጥር ከሌሎች አህጉራት ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆኑን በመረዳት ማህበሩ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ከሌሎች መሰል ድርጅቶች ጋር በመተባበር ባደረገው ትግል ቁጥሩ አጥጋቢ ባይሆንም በየዓመቱ እንዲጨምር በማድረግ በኩል ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጓል።



የማህበሩ ሠራተኞች በሥራ ላይ



ኢትዮጵያውያን በአብዛኛው በሚኖሩበት አካባቢ ከገቢ ጋር ተመጣጣኝ የቤት ኪራይ (affordable housing) የሚያገኙበትን ሁኔታ በመፍጠርና ጥረት በማድረግ ጥሩ ውጤቶችን አስገኝቷል። ማህበሩ እነዚህንና የመሳሰሉትን የማህበራዊና የሰብዓዊ አገልግሎቶችን በመስጠት በኩል ባደረገው አስተዋጽዐ ከልዩ ልዩ ድርጅቶች በየጊዜው ሽልማቶችን አግኝቷል። በዚህ በ1992 ዓ.ም. ብቻ ሁለት ዋና ዋና ሽልማቶችን አግኝቷል። እነኚህም Link, Inc. በመባል ከታወቀ የአፍሪካን አሜሪካን ሴቶች ድርጅትና United to Serve America በመባል ከታወቀ ድርጅት የተሰጡ ከፍተኛ ሽልማቶች (Diamond Award)ናቸው።

ማህበሩም ወደፊት አገልግሎቱን በሰፊው የሚቀጥል መሆኑን በማስረዳት ለዕድገቱ አስተዋጽዖ ያደረጉትን የኮሚኒቲውን አባላትና ሌሎችንም የሚያመሰግኑ መሆኑን የማህበሩ ኤግዜኪቲቭ ዲሬክተር ዶክተር እርቁ ይመር ገልጸዋል።

ይህንን ታላቅ አስተዋጽዎ በሚያደርገው የኮሚኒቲ ማህበር አባል ለመሆን የምትፈልጉም ሆነ ዕርዳታ ማድረግ የምትሹ ወይም ለመረዳት የምትፈልጉት ነገር ካለ በስልክ ቁጥር (312) 728-0303 ዘወትር በሥራ ሰዓት ደውላችሁ ልታነጋግሩን ትችላላችሁ። ወይም በአድራሻችን በመጻፍ ትችላላችሁ።

Ethiopian Community Association of Chicago
4750 N.Sheridan Rd., Suite #249
Chicago, IL. 60640

# የአበው ቅርስ

አማርኛ ብዙ ምስጢራዊ አነጋገሮች አሉት። በተረትና ምሳሌ፣ በቅኔ እንዳደም በዘፋን ግጥሞች ሲቀርቡ ደስ ከማለታቸውም ሌላ የቋንቋውን ብስለት ያረጋግጡልናል። እስቲ አንድ አዲስ አበባ እያለሁ አንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህር (ጓደኛዬ) ያለኝን ልንገራችሁ።

"ጣልያንኛ ለቁጣ፣
እንግሊዝኛ ለጉራ፣
ፈረንሳይኛ ለፍቅር፣
አማርኛ ለነገር።"

አማርኛ ቋንቋ የነገር ቋንቋ ነው ለማለት አይደለም ይህ የተባለው፣ ብስለቱንና የአባባሎችን ጥንካሬ ለመግለጽ እንጂ። እናም "ላንዳፍታም" ይህን "የአበው ቅርስ" የተሰኘ አምድ የከፈተችው እነኚህን አባባሎች እየፈለገች በማቅረብ ከአገር ርቀን ለምንገኝ እንዳንረሳቸው ለማስታወስ ነው። ስለዚህ አምድ ማደግ የአንባብያን አስተዋጽዖ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ታዲያ ተረቶች፣ ቅኔዎች ጠለቅ ያለ ትርጉም ያላቸው ግጥችና አባባሎች በመዘከራችሁ ካለ ላኩልን።

---

## ተረትና ምሳሌ

1. በልቶ መጠጥ ያጣ ተበድሎ ፍርድ ያጣ።
2. ከአነጋገር ይፈረዳ ከአያያዝ ይቀደዳል።
3. በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ።
4. ጉድና ጅራት ከበስተኋላ ነው።
5. ብዙ ቧልት ያፈርሳል ንብረት።

................................

## ተረት ተረት የመሠረት

በእንስሳት ገጸ ባህሪነት እየተሳለ በልጅነታችን ይነገሩን የነበሩት ተረቶች ትዝ ይሏችኋል። የጦጣን ብልጠት፣ የጅብን ሆዳምነት፣ የአንበሳን ያልነት እያወሳ በዘዴ ይሰጠን የነበረው ትምህርት ለአስተዳደጋችን ትልቅ አስተዋጽዖ ነበረው ብንል የምንሳሳት አይመስለኝም። ዝቅተኛ ክፍል እያለን የተማርንበት የከበደ ሚካኤልን "ታሪክና ምሳሌ" ማስታወሱ ይበቃል። በርቀት የተነሳ አግኝተን ፈቃዳቸውን ለማግኘት ባንችልም ለትምህርት ስለሆነ አይቆጡም በማለት አንድ ተረታቸውን አቅርበናል።

## ዝንጀሮ

(ከታሪክና ምሳሌ 3ኛ መጽሐፍ የተወሰደ)

እንዲት ዝንጀሮ ናት የምታስደንቀን፣
ሥራዋን ስናስብ ዘዴኛ ናት ብለን።
አንድ ቀን ስትሄድ ጥቅጥቅ ባለው ጫካ፣
በመሓ አካሏ ብዙ እሾህ ተሰካ።
እንዳትቀመጥም ወይም እንዳትቆም፣
ወግቶ አስጨንቋት ተጠምቃ በደም።
አንድ ሰው አየና ቀርቦ ጠየቃት፣
የቱን ልንቀልልሽ ንገሪኝ አላት።
ሁሉንም ለማውጣት አልተቻለኝም፣
ቸኩያለሁና ጊዜ አላገኘም።
ከነቀልህልኝስ አለችው ጌታዬ፣
መጀመሪያ ይውጣ የመቀመጫዬ።
ቂጤ መሬት አርፎ ትንፋሼን ካገኘሁ፣
የቀረውን ሁሉ እኔ አወጣዋለሁ።
ይህንን ተናግራ ዝንጀሮ አረፈች፣
እሾሁን በተራ እያወጣች ጣለች።

---

## ቅኔ

እስቲ እነኚህን ቅኔዎች ተወያያታችሁ ፍቷቸው።

የድሮ መድሐኒት ኮሶ ምን አላችሁ፤
ምንም አያስቀምጥ ይኼስ ቀጨሟችሁ።

*

ቆላ ወርጄ ጥጥ ብዘራ፣
አላብብ አለኝ አላፈራ።
ምን እለብስ ብዬ ሲጨንቀኝ፣
አፈራለሁ አለኝ።

*

እንጀራ ቆርሶ ማን ባበላኝ፣
እኔማ ጣቴ አስጠላኝ።

---

## ፈሊጦች

ቃላት ከሌሎች ቃላት በሚቀናጁበት ጊዜ ከነበረው ፍቺ የተለየ ትርጉም ይሰጣሉ። በእንግሊዝኛው Idiomatic Expression እንደሚባለው ዓይነት ነው። እስቲ ከዚህ በታች ያሉትን ፈሊጦች በመልሳቸውን ከፋትለፊታቸው ካለው ዝርዝር አዛምደው ያግኙ።

| | |
|---|---|
| 1.የብረት ልጥ | ሀ. ተራቆተ |
| 2.በደረቁ ላጨኝ | ለ. ትውከታ |
| 3.ሁለት ልብ | ሐ. እጭር |
| 4.ዐይነ ሌባ | መ. ወላዋይ |
| 5.ላይበሌ | ሠ.ቀልድ አይደለም |
| 6.አንድ በለኝ | ረ. ጠንካራ ክንድ |
| 7.ካንጀቴ ነው | ሰ. መንቃራ |
| 8.ቂጡን ጣለ | ሸ. ሴሰኛ |
| 9.ቁመተ ዶሮ | ቀ. አታለለኝ |
| 10. ማዶ ማዶ | በ. አስጥለኝ |

---

## የልጅነት ጨዋታ ትዝታ

ሀይሉ ሶርሱ ሮበሌ (ከችካጐ) ናቸው የላኩልን

ዳንኪራ ዳንኪራ፤ ዳንኪር መቃመቆ
የድሮ ሽንበቆ፤
የድሮ ማርማሬ፣ ወንዛ ወንዜ ሲዞሬ፤
ወንዜ ምን ሰማሽ፣
እንዶዴ በላሽ፤
እንዶዴ ዳገቴ
ልጥለፍሽ ብላኝ
እናት አባት የለኝ።
እናት አባት የድሮ፣
ሁሉን አስተዳድሮ።
ከቤቴ በላይ ቁራ ሰፍሮ ቁራ ሰፍሮ፤
የለችም ብሎ ሄዶ በሮ ሄዶ በሮ።
እኔን ያብረኝ ያክንፈኝ ያክንፈኝ፣
የዝሆን እሞት ያስጠጣኝ ያስጠጣኝ።
የዝሆን ሐሞት መራራ ነው መራራ ነው፤
የጉበዝ ልቡ ተራራ ነው፣ ተራራ ነው።
ተራራ ሂጄ ስመለስ ስመለስ፤
አህያ ሞቶ ጅብ ሲያለቅስ ጅብ ሲያለቅስ፣
እርጉብ ቁጭ ብላ ስትቀድስ ስትቅድስ።

---

## የዘፈን ግጥሞች

ከወንድወሰን ይመር (ችካጐ)

ሎሚ ብወረውር ደረቷን መታኋት፣
አወይ ኩላሊቷን ልቧን ባገኘኋት።
ከእባይ ወዲያ ማዶ ወዳጅ አለኝ ማለት፣
ዋ! ብሎ መቅረት ነው ውሃ የሞላለት።
አንባሰል ለገደል ምን ያሽሟጥጡታል፣
ፈረስ ባያስጋልብ ልጅ ይወጣበታል።
ትዝታህን ውሰድ ብለሽ የላክሺብኝ፣
አንቺው ጋ ይቀመጥ እኔም ሌላ አለብኝ።

## ዘሬን አትጠይቁኝ!

ከግርማ ዘገየ ይግለጡ

ሁሌ ይጠይቀኛል፣
አንተ ማነህ ይለኛል፤
ዘርህን ቁጠርልኝ፣
ብሎ ያስቸግረኛል፣
አንተ ማነህ ይለኛል፣
ይወተውተኛል።

የማን ዘር የማን ደም፣
ከየት ነህ ይለኛል።
እራስህን እወቅ፣
ሐረግህን መርምር፣
እኮምናስፈራህ አንተነትክን ዘርዝር።
ይለኛል ወገኔ ዘሩን የተረዳው፣
ዘርማንዘሩን አውቆ ሐረግ የቆጠረው።
አንተ ማነህ ይለኛል፤
አፍጦ ይይዘኛል።

ዘርህን ቁጠርልኝ፣
ሐረግህን መዝህ እከሌ ነኝ በለኝ።
ይለኛል ወገኔ ዘር ግንዱን ያወቀው፣
በዘር ሐረግ ጥናት በጣም የረቀቀው።
ደሞ ይጠይቀኛል፣
ይጨቀጭቀኛል፤
ዘሬ ጠፍቶኝ እንደሁ ምርጫ ይሰጠኛል።

ጉራጌ ነህ ኩሎ?
ሲዳሞ ነህ ዶርዜ?
ተጉለቴ ነህ ሞረት?
ዋጂቱ ነህ መንዜ?
የጉንደር አማራ ወይስ ነህ ጉጃሜ፣
የትግራይ ወርጂ ነህ ወይስ ከአጋሜ።
ሣህል ነህ ኩናማ፣
ወይስ ከአሳውርታ፤

የሸዋ ኦሮሞ ከወደ ሱሉልታ?
አፍጦ ይይዘኛል፣
ዶርዜ ነህ ከምባታ፣
ተናዘዝ ይለኛል።

ኩሎ ነህ አርጉባ፣
ቆቱ ነህ ሱማሌ፣
ንገረኝ ልወቅህ በለኝና እገሌ።

እኮ አንተ ማነህ?
ግንዱ የጠፋበት ዘርህን የማትቆጥር፤
ማንነትህን አውቀህ ደፍረህ ማትናገር።

ሸናሻ ነህ ወይጦ
ቅማንት ነህ አፋር፣
የቢለን ትግሬ ነህ ወይስ የቢንአምር።

አማራ ነህ ትግሬ
ዶርዜ ነህ ከምባታ፣
ኦሮሞ ወላሞ
ወይስ አሣውርታ።

ይወተውተኛል
ፈተናህን እለፍ ዘር ቁጠር ይለኛል።

ሁሌ ንዝንዙ ፈተናው ቢከብደኝ፣
ዘሬን ዘርማንዘሬን ፍለጋ ገባሁኝ።
እኔ የማላውቀውን፣
ችዬ ማልዘልቀውን፤

እናቴን ጠየቅሁኝ ቢቸግረኝ ጊዜ፣
ዘሬን ውለጂ አልኳት
ጉራጌ ነኝ መንዜ።
እሷም ነገረችኝ ሁሉንም ዘርዝራ፣
ዘርማንዘር ሐረጌን በርብራ አበጥራ።

"የአባትህ አያቶች የሴቷም የወንዱም፣
በጣም ልዩ ናቸው ዘራቸው አይገጥምም።
በአባታቸው ወገን ሴቷ ናቸው ጋላ፣
የናታቸው ትውልድ ድሬ ነው መጋላ።

ወንድዬው ከሸዋ ከወደ አሊልቱ፣
ባንደኛው ጉናቸው አፋርና ኢቱ።
እነዚህ ተባዝተው
ሌላ ዘር ጨምረው፣
ዘር በትነው ወልደው፤
አያቶችህ መጡ ሁለት ዘር አክለው።

አሁን ጥፍት አለኝ ጊዜው ረዘመና፣
ይኼ ይመጣል ብዬ መች ገመትኩኝና።
ብቻ ትዝ ይለኛል፤

በጣም ትዝ የሚለኝ የአባትህ እህት፣
ከሌላ ተወልደው ከወደ ተጉለት፣
የአማራም ደም አለህ፣
በአንደኛው ጉንህ።

አባትህ ተዛውሮ ሲመጣ ለሥራ፣
ከኔ ጋር ተያየን እዚሁ አስመራ።
በፍቅር ወደቅን ምን ብዬ ልንገርህ፣
የእህል ውሃ ሆኖ ይኸው በቃን ለዚህ።

የኔን ያልነገርኩህ ዘሬን ቆጣጥሬ፣
ባልነግርህ ይሻላል ላልዘልቀው ቆጥሬ።
እኔ ከቆጠርኩት ሁሉንም በውጉ፣
ከዘጠኝ አያንስም የዘሬ ሐረጉ።

ልጄ አንጀቴ ሆዴ
ልንገርህ ኑዛዜ አንድ ትልቅ ነገር፣
ትንሽ ምላጭ ብጤ ቤሳ ፈልግና፣
ከጣትህ ላይ ላመል ሰንጠቅ አድርግና፤
ደምህን ውሰደው
ለመርማሪ አሳየው፣

ይወቁት እነሱ ይመርመር በብርቱ፣
ያጣሩት በወንፊት ሐኪም ሊቃውንቱ።
ታዲያ መጨረሻ ምን እንዳገኙልህ፣
ደምህ አመዝኗል
በአንደኛው ዘር ግንድህ።
ወይም ቸግሮናል ለማግኘት ዘርህን፤
ቢሉህም ንገረኝ የደረስክበትን።"

ብላ ነገረችኝ፣
እናቴ አዘዘችኝ፣
ደምህን ሊቃውንት አስመርምር አለችኝ።

እኔ ግን ወሰንኩኝ
ቃሌን አጸናሁኝ፤

ዘሬን አለመቁጠር በሕግ ካስቀጣኝ፣
ደምብ ሆኖ በችሎት እኔን ካስጠየቀኝ፤
ያውግዙኝ ይስደቡኝ
ዲቃላ ይበሉኝ።
ይሳቁ ይሳለቁ
በጠባቡ ችሎት፣
ለዘር ፍርድ ያቅርቡኝ፤

እኔን ለፈጠሩኝ ደሜንም ይስጧቸው፣
ሥጋዬን አጥንቴን በቅርጫ ያካፍሏቸው።
ዘር ባለመቁጠሬ
አገር የለህ ካሉኝ፤

ሀገሬን በዘር ግንድ
ነጥቀው ከወረሱኝ፣
ዘርህን አልቆጠርክም
አንተ ማነህ ካሉኝ፤
ጂፕሲ ነኝ ከርታታ፣
የትም እኖራለሁ
ዘር ከማይቆጥሩት ጋራ።
ቅይጥ ከሆኑት ጋር
በጋራ አብራለሁ።

የኔ ግን ጽናቴ፣
የደም አምድ እምነቴ፤

የዘወትር ምኞት ማላ፣
የኢትዮጵያዊነት እምነት ቃሌ፤

የነገ እኔ ድርና ማግ፣
የአዲስ ሕይወት ቀጭን ፈትሌ፤
የእርስ በርሴ የእርቅ ሰነድ፣

የቃልኪዳን ጠናን ውሌ፤
የሕሊና ጠዝጣዥ ቁስሌ፣
የልብ ውስጥ እኽ መግሌ።

የቁጭት ፍም ረመጥ፣
የውስጥ እሳት እንፋሎቴ፤
የመሆኔ እንጥረኛ፣
አቅላጭ አፍሳሽ እኔነቴ።

የፍልሚያዬ መካተቻ፣
የጦር ጋሻ መሰቂያዬ፤
የኔው የኔ መበቀያ፣
የድል ሀሴት ርካታዬ፣
ዓላማዬ፣

ሰው መሆኛ ቀጠሮዬ፣
የመዋተት እፎይታዬ፤

የአንድነት ቀጭን ጥብጣብ፣
የጋራ ዕድገት መሀላዬ፤
የነገ እውን እውነታዬ፤

ሐረጌ አይደለም አቋሜ፣
ዘሬ አይደለም ዓላማዬ።

ሀቁ ነው ትልም እትብቴ፣
አንድነት ነው እምነቴ፣

ዘሬ አይደለም ዕውቀቴ።
ሐረጌ ድብልቅ ነው፣

ዘሬን አትጠይቁኝ፣
በውስጤ ይቀመጥ አትወትውቱኝ፣

የኔ ግን እምነቴ
በቂ ነው ኢትዮጵያዊነቴ።

BRANA ELECTRO PUBLISHING COMPANY

ብራና ኤሌክትሮ አሳታሚ

ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

P.O.BOX 31387

ADDIS ABABA, ETHIOPIA

የወንዛችን ልጆች! እንደምናችሁ? ብቸኝነቱ መቼስ እያንገላታችሁ ነው! ያውላችሁ ድርጅታችን ጉብኝ ይዞላችሁ ቀርቧል። ልብ በሉ። ድርጅታችን በየሁለት ሳምንቱ በአማርኛና በእንግሊዝኛ እየታተመ በሚወጣው "እንካችሁ" ("SCRAMBLE") የማስታወቂያ ጋዜጣው አገልግሎት መስጠት ከጀመረ 6 ወር አልፏል።

** ብቸኝነቱን ለመቋቋም ወዳጅነት ለመመሥረት ካሰቡ ዛሬውኑ ስለ ራስዎ ዘርዘር አድርገው ከመለያ ስሞና የፖስታ አድራሻዎ ጋር የሚፈልጉትን ወዳጅ ዓይነት ይጻፉልን። በኛ ይሁንብዎ ደብዳቤው ይንጋጋልዎታል።

** እንኳን ደስ አለዎት (ለሠርግ፣ ለልደት) እና የማጽናኛ (ለሃዘን፣ ለሕመም) ዓምድ ስላለን ወዳጅ ዘመድ ያስታውሱ፣ ያስገርሙ!

** ኢትዮጵያ ውስጥ መፍጠር የሚፈልጉት የንግድ ግኑኝነት (Business Contact)፣ የሚሸጡት፣ ሚገዙት ወይም የሚፈልጉት ማንኛውም ነገር ካለ ዛሬውኑ ቶሎ ጻፉልን፤ እስካሁን የቆዩት ይበቃል።

** መጽሐፍት፣ የመጽሔትና የጋዜጣ ጥራዝ manuscript) ተቀብለን እናሳትማለን፣ እናሰራጫለን።

** በውጪ የሚታተሙትን ማንኛውም ጽሑፎች አገር ውስጥ አሳትመን አባዝተን እናሰራጫለን፣ እንሸጣለን።

** የግል ማስታወቂያዎ (private) በነፃ ይስተናገዳል።

እባክዎን ገንዘብ አይላኩ!

አድራሻችን፤ ብራና ኤሌክትሮ አሳታሚ
ፖ.ሣ.ቁ. 31387
አዲስ አበባ




በኢትዮጵያ የ"ላንዳፍታ" አሳታሚና አከፋፋይ

P.O.box 31387
Addis Ababa

Tel. 514662
Telex 21183 - Fax 513199

## ሁሉም ቀልድ ያስቃል ?

እስቲ ስለ ቀልድ ትንሽ እናውራ። ማንኛውም ቀልድ ሁሉንም አያስቅም። ለምን እንደሆነ ይገርማችሁ ይሆናል። አንድ ቀልድ ሲነገር አንዳንዱን ልቡ እስኪፈርስ ሲያስቀው አንዳንዱን ንቅንቅ አያደርገውም። ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ቀደም ብሎ በተደጋጋሚ የተሰማ ከሆነ ላያስቅ ይችላል። ሊቀለድበት አይገባም ተብሎ የሚታሰብ ሁኔታ ላይ ያተኮረ ቀልድ ከሆነ ያናድዳል እንጂ አያስቅም። ሁኔታና ቦታ ታይቶ ቀልድ የሚወራው። ይህ ብቻ አይደለም። የሚነገርበትም ቦታ ሆነ እንዲሰማ የሚነገረው ሰው አካባቢውም ሆነ ባህሉ ወሳኝነት አለው። የአዳማጩ ጾታና ዕድሜም ትልቅ ሚና አላቸው። ለአቅመ ሔዋን በደረሱ ሴቶች ድክመት ላይ ያተኮረ ቀልድ ሴቶችን አያስቅም፤ ጐረምሶችን ግን ልባቸውን ያፈርሰዋል። የጐረምሶችን ድክመት የሚያጋልጥ ቀልድ ሴቶችን ሲያንከተክት ወንዶችን ያጨሳል። እና ምን ለማለት ነው። አንድ ቀልድ ተናግረን ያልተሳቀልን እንደሆነ መናደድ እንደማይገባን ለማሳሰብ ነው። ምክንያቶች ስላሉት።

የቀልዱ አቀራረብና አነጋገርም ወሳኝነት አላቸው። ጥሩ ቀልድ ተናጋሪ የማያስቀውን ነገር አጣፍጦ ቅመሟን ጨምሮ በመናገር ያስቃል። አንዳንዱ ለዛቢስ ደግሞ በጣም የሚያስቀውን ነገር ሲናገር የሚስቅለት አያገኝም። አንዳንዱ ቀልድ ሲናገር ራሱ ስቆ ይጨርሰዋል። የተናገረው ቀልድ ሳይሆን የአሳሳቁ ሁኔታ ራሱ ያስቃል።

አንዳንዱ ደግሞ ሁሌ ተሳቀልኝ እያለ በማያስፈልገው ቦታና ሁኔታ ላይ ሲቀልድና ሲያሾፍ የሚውል አለ። ካልተሳቀለት ስለሚሳደብ በተናገረ ቁጥር አጠገቡ ያሉት ሁሉ ይስቁለታል። ካልሳቁለትማ ወዮላቸው።

ይህን ሁሉ ያነሳሁት "ቀልዶች ለምን ሁሉንም አያስቁም?" በሚል ያደረግሁት ሰፋ ያለ ጥናት ኖሮ ሳይሆን እንዲያው ልለው ለፈለግሁት ነገር መነሻ እንዲሆነኝ ብዬ ነው።

አንዴ አንድ አገሬ እያለሁ የሰማሁትን በጣም የሚያስቅ ቀልድ ለአንዱ አሜሪካዊ የሥራ ባልደረባዬ ነገርኩት። ይስቃል ብዬ ብጠብቀው ዝም ብሎ አፍጦ እየኝና አሳፈረኝ። " ምነው አያስቅም እንዴ?" ብዬ ብጠይቀው "ጨርሰሸዋል እንዴ?" አይለኝም መሰላችሁ። በሆዴ የት ይገባሃል ብዬ ቆሽሬ ተውኩት። አገኘሁታ እኔ ደግሞ ተራዬን። ሌላ ጊዜ ቀልድ ልንገርህ አለኝና ይህን ነገረኝ።

አንዱ አንዷን "በጣም ስለምወድሽ ላገባሽ ወስኛለሁ።" ይላታል። እሷም "አባቴን አነጋግረሃል?" ትለዋለች። እሱም "አዎን ብዙ ጊዜ አነጋግሬአቸዋለሁ
ቢሆንም አንቺን ነው የማገባው።" አላት ብሎ ጥርሱ እስኪረግፍ ሳቀ። እኔስ ማነኝና፤ ንቅንቅም አላልኩ።

"Isn't that funny?" አለኝ ባለመሳቄ እፍር ብሎ ከሳቁ እየተመለሰ።

"Not for me." አልኩትና ጥዬው ሄድኩ። ብድር የለብኝ።

ነገሩ እንግዲህ ከተለያየ የባህል ልምድ መምጣታችን መሰለኝ። እዚህ አገር የሚነገሩ ቀልዶች እኛን ባያስቁ ልንገረም አይገባም ለማለት ነው። ይህን ስል ታዲያ ምንም ቀልዳቸው አያስቀንም የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ አይደለም።

እስቲ አንዳንድ እዚህ አገር በቀልድ መልክ የሚቅርቡትን ጨዋታዎች እንዲገቡን አድርጌ የተረጐምኳቸውን ላቅርብላችሁና እንየው። አሳቃችሁም አላሳቃችሁ የናንተ ፋንታ ነው። ባያስቃችሁ አጠገባችሁ ስለሌለሁ አልናደድም።

---

### ሰይጣን ነኝ

ባሏ ሁሌ እየሰከረ አምሽቶ መምጣቱ ያናደዳት ሚስት ለማስጣል ብዙ ሙከራ አድርጋ አልሳካ አላት። ጓደኞቿን አማክራ አንድ ዕቅድ አወጣች። አንድ ምሽት ልክ እንደ ሰይጣን ለብሳ መልኳን በቀለም ቀያይራ እንደልማዱ አምሽቶ ሲመጣ ከቤት ውጪ ዛፍ ስ ትደበቅና ታስደነግጠዋለች።

ባልም "ማነህ አንተ?" ይላል በተኮላተፈ የሰካራም ድምጽ።

ሚስትም "ሰይጣን ነኝ!" ትለዋለች ጐርነን ባለ በሚያስፈራ ድምጽ።

ባልም፤ " ሃይ! ሰይጣን፤ ና ጨብጠኝ፤ እህትህ ሚስቴ እንደሆነች ታውቃለህ?" ይላል።

---

# ቢስቁም ባይስቁም

### ተዘርፌአለሁ!!

ባል አመሻሽቶ ወደ ቤቱ ሲገባ ሚስት አልጋው ላይ ጋደም ብላ በትዝብት ታየዋለች። ምንተፍረቱን እዚያው ፊትለፊቷ ልብሱን ማወላለቅ ጀመረ። ሱሪውን ሲያወልቅ ለካ የውስጥ ሙታንቱ የለም።

"እንዴ ሙትንትህ የት ሄደ?" ትለዋለች በመገረም።

ለማረጋገጥ ጉንበስ ብሎ ያይና፣ " ኸረ የፈጣሪ ያለህ፣ ለካ ቦርሳዬን ብቻ ሳይሆን እሱንም ዘርፈውኛል፣ እሱን አላስመዘገብኩም።" ይልና ምንተፍረቱን ሱሪውን መልሶ ይታጠቅና ከቤት ይወጣል።

---

### ወተት አዳዩ

እሳሉን ውስጥ ወተት አዳዩ ሱሪውን እያወለቀ እያለ ባል ሆዬ የረሳው ዕቃ ኖሮ ወደ ቤቱ ተመልሶ በሩን ከፍቶ ይገባል። ወተት አዳዩም ከፊትለፊቱ በውስ ልብስ ብቻ የቆመችውን የሰውዬውን ሚስት፣

"የእኔ እመቤት የወተቱን ዋጋ ቶሎ ካልከፈሉ እዚህ ምንጣፍ ላይ መሽናቴ ነው፣" ይላታል።

---

### ውሽቷን ነው!

ሁለት ጓደኞሞች ቡና እየጠጡ ያወራሉ።

"ሚስቴ ውሽታም መሆኗን ዛሬ አወቅሁ፣" ይለዋል።

"ምነው ምን አገኘህባት?" ይጠይቃል ጓደኛው።

"ትላንት የት አደርሽ ስላት ከጓደኛዬ ከአበበች ጋር አትሰኝም መሰለህ?"

"ታዲያ ውሸት መሆኑን እንዴት አወቅህ?"

"አበበች ያደረችው ከኔ ጋር ነዋ!" ይለዋል።

---

### ጸሎትሽ ሰምሯል!

የአስር ዓመት ልጅ እናቱን እንዲህ ይላል።
"ከዛፍ ላይ ብወድቅ ወይስ ሱሪዬ ቢቀደድ፣ የቱ ይሻላል እማዬ?
"ውይ ልጄ ምን በወጣህ! ከዛፍ ላይ ከምትወድቅ ሱሪህ ቢቀደድ ጸሎቴ ነው፣" ትለዋለች።
"እማዬ እንግዲያውስ ደስ ይበልሽ! ጸሎትሽ ሰምሯል፣"

---

### እኔን!

በክረምት ወራት አንድ አዛውንት በድጥ መንገድ ሲሄዱ እዳልጧቸው ይወድቃሉ። አንዲት ሴት ያዩ ኖረው "እኔ ልውደቅ!" ቢሏቸው "ቆይ እኔ ልነሳልሽና!" አሏቸው ይባላል።

ብርሀን አብርሃም (ከዲ.ሲ.)

---

### ምላስ ብቻ!

አንድ ሰው ሥጋ ለመግዛት ሥጋ ሱቅ ገብቶ ይጠይቃል።

ገዥ፣- ታላቅ አለ?
ሻጭ፣- የለም
ገዥ፣- ታናሽ አለ?
ሻጭ፣- የለም
ገዥ፣- (በመበሳጨት) ታዲያ ምን አለህ?
ሻጭ፣- ምላስ ብቻ

ወንድወሰን ይመር (ችካጎ)

---

### ምን ትጠብቃለህ?

አዛውንቱ አውቶቡስ ይጠብቃሉ። ዱሮ የሚያውቁትን አንዱን ሰውዬ ያገኙትና ሞቅ ያለ ሰላምታ ይለዋወጣሉ። ከዚያም "እንዴት ነው ሚስት አገባህ?" ይሉታል። እሱም "አላገባሁም፣" ይላቸዋል። "ምን ትጠብቃለህ ልጄ?" ሲሉት "አውቶቡስ፣" ብሏቸው እርፍ።

ፍቅሩ ገሠሠ (ችካጎ)

---

### እግዜር የባረከው!

አንድ ቄስ እንግድነት ተጋብዘው እሄዱበት ቤት ምሳ ቀርቦ ሲበላ የጋባገሮቹ ልጅ ከቄሱ ፊት ያለውን ሁሉ እየተስገበገበ ከበላ በኋላ ይነሳል። በሁኔታው የተቃጠሉት ቄስ ወዲያውኑ "ይኸ ልጅ እግዚአብሔር የባረከው ነው፣" አሉ። በልጃቸው ጋጠወጥነት የተናደዱት አባትና እናትም "ምን እግዜር የባረከው ይላሉ፣ የተጣላው በሉ እንጂ፣" ይሏቸዋል። "የተባረከ ልጅ ነው፣" ይላሉ አባ። "ኸረ እክዎን ይተውን" ይላሉ ወላጆች። "ቢሆን ነው እንጂ፣ ገበታውንስ አለመውሰዱ እሱ ሆኖ አይደል?" አሉ ይባላል።

ዳኛቸው ፋንታ (ዲ.ሲ.)

# መርካቶ

# MERKATO

Los Angeles, CA 90019
1036 1/2 South Fairfax Ave.

**ለግብዣ የሚያስፈልጋችሁ ሁሉ አለ።**

**We have everything you need to prepare an Ethiopian Feast.**

Fresh Teff Injera and meat
Ethiopian Green Coffee
Ambasha & Dabo
We also carry:

- *Ethiopian Traditional clothes*
- *cultural paintings*
- *Artifacts*
- *Gold & ornament*
- *Cassettes, vidieo tapes,*
- *Books, magazines*

ትኩስ የጤፍ እንጀራ፣ ሥጋ፣
ቡና፣እምባሻ፣ ዳቦ፣
እንዲሁም የአገር ልብሶች፣
ባህላዊ ሥዕሎች፣
ወርቅ፣ ጌጦች፣
ካሴቶች፣ ቪዲዮዎች፣
መጽሐፍት፣ መጽሔቶች፤

**ደውለው እነጋግሩን።**

For more information please call us at
(213) 935-1775

**በቅርቡ የወጣው**
**«የብከይ ነበልባል»**
**ባልተወለደው ልጁ ማስታወሻ፤ ከአሳምነው ገብረወልድ በመሸጥ ላይ ነው።**

# HARAR TRAVEL & TOURS

## ሐረር የጉዞ ወኪል

***Around the World Travel***
***Best International Air Fares on Major Airlines***

**Professional Courteous Staff ready to assist you**

*** Express Delivery Service**
*** Well Planned Itineraries**
*** Car Rental**
*** Hotel Reservations**
*** Very Low rates**

ለሥራ ጉብኝት ወይም ለዓመት ዕረፍት፤
የአይሮፕላን ጉዞ ማድረግ ቢያስፈልጎት፤
የተስተካከለ የተቃና ጉዞ እንዲሆንልዎ፣
በዋጋውም በኩል ብዙ ሳይጎዳዎ፤
ቲኬት ተዘጋጅቶ እንዲላክልዎ፤
ስልኩን ብድግ አርገው መደወል አይርሱ፤
ሐረር ትራቭልን ምን ጊዜም ያስታውሱ።

**For Reservations: Please Call**
**ሐኪም መሐመድ**
**HAKIM MOHAMED**

**(214) 247-2645 or (214) 490-1122 Fax (214) 247-5042**
**16000 Preston Rd., Suite 1576 - Dallas, Tx., 75248**

## ጨዋታዎች ??? ውድድሮች

## የአለፈው እስኪ እንፈትኖት መልስ

1. 12 ብርትኳን 2. 14 ብርትኳን 3. 20 ብርትኳን 4. 25 ብርትኳን 5. 18 ብርትኳን

በትክክል የመለሱ፤-

አቶ ዘውዴ በዳዳ ከቺካጐ ሁሉንም በትክክል መልሰዋል። የሰንጠረዡንም ጨዋታ በትክክል ስለመለሱና ስሀተትም ስለጠቆሙ 1 የላንዳፍታ መጽሔት በነጻ እንሰጥዎታለን። አቶ ታዬ ጥበቡ ከአዲስ አበባ የመጀመሪያውን ሁለቱን ተሳስተዋል። ሌሎቹን በትክክል መልሰዋል።

## እስቲ ይሞክሩት

እነዚህን 9 ነቁጦች በ4 ቀጥተኛ መስመሮች ያገናኙ። መስመር መሥራት ከጀመሩ እጅና መንቀል አይፈቀድም።

ዳኛቸው ፋንታ ናቸው ከዲ ሲ የላኩልን። እናመሰግናለን አቶ ዳኛቸው፤ ይልመድቦት ታዲያ።

ለእነኚህ አምስት ጥያቄዎች መልሳቸውን ላኩልን።

1. በሚሰለች ጊዜ ቢዘጋ የማይከፋው ?
2. ያጐቱ እህት ናት፣ አክስቱ ግን አይደለችም?
3. ራሱ ቃሉ ሲጠራ የሚጠፋ ?
4. በአንዱ ጫፍ እሳት በሌላው ጫፍ ሞኝ?
5. የሞት አስፈሪነት የበለጠ ጎልቶ የሚታይበት ወቅት?

## ቃላት በሰንጠረዥ

### የአለፈው መልስ

በትክክል የመለሱ፤

1. አቶ ዘውዴ በዳዳ (ቺካጐ)
2. አቶ ታዬ ጥበቡ (አ.አ.) ብቻ ናቸው።



እንዳለፈው ቃላት በሰንጠረዥ ጨዋታ ነው የሚጫወቱት። በእንግሊዝኛ ለተጻፈው የአማርኛ ትርጉሙን በመስጠት በአማርኛ ተጽፎ ባዶ ቦታ ለተተወው ስሜት በሚሰጥ የአማርኛ ቃል ሰንጠረዡን ይሞላሉ። መልሱን በሚቀጥለው እትም እናወጣለን። በትክክል ሠርተናል የምትሉ መልሱንና ስማችሁን ላኩልንና እናወጣዋለን።

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | ■ | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | ■ | 13 | 14 | 15 | 16 | ■ | 18 | ■ | 20 |
| 21 | 22 | ■ | 24 | 25 | ■ | 27 | 28 | 29 | 30 |
| 31 | 32 | 33 | ■ | 35 | 36 | 37 | ■ | 39 | 40 |
| ■ | 42 | 43 | 44 | 45 | ■ | 47 | 48 | 49 | 50 |
| ■ | 52 | 53 | 54 | ■ | 56 | 57 | 58 | ■ | ■ |
| 61 | 62 | 63 | ■ | 65 | 66 | ■ | 68 | 69 | 70 |
| 71 | 72 | ■ | 74 | 75 | 76 | 77 | 78 | ■ | 80 |
| 81 | ■ | 83 | 84 | 85 | 86 | ■ | 88 | 89 | 90 |
| 91 | 92 | 93 | 94 | 95 | ■ | 97 | 98 | 99 | 100 |

## ወደ ጎን

1. የሐረርጌ አንድ አውራጃ
7. He made them agree.
13 When I keep quiet
21. Ethiopian sauce
24. He laughed
27. To advise
31. Couple
35. Portrait
39. He divorced
42. If we run
47. To put in
52. ጅማ አጠገብ ያለ ትልቅ ከተማ
56. Loan
61. Let us see
65. W.C.
68. When I hear
71. He forgot
74. Mirror
88. Finished
91. Patience
97. In the wind

## ወደ ታች

1. Delinquent
3. Banana
4. For lunch
5. Let her put it
8. When I kiss
10. To strengthen
22. የሞተ አውሬ የሚበላ
27. To adapt
29. He opened
33. Rock
44. Grievance
48. የ____ ሃይማኖት ተከታይ
56. Strength
61. recess
65. Magic
70. To cry
74. Response (answer)
83. Sheep
89. ቆዳውን አ _ _I

## የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ለመሆን ወይም በስጦታ ለመላክ

የላንዳፍታ መጽሔት ልክ እንደወጣ በፖስታ ቤት እንዲደርስዎ የሚቀጥለውን ቅጽ በመሙላት ከነክፍያው ይላኩልን።
አከፋፈል፤ - ለአራት ተከታታይ እትሞች
ለ U.S.A. $10.00
ለ Canada U.S.$12.00
ለ Europe U.S.$15.00

---

## የላንዳፍታ መጽሔት ማዘዣ ቅጽ

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY/STATE/ZIP ______________________________

PHONE ______________ ______________

BACK ISSUE ORDERS ______________________________

..........................................................................

## ላንዳፍታ መጽሔትን ለጓደኛ፣ ለዘመድ ይላኩ፤ የቤተሰብ መጽሔት ናትና፤

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY/STATE/ZIP ______________________________

PHONE ______________ ______________

BACK ISSUE ORDERS ______________________________

---

የሚያዙዋቸውን መጽሔቶች ክፍያ Payable to LANDAFTA በማለት ከቅጹ ጋር በአድራሻችን ይላኩ። እባክዎን አድራሻዎን ሲጽፉ ጉልህ ያድርጉት። ክፍያው በቼክ ወይም በMoney Order ሊሆን ይችላል። ያለፉትን እትሞች ለማዘዝ ከፈልጉ ይህንኑ በቅጹ ላይ ይጥቀሱ።

LANDAFTA
P.O.Box 409358
Chicago, IL 60640
(312) 561-6865

# በላንዳፍታ ማስታወቂያ ማውጣት ለሚፈልጉ

በአጭር ጊዜ ዝናን ያተረፈችው የአማርኛ የመዝናኛ መጽሔት ላይ
ድርጅቶን ወይም የንግድ ሥራዎን ያስተዋውቁ።

ማስታወቂያዎን በአማርኛ ተርጉመን ቆንጆ ቅርጽ (Design) በመስጠት እናወጣዋለን።

ጠቅላላ በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮጳና በኢትዮጵያ አከፋፋዮች ስላሉን ለብዙ ኢትዮጵያኖች የምትዳረስ መጽሔት መሆኗን አይዘንጉ።

ክፍያችን ከሌሎች በጣም ያንሳል።

ለአንድ እትም የማስታወቂያ ዋጋችን እንደሚከተለው ይሆናል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | ለ 1/4ኛ ገጽ | | - $45.00 |
| 2. | ለ 1/2ኛ ገጽ | | - $80.00 |
| 3. | ለሙሉ ገጽ | | - $130.00 |
| 4. | ገጽ ሽፋን ከውስጥ | (ፊትለፊት) | - $150.00 |
| | | (ከጀርባ) | - $140.00 |
| 5. | ገጽ ሽፋን ከውጭ (ጀርባ) 3 ከለር | | - $300.00 |

(Camera Ready ለሆኑና ትርጉምና የመሳሰሉትን የእኛን ምንም ሥራዎች ለማይጠይቁ ማስታወቂያዎች ከላይ ከጠቀስነው ዋጋ 10% እንቀንሳለን። (ዋጋዎች ወደፊት እንደየሁኔታው ይቀየራሉ)
ማስታወቂያ ማውጣት የምትፈልጉ ከዚህ በታች ያለውን ቅጽ በመሙላት ከክፍያው ጋራ ትልኩልናላችሁ።

---

## የላንዳፍታ ማስታወቂያ ማዘዣ

ስም፤- ______________________________

አድራሻ፤ ______________________________

______________________________

ስልክ ቁጥር፤ ______________ ______________

የሚፈልጉት

ገጽ፤ ______________________________

የእኛን ሥራ ይጠይቃል ______________ አይጠይቅም (Camera ready ነው ______________

ክፍያው $ ______________ ከዚህ ጋር ተያይዞ ተልኳል።

የሚከፈለው በቼክ ወይም በ Money Order Payable to LANDAFTA ተብሎ ነው።

LANDAFTA

P.O.Box 409358

Chicago, IL 60640


ለማንኛውም ጥያቄ በስልክ ቁጥር (312) 561-6865 አነጋግሩን።

ዋሽንግተን ዲ ሲ አካባቢ ላላችሁ አዲሱ ገበያ አዳራሽን አነጋግሩ።

Live Reggae

# THE WILD HARE

& SINGING ARMADILLO FROG SANCTUARY




# CHICAGO

3530 No. Clark

(312) 327 - Hare

$2.00